

ዋጋ ብር 3.00

© Safeguarding Religious Treasures of the Ethiopia Orthodox Church

# ፈለገ ጥበብ

፫ ዓመት ቁጥር ፫ ሚያዝያ - ሰኔ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም



- ቋንቋችን አንድ ይሁን
- ሕገ እግዚአብሔር ይጠበቅ
- ከሆሣዕና እስከ ትንሣኤ
- ጾም በመጽሐፍ ቅዱስ
- የመናፍቃን ድብቅ ዓላማ ሲጋለጥ
- ዕድሜአችሁ እንዲረዝም እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ጠብቁ

www.ethiopianorthodox.org

# እኛና እናንተ

## ሁሉም ነገር በአግባቡ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

ውድ የፈለገ ጥበብ መጽሔት አዘጋጆች እንደምን አላችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ።

መጽሔታችሁ ለሃይማኖታችን እድገት እና ብልፅግና ካላት አስተዋፅኦ አንፃር ወድጃታለሁ። በዚሁ ገፁብት፡፡ ዛሬ እኔም አንድ መልእክት ላስተላልፍበት ፈልጌ ነበር። ከፈቀዳችሁልኝ እኛ ሰዎች የእግዚአብሔር መንግሥት ለመውረስ ከአስርቱ ትእዛዛት በተጨማሪ መጾም መጸለይ፣ መስገድና፣ መመጽወት ይጠርብናል። ታዲያ ሁሉም ነገር በአግባቡ እና በስርዓቱ ቢሆን ጥሩ ነው። ለዛሬ ማንሳት የፈለኩት ስለ መመጽወት ነው። መመጽወት (መስጠት) ማለት ካለን ለሌለው ወገናችን የምናካፍለው ነገር ማለት ነው። ታዲያ መመጽወት ያለብን መቼ እና እንዴት ነው? መቼም እኛ ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመላለስ ያጡ እና የተቸገሩ ወገኖቻችን በቤተ ክርስቲያን በር አካባቢ ሁል ጊዜ እናገኛለን። እነሱ በተቀመጡበት ያለንን ብንረዳቸው ጥሩ ነው። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በተለይም በቅዳሴ እና በትምህርት ሰዓት እየተዘዋወሩ ለሚለምኑ ነዳያን መስጠት በበኩሌ እንደ ኃጢአት ነው የምቆጥረው። ምክንያቱም እግዚአብሔር በሚመሰገንበት ሰዓት እና እኛ በተመስጦን በምናስቀድስበት ወቅት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እየጮሁና በመሀከላችን እየገፈታተሩን የቅዳሴውን ሥርዓት ለሚረብሹና ኅሊናችንን ለሚያስቱ ሰዎች መመጽወት ትክክል አይመስለኝም። ይህ ሲባል፣ እንመጽውት ማለቴ አይደለም። ነገር ግን በአግባቡ እና በሥርዓቱ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር በማያጣላን መልኩ ይሁን።

ዳንኤል ኢብራሂም ነኝ

ከካዛንቺስ

### ከአዘጋጅ:-

ውድ ወንድማችን ዳንኤል ኢብራሂም አንተ እንደ ተናገርከው ዛሬ በአብዛኛው በቤተ ክርስቲያኖችን መላ ያጣ ልመና እየተስፋፋ ነው። በዚሁ በኩል የምእመናን ተሳትፎ እንዳለ ሆኖ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ከአስተዳድሩ ጀምሮ እስከ ዘበኛው በአጥቢያው (በቅጽረ ቤተክርስቲያን) የሚከሰተውን ማንኛውንም ነገር መቆጣጠርና ማስተናገድ ግዴታ አለባቸው።

ይሁንና ምን ችግረኛ እየተባለ ለማኙ፣ ነጋዴው፣ ሌላውም ቅጥ ያጣ ንግድ በየወርኃ በዓሉ የሚታየው በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ነው።

ስለዚህ ጉዳዩ አሳሳቢ እየሆነ ስለመጣ ማንም ሰው በቅዳሴና በስብከት ጊዜ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን መለመንም ሆነ መነገድ ችግር እያስከተለ ስለሆነ። ለዚህ አፈጻጸም ስኬታማነት የምእመናን ተሳትፎም ወሳኝ ሆኖ። የሚመለከታቸው አለቆችና ሠራተኞች ግቢውን የማስጠበቅ ኃላፊነት ስለ አለባቸው ሊያስቡበት ይገባል።

## መጽሔታችሁ የሰሎሞንን ጥበብ የያዘች ናት

ሰላም ጥበብንና ፍቅርን ያደላችሁ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን አሜን።

ፈለገ ጥበብ ፪ኛ ዓመት ቁጥር ፫ ላይ የነቢዩ ኤልያስ ስዕል በማየቴ በጣም ተደስቻለሁ። በጉጃም ክፍለ ሀገር የሚገኘውን እኔም ስለማውቀው ከብዙ በጥቂቱ የቤተ ክርስቲያኑንና የኤልያስን ታሪክ አውጥታችሁታል። በይበልጥ ፩ኛ መ.ነገ.፲፯ ጀምሮ እና ፪ኛ ነገሥት ም.፪፣ ጀምሮ ያለውን ታሪኩን በሙሉ አምድ ስጥታችሁ ብታወጡት ትልቅ ትምህርት አለው በዩ እምናለሁ ሌላው በአዋሽ ፯ ኪሎ ከተማ የምትገኘው ቅድስት ማርያም አገልጋዮችም ሆኑ ምዕመናን ፈለገ ጥበብን እያገኙም እባካችሁ አዘጋጆች መጽሔታችሁ የሰሎሞንን ጥበብ የያዘች ናትና በየአቅጣጫው እንድትዳረስ አድርጉ።

ይታየው ታገለ ከአዋሽ ፯ ኪሎ ከተማ

(ወልደ አማኑኤል) ሠን ሥራዎች

### ከአዘጋጅ

ውድ የመጽሔታችን ደንበኛ መልእክትዎን አድርሰናል። ለመጽሔቱ ስርጭት መስፋፋት የሁሉም ጥረትና ቀና አመለካከት ስለሚጠይቅ በእናንተ በኩልም ወስዶ ሊያሰራጭ የሚፈልግ ካለ በእኛ በኩል ለመስጠት ዝግጁ ነን።

## በጣም ወድጃታለሁ

መጽሔቷን እጅግ በጣም ወድጃታለሁ። ጥሩ ትምህርት ሰጭ መጽሔት ናት በቀላሉ ለማግኘት እጅግ በጣም ተቸግሬ ነበር። ነገር ግን ከ፫ ወር ፍለጋ በኋላ አድራሻችሁን ማግኘት ቻልኩኝ ወዲያውኑ ፈለገ ጥበብም ደረሰችኝ። በዚህም እግዚአብሔርን አመሰግንኩኝ። ከአሁን በኋላ ቋሚ ደንበኛ አባል ለመሆን እፈልጋለሁ እንደ እኔ መጽሔቷን ለማግኘት የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉና መላክ የሚቻልበትን መንገድ አመቻቹና ላኩልን ክፍያውን ለመላክ አመች በሆነው መንገድ እንልክላችኋለን በሙከልናም ላከፋፍልላችሁ ፈቃደኛ ነኝ።

አይናለም አውግቸው

ከጥባሴላ ኢጣሊያ

### ከአዘጋጅ

ውድ ደንበኞችን አስተያየትሽንና ጥያቄሽን በደስታ ተቀብለነዋል ይህ የሁሉም ደንበኞቻችን ጥያቄ በመሆኑ ስለ አላላኩና የዋጋውን ተመን በተመለከተ በዚህ ሕትም አውጥተናል የሁሉንም ጥያቄ መመለስ እንችላለን ብለን እናምናለን። በተሳትፎሽ ቀጥዪ።

## ይድረስ ለፈለገ ጥበብ መጽሔት ዝግጅት ክፍል

ብዕሬን አንስቼ ወደ እናንተ የጻፍኩት ጥያቄ ለመጠየቅ ነው። ይኸውም መዝሙር ግጥም በደብዳቤ ብልክላችሁ ሳንሱር ታደርጉልኛላችሁ ወይ? ብርስ ያስከፍላል? እስከ አሁንስ ዘማርያን በእንዴት ዓይነት መልኩ ነው መዝሙራቸውን የሚያወጡት?

ዮሐንስ ከአዲስ አበባ

**ከአዘጋጁ**:- ውድ ጠያቂያችን ጥያቄዎቹን በሙሉ ተመልክተናቸዋል በትክክል መጠየቅ የሚገባው ጥያቄ በመሆኑ በሚከተለው ሁኔታ አስተናግደነዋል።

ማንኛውም ወጣት ዘማሪ መዝሙር ከማውጣቱ በፊት በቅዱስ ሲኖዶስ በተወሰነው መሠረት ዜማውና ግጥሙ በማደራጃ መምሪያችን ተመርምሮና ታርሞ ካልወጣ በቤተ ክርስቲያን በውደ ምሕረት ሁሉ እንዳይዘመር ተከልክሏል። ስለዚህ ይህንን አውቀው በአሁኑ ሰዓት መዝሙር የሚያሳትሙ ወጣቶች በሙሉ መዝሙራቸውን በግንባር ይዘው በመቅረብ አስመርምረው የማረጋገጫ ደብዳቤ ተጽፎላቸው በማውጣት ላይ ይገኛሉ። ሳንሱር ለማድረግ ምንም ዓይነት ክፍያ የሌለ መሆኑን ልናስገነዝብ እንወዳለን።

## ለብፁዕ አቡነ ቁርሎስ ሊቀ ጳጳሳት

ከገጽ 17 የዞረ

መሥዋዕተ መድኃኒት መዓዛ ዕጣን
በቃለ በረከቱ ዓለም የሚድን
እናመሰግናቸው ክህናት አብረን
ኅረይኑ ወኄመኑ እያልን።

### መወድስ

ለጴንጤና ጆባ ውሾች ሁሉን ለሚበሉ
እንዳንበኀ ክህናት በየምንገዱ ቢለፈልፉ
ተንሥተዋልና በጥብት በክህደት መርዛቸው ሊሰክሩ
በያለንበት ንቅተን እንተኛ
ሰላም የለምና እነሱ ካልጠፉ
ጤንነትንም የምትሹ
በቃለ ወንጌል በትር ለመከላከል ተሰለፉ
ዳግመኛም ሂ ተጠንቀቁ እንዳትገቡ ከጉርፉ
የከርምት ወሆች ጴንጤና ጆባ ዘመናቸውን አስቢያሳልፉ
ወንጌል ጉዳናን ትተው ተንጠልጥለው ያሉ ቫፉፉ
በክህደት የውሃ አደጋ ብዙች አሉና የታጠለፉ

ደራሲና ጸሐፊ መሪጌታ እሣላፊ



www.ethiopianorthodox.org

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃና ማስተባበርያ መምሪያ

በየ፫ ወሩ የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት

# ፈለገ ጥበብ

፫ኛ ዓመት ቁጥር ፰

ሚያዝያ – ሰኔ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም

## ማውጫ

ቋንቋችን አንድ ይሁን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፪

ቃለ በረከት

ምጽአተ ክርስቶስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፫

ሕገ እግዚአብሔር ይጠበቅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፭

ትምህርተ ሃይማኖት

ከሆሣዕና እስከ ትንሣኤ . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፱

ለብፁዕ አቡነ ቁርሎስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፯

እኔም ወጣት ነበርኩኝ

የልማት አባት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፰

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

ጾም በመጽሐፍ ቅዱስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፩

ከወጣቱ ለወጣቱ

የመናፍቃን ድብቅ ዓላማ ሲጋለጥ . . . . . . . . . . . . . . ፳፬

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

«ዕድሜአችሁ እንዲረዝም እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ጠብቁ» . . . . . . . . ፳፮

መግረሬፀር

እስከ ሞት የታመንህ ሁን . . . . . . . . . . . . . . . . ፳፰

ቤተ ክርስቲያናችን ኤድስን በመከላከል ያገኘችው ዓለም አቀፍ እውቅና . . . . . ፳፱

ዜና መጽሔት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፴፩

እኛና እናንተ . . . . . . . . . . . . . . . . . . የሽፋን የውስጥ ገጽ

አርታዕያን(ኤዲተሮች)

ሊቀ ካህን ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ

መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

ቀሲስ በላይ ተገኝ

አዘጋጆች

ዋና አዘጋጅ መምህር ዕንቈባሕርይ ተከሥተ

ም/ዋና አዘጋጅ መ/ም ሰሎሞን ገብሩ

ስልክ 56-26-52፣ 55-00-98፣

55-00-99 Ex 46

ፖ.ሣ.ቁ.81286 – አዲስ አበባ

ርዕሰ አንቀጽ

# ቋንቋችን አንድ ይሁን

በሀገራችን በኤድስ ላይ እየተደረገ ያለው የመከላከል እንቅስቃሴ አበረታች ቢሆንም የመከላከሉ መንገድ አንድ ወጥ አለመሆን ግን በአጭር ጊዜ የሚፈለገው ውጤት ለማምጣት አልተቻለም።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አቋምና እንቅስቃሴ ግልጽና የማያሻማ ነው። የሕዝቡን ክብር እና ባህል የጠበቀ ነው።

ቤተ ክርስቲያኒቱ የምታምንበት እና የምትከተለው መርህ በሕግ አምላካዊ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት፣ አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ተወስኖ እንዲኖር ነው። ይህ ትምህርት አዲስ ወይም ጊዜ አመጣሽ አይደለም። ከብዙ ዘመናት ጀምራ ሕዝቡን አስተምራ ሕዝቡን ስትመራበት የነበረ ነው።

ቤተ ክርስቲያኒቱ አሁንም ይህን መርህ ይዛ ኤድስን ለመከላከል ከከተማ እስከ ገጠር ድረስ በግንባር ቀደምትነት በማስተማር ትገኛለች። ለዚሁም በክፍላተ ሀገር በየገጠሩ ከምታካሂደው ጉባኤ ሌላ በቅርቡ መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት መሪነት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ለመላ የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት ወጣቶች እና ለየድርጅቱ ሠራተኞች የተደረገው ታላቅ ጉባኤ በቂ ማስረጃ ነው።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ዓላማ ለዚሁ ኤድስ ለሚባለው ቀሳፊ በሽታ ፍቱን መድኃኒት አንድ ለአንድ ጸንቶ መኖር መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

የመገናኛ ብዙኃን ሰዎች እና የዘመኑ ጠበብት ነን ባዮች ግን ኤድስን ለመከላከል መጀመሪያ መታቀብ፣ ወይም አንድ ለአንድ መወሰን፣ ይህ ካልሆነ ደግሞ በሰው ሰራሽ (በኮንዶም) መጠቀም ኤድስን መከላከል ይቻላል የሚል ነው።

በዚህ መካከል በኮንዶም ንግድ ገንዘብ የደራላቸው ነጋዴዎች ኃላፊነት በጐደለው አገላለጽ በኮንዶም ብቻ ኤድስን መከላከል እንደሚቻል አድርገው ነጋ ጠባ በመገናኛ ብዙኃን እያስተላለፉ ይገኛል።

በዚህ ሂደት ውስጥ ለመከላከል ተብሎ ቢነገርም ቴሌቪዥንና ሬድዮን የሚከታተለው ሁሉ አንድ አይደለም። ለበጎ ተብሎ የሚነገረው በዚያ ብቻ ይተረጐማል ብሎ ማሰብም የዋኅነት ይሆናል። ለካ እንዲህም አለ ብሎ ያላሰበውን ለመሥራት የሚሞክር እንደሚኖር መዘንጋት አልነበረበትም።

በሌላ በኩልም በዓለም ላይ ከ፴፮ ሚልዮን በላይ የዚህ መቅሠፍት ተጠቂ መሆኑ ሲነገር መከላከያ ተብሎ የሚነገርለት የፋብሪካ ውጤት (ኮንዶም) በማጣቱ ነው ብሎ መገመት ራስን ከማታለል ያለፈ ፍልስፍና አይሆንም።

ከሚስቱ በስተቀር ምንም ለማያውቅ አባወራ ገበሬ ስለኮንዶም ጠቃሚነት ማስተማር ማለት፣ ሂድና ...ይቆጠራል።

ለገበሬው ሆነ ለሌላው ኅብረተሰብ የሚበጀው ግን ይህ ሳይሆን ተጠንቅቆ እንዲኖር ወደ ከተማ ሲሄድ ከሚስቱ በስተቀር ከሌላ ሴት ከተገናኘ በበሽታው እንደሚጠቃ መንገር፣ ማስተማር ነው። የኤድስ መድኃኒት በጋብቻ ሥርዓት ጸንቶ፣ ወይም በንጽህና ተጠብቆ መኖር መሆኑን በግልጽ እየታወቀ፣ ለወጣቱ ትውልድ በተለይም በንጽሕና ለሚኖር ገበሬ ሰው ሠራሽ መከላከያ ተጠቀም ብሎ ማወጅ በንጹሕ ገበሬ ሕይወት ላይ መፍረድ ይሆናል።

እንግዲህ ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው ሊታረቁ የሚችሉ ነገር ግን ተወያይቶ መፍትሄ የሚያስፈልጋቸው ነጥቦች እንዳሉ ግልጽ ነው።

በቤተ ክርስቲያኒቱ በኩል ፈጽሞ መታቀብ የሚለው የራሷ አቋም ስለሆነ በትምህርቱ ትቀጥልበታለች። በሕግ ተወስነው ለሚኖሩ ደግሞ እንደዚያው ከጥንት ጀምሮ የምታስትምርው በመሆኑ ሰው ከኤድስ በሽታ የሚድነው ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ፣ በሥርዓት መኖር ሲችል ነው። ብላ ስለምታምን፣ አሁንም ወደፊትም ታስተምረዋለች።

በሰው ሰራሽ (በኮንዶም) ኤድስን መከላከል ይቻላል እየተባለ ያለው ግን የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እውነት አልተገኘበትም። ሰው በኮንዶም የሚከላከል ቢሆን ኑሮ እስከ አሁን ድረስ በሚልዮን የሚቆጠር (ሰው ሰራሽ) ኮንዶም ተሸጧል። ዛሬ እየተነገረን ያለው አስደንጋጭ የበሽተኞች ቁጥር ብዛት ባለተከሰተም ነበር።

ሰው ሰራሽ (ኮንዶም) ሕገ ወጥነትን ከማስተማር በስተቀር አንዳችም ለውጥ አላመጣም። መሠረታዊ ችግሩ በአንድ በኩል ኤድስን እንከላከላለን እያሉ በሌላ በኩል አመንዝራነትን የሚያስፋፉ ሥራ እየሠሩ መገኘት ነው። ኤድስን ለመከላከል የአመንዝራነትን ሥራ ከሥሩ ማጥፋት ያስፈልጋል። በቂ ቅስቀሳ በማድረግ በገጠርም በከተማም በብቃት ማስተማር ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው።

ኤድስን አስመልክቶ በአዲስ አበባና በአንዳንድ ከተሞች ስብሰባዎች ተደርጓል። ተናጋሪዎችም ተናግረዋል፣ በቂ ግን አይደለም፣ ውጤቱ እንዴት ይገመገማል? ራስ ሰርቶ በራስ እንዲህ ተደርጓል ማለቱ የትም አያደርስም። ሁሉም በአጭር ታጥቆ በበሽታው (በመቅሰፍቱ) ላይ መዝመት አለበት። በኮንዶም ተጠቀሙ ማለት አመንዝራነትን ሕጋዊ እንደማድረግ ይቆጠራል። ዝሙት በሕገ እግዚአብሔር የሚያስፈርድ ከመሆኑም ሌላ በሀገሪቱም ሕግ ወንጀል ነውና፣

በዚህ በኩል ከዛምቢያ ትምህርት መውሰድ ይቻላል። «የኤድስ ቫይረስ ስርጭትን ለመቀነስ በሚል ሽፋን በቴሌቪዥንና በሬዲዮ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎች ኤድስን ከመከላከል ይልቅ ወጣቱን ለልቅ ግብረ ሥጋ ግንኙነትና ለሥርዓተ አልበኝነት በመጋበዝ በሽታው የበለጠ እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኖአል።» በማለት የዛምቢያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ባቀረቡት ከፍተኛ ተቃውሞ የሀገሪቱ መንግሥት የኮንዶምን ማስታወቂያዎች በቴሌቭዥን እንዳይተላለፍ አግዷል» በእርግጥ ድርጊቱ ይበል የሚያሰኝ ነው።

በሀገራችንም በተለይ ወጣቶች የሥርዓተ ጋብቻ ክቡርነትን ተገንዝበው በሥርዓተ ተክሊል እንዲጋቡ፣ ሌላው ኅብረተሰብም ዘመን ባመጣው ማስታወቂያ ሳይዘናጋ ቃል ኪዳኑን ጠብቆ በቅድስናና በንጽሕና መኖር ሕይወቱን ከመቅሠፍት እንዲታደግ ይግባዋል።

እንግዲህ በእኛ በኩል የምንለው የኤድስ ቫይረስን ለመከላከል ቋንቋችን አንድ ይሁን፣ አንድ አጀንዳ ይኑረን፣ ሕዝባዊ፣ ሀገራዊ ኃላፊነትና ወገናዊነት ይሰማን። ልክ ድንቁርናን ለማጥፋት ዘመቻ በኅብረት እንደ ተደረገው ሁሉ ዛሬም ወደ ገጠሩ ሰርጾ በመግባት በኅብረት ኤድስን ለመከላከል መዝመት ይኖርብናል። ✣

# ምጽአተ ክርስቶስ

**ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት መጋቢት ፱ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም**

**የደብረ ዘይት ዕለት በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ያስተላለፉት ቃለ በረከት።**



በውጭም በውስጥም ያላችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ሁላችሁ እንደምን አላችሁ፣ እግዚአብሔር አምላክ ይባርካችሁ፣ ይቀድሳችሁ። እነሆ ቸሩ አምላካችን እንደገና ዓምና ባከበርነው በዓል ማስጠንቀቂያው የሰማንበት ጊዜ አልፎ እንደ ገና ሌላ ጊዜ ሠጥቶናል። ለዚሁ በጣም ከበድ ያለው ስሜት ያለው ዕለት በሰላም ጠብቆ አድርሶናል። ይህም ማለት እግዚአብሔር ሥራውን እየሠራ ነው። አንድም ጊዜ ያቋረጠበት የለም። ዓምና መልእክት አስተላልፈን ነበር፣ እግዚአብሔር በሕይወት እንዲጠብቀን፣ ለንስሐ ሞት እንዲያበቃን፣ ለምነነው ነበር።

እኛ በቃላችን ብንጸናም፣ ባንጸናም፣ እግዚአብሔር በባሕርዩ ቸር ስለሆነ ጠብቆናል።

እግዚአብሔር ዕድሜ የሚሰጠንና በየጊዜው ሕይወታችንን በሰላም ጠብቆ የሚያኖረን፣ ለንስሐ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው የጴጥሮስ መልእክት የእግዚአብሔርና የሰው የዘመን አቆጣጠር ምን እንደ ሆነ ከተናገረ በኋላ እግዚአብሔር ደግሞ ለሰው ዓመታትን የሚሰጠው፣ ለምን እንደ ሆነ በግልጽ ተናግሯል።

እግዚአብሔር በፍቅር የፈጠረው ፍጡር እንዲጠፋ ፈቃዱ አይደለም፣ ሰው በደካማነቱ እንዳይጠፋ፣ ባለማስተዋል፣ የማይገባውን ሥራ በየዕለቱ እየሠራ፣ በዚያው ሳይስተካከል፣ እየተሰናከለ ሳለ እንዳያልፍ፣ ለክብር የተጠራ ነውና፣ ለተጠራበት ደረጃ ሳይደርስ እንዳያልፍ እግዚአብሔር ሰው ስሕተተኛ መሆኑን እያወቀ፣ ዘመናትን ይሰጣል።

ለምን? መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው በቅዱስ ጴጥሮስ አንደበት እንደ ተናገረው ንስሐ ይገባ ዘንድ፣ ይቅርታ ይጠይቅ ዘንድ ነው።

ነገር ግን ቀደም ብሎ እግዚአብሔር በኋለኛው ዘመን ለፍርድ ይመጣል ተብሎ የተነገረውን፣ ብዙ ሰዎች ግዴታቸውን በመፈጸም ፈንታ ያን የታዘዘውን ትእዛዝ ያሻሽሉታል። ረዘመ፣ አይመጣም ይሆናል፣ ብለው ምክንያት እየፈለጉ ግዴታቸውን ላለመፈጸም፣ መሳሳታቸውን እንዳልተሳሳቱ ለማስመሰል፣ ምክንያት እየፈጠሩ፣ ራሳቸውን የሚያጽናኑ አሉ።

እንደ እውነቱ ከሆነ በየአንዳንዳችን የሚጨነቅ ልቡናኮ አለ፣ ግዴታየን አልፈጸምኩም የሚልኮ አለ። እች በተፈጥሮ የተሰጠች መዘዘኛ ትደነግጣለች፣ ትፈራለችኮ፣ ያንን እውነትን ለማደንዘዝ የፈጠራ ቋንቋ ያመጣሉ። ዘግይቷል፣ ተረስቷል፣ አይመጣም፣ እያሉ። ምን ለማድረግ ነው የእግዚአብሔርን ሕግና ትዕዛዝ አይፈጸምም ብለው ደፍረው የሚናገሩ፣ ሰዎች በምን ምክንያት ነው? አሁን ስለ ተሸነፉ ነዋ! ትእዛዝ ፈጻሚዎች ስለ አልሆኑ የሚሠሩትን ስሕተት በዚያ አሚልቶ ትክክለኛ ለማስመሰል ነው።

እግዚአብሔር ግን ተናገረ፣ አይ አላውቃችሁም፣ እግዚአብሔር የሚጠቀመው አቆጣጠር እና የሰው አቆጣጠር የተለየ ነው። የእግዚአብሔር አንዲት ቀን በሰው ሺህ ዓመታት ናት። የሰው ሺሕ ዓመታት በእግዚአብሔር አንዲት ቀን ናት።

ስለዚህ እግዚአብሔር በወሰነው ውሳኔ የሚመጣ ነው። በዚህ መካከል

www.ethiopianorthodox.org

መንፈስ ቅዱስ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይናገራል። «እግዚአብሔርሰ ገሀደ ይመጽእ ወአምላክነሂ ኢያረምም እሳት ይነድድ ቅድሜሁ»

እግዚአብሔር በግልጥ ይመጣል አምላካችንም ዝም አይልም፣ በፊቱ እሳት ይነዳልና። ብዙ ጊዜ ዝም ብለዋል፣ በነበርንባቸው ዘመናት ሁሉ ጣዕም ባለው ድምፅ ከማስተማር በቀር አልተናገረም፤ አሁን ግን ሊናገር ነው። በዘመናት ውስጥ እኛ ልንሠራው የታዘዝነውን ሁሉ የሚያስፈልገንን መሣሪያ ሁሉ ጨምሮ ከሠጠን በኋላ ዝም ነው ያለው። ነገር ግን ይመጣል፤ ጌታ መጥቷል፤ አስተምሮዋል፣ መከራ ተቀብሏል። ተሰቅሏል፣ ሙቶ ተነሥቷል፣ ይህ ሁሉ ተነግሯል። ሰው ደግሞ ምን መሆን እንዳለበት ተናግሯል። መዋዕለ ዘመኑን በምን መፈጸም እንዳለበት ለሰው ልጅ የሚያስፈልገው መሣሪያ ተሰጥቶታል።

ግን እንደ ምድራዊ ባለሥልጣን፣ እንደ ምድራዊ አሠሪ እየተቆጣጠረ አንተ ይህን አድርግ፣ ምነው ዝም አልክ? ምነው ዘገየህ? እያለ አያስጨንቅም፣ ያ ሁሉ ዘመናት የሰማንያ፣ የዘጠና ዓመት ለአንድ ሰው ዕድሜ ቀላል አይደለም። አሁንም እግዚአብሔር ዕድሜን እየሰጠ ነው።

እኛ ነው የማንጠቀምበት እንጂ እግዚአብሔርማ ጊዜውን ሰጥቶናል። መሬት እየመሸብን አይደለም። እግዚአብሔር ለዚህ ያህል ጊዜ ለሰው ልጅ የሰጠው የሚናገርበት ጊዜ እንዳለ ይናገራል። የእነዚህ ሁለቱ አመጣጦች ብቻ ነው ማወቅ የሚያስፈልግው።

በሐዘን፣ በርኅራኄ፣ በፍቅር፣ በቸርነት ብዛት፣ ከዚሁ የተነሣ ባሕርዩን ዝቅ አድርጎ ለአገልጋይነት ነው የመጣው፣ በዚሁ ሰውን ወደ ተፈጠረበት ክብር ለመመለስ ያላደረገው ነገር የለም። ከኃጢአት በስተቀር እንደ ሰው በየጥቂቱ አደገ፣ ይላል። ኃጢአት ከመሥራት በቀር ጽድቅን በመሥራት፤ ሰው ወደ ጽድቅ የሚመጣበትን በማስተማር ረዥም ጊዜ ሠጥቷል። እንግዲህ የሚናገረው ምን ይሆን? ምን ያልሠራነው ነገር አለ? ያ ሁሉ መሣርያ ተሠጥቶናል፣ ዘመናት ተሰጥተውናል፤ ያልሠራነው ምን አለ?

እንግዲህ አባቶች ይህ ሥርዓት ከተጀመረበት ጀምሮ ጌታ ባስተማረው መንገድ ሕዝብ ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲመጣ፣ እግዚአብሔር የሰጠው ነው። በፈለገው ዓለም ይኑር፣ ታድያ ግን አምላኩን በመርሳት አይደለም። ነፃነት አምላክን በመርሳት፣ ግዴታውን ባለማክበር ዝም ብሎ እንስሳ መሆን አይደለም። የተሰጠውን ደረጃ በደረጃ እየፈጸመ እንዲኖር ነው የታዘዘው።

ስለዚህ ይህች ዕለት እንዲሁ ታሪኳን በምናነብበት ጊዜ የመጨረሻይቱ ቀን ናት። አሁን እግዚአብሔር በግልጥ ነው የሚመጣው። ይናገራል ዝም አይልም።

«እሳት ይነድድ ቅድሜሁ» የእግዚአብሔር ቁጣ ነው ምንድነው? ስለ ዚህ ልጆቻችን እኛ ማድረግ የሚገባን እንዳለ ብዙ ተነግሯል፤ ጌታችን አስተምሯል። አባቶች ስለ ንስሐ ደጋግመው ተናግረዋል። ለምን? ለዚህች ቀን የሚሆን ነው ለዚህችው ቀን በምንቀምርበት ጊዜ፣ ወደዚህ በምንደርስበት ጊዜ፣ ወይም ፍርድ አለ ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ፣ ሰው ሁሉ ይደነግጣል። እንዲያውም ይህ ዕለት ከሁሉ የበለጠ ሊያስደስተንና ልንጓጓለት የሚገባ ዕለት ነው። ለምን? ይኼ አድለዊ ዓለም የሚያልፍበት ነውና። ለምን? የታዘዝነውን ከፈጸምን ወደማያልፍ ክብር የምንሸጋገርበት ነውና። ስለዚህ የሚያስደስት ነው። ንስሐ ስለ አልገባን ነው የምንፈራው፣ የምንርበተበተው። ጌታ እንደሆን ያልነገረን ነገር የለም። «ተጠንቀቃችሁ ኑሩ የምመጣበትን ጊዜ አታውቁምና፣ ስለዚህ ሁል ጊዜ ዝግጁ ሆናችሁ ኑሩ» ብሎአል።

ለዕብደት ብቻ የተዘጋጀ ጊዜ የለንም። ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የምትለዋ የማትቀር ናት። እግዚአብሔርም በአሁን ጊዜ ተደብቆ አይመጣም። በግልጥ እንደሚመጣ ተናግሯልና። የሚመጣውም ለአንድ ነገር ብቻ ነው። እኔና እናንተ በነበርንበት ዘመን የተሠራውን ለመቆጣጠር ነው። ያ የሠራነውን፣ የተሰጠነውን ጸጋ፣ ሥራ ላይ ማዋላችንን ለመቆጣጠር ለምን እኛ እንድንጠቀም ነው። ሌላ ነገር የለም።

ስለዚህ ይህን ቀን በታሪኩ አስፈሪ የመሆኑን ያህል ግዴታቸውን ለፈጸሙ ደግሞ የሚፈነድቁበት ቀን ነው። አዲስ ሙሉ ሕይወት፣ የተስተካከለ ሕይወት፤ ምስኪንና ኃላፊ ሆኖ ከመኖር ወደማያልፉበት ደረጃ የሚደረስበት ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ይህች ዕለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዕለት ናት። በከፍተኛ ፍርድ ቤት ሄዶ ከመደናገርና ከመደናገጥ እዚያ ሲሄዱ የሚያስፈልግውን ማስረጃ ይዞ መሄድ ያስፈልጋል። የተስተካከለ ማስረጃ ይዞ ከተሄደ፣ ፍርሐትና ድንጋጤ የለም።

ከእንግዲህ ወዲህ ግን ንስሐ የለም ማለት፣ ዕለቱ ከደረሰ በኋላ ንስሐ የለም ማለት ነው። ንስሐ የሚደረገው ዕለቱ ሳይደርስ እኛም በሕይወተ ሥጋ እያለን ነው። ከሕልፈተ ሥጋ በኋላ ንስሐ የለም፣ ፍርድን መቀበል ብቻ ነው።

ድሮ ሕፃናት ልጆች ነበር፤ በእጃችን አንጠልጥለው የሚያመጡን ነበርን፣ አሁን እኛ ደርሰን ሌሎችን አንጠልጥለን እንመጣለን፣ ሰውነታችንም ከጥንካሬ ወደ መድከሙ እየሄደ ነው። በአካላችን ደግሞ አዳዲስ ቆዳዎች እየመጡ ናቸው። ሁሉም ግን ወደዚያው ነው የሚደርሰው። ጠቅላላ ትምህርቱ የሚነገረው ሕዝብ በሥርዓት እንዲኖር አይደለም? ይኽ የፍርድ ቀን ስለ አለ ነው።

እንግዲህ በተሰጠን የማስተካከያ የተፈጥሮ ጸጋ ሁሉንም አሟልቶ መኖር ነው የሚያስፈልግው፤

በትንሽ ነገር ፈተና የምንገባ ከሆነ የትም አንደርስም። የሚታገስ ይድናል። እግዚአብሔር በቸርነቱ ይጉብኘን። ✣

# ሕገ እግዚአብሔር ይጠበቅ

ከአባ ገሪማ

የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊና

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ሊቀ ጳጳስ የቀረበ ትምህርታዊ መግለጫ



ሕግ፣ እውቀትና እውነት የሆነ አድርግ የሚል የተወሰነ ወሳኝ ሥርዓት ነው።

ከዚህም ጋር አታድርግ የሚለው ሕግ ሲሆን፣ አድርግ የሚለው ትእዛዝ መሆኑ ይታወቃል። (ዘጸ.፳፥፩–፲፯፣ ዘሌ.፲፱፥፲፰፣ ዘዳ፮፥፭–፱፣ ማቴ፳፪፥፴፭–፵፩)

እግዚአብሔር ዓለሙንና ሕዝቡን የሚያስተዳድረውም በዚሁ በሠራው ሕግ ነው። ይህም እንደ ሰው ሠራሽ ሕግ ጊዜ እየታየ የሚለወጥ፣ የሚለዋወጥ አይደለም፣ ሰማይንና ምድርን አሳልፎ የሚኖር ነው እንጂ።

ሕገ እግዚአብሔር የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ነው።

ዓለም ከተፈጠረ፣ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ሦስት ሕግጋት በቅደም ተከተል ተያይዘው የመጡ መሆናቸውን እናውቃለን። ይዞታቸውና አቋማቸውም በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቃሎና ተመዝግቦ ይገኛል።

እነዚህም ሦስት ሕግጋት የሚባሉት:-

፩ኛ. ሕገ አበው (ሕገ ልቡና)

፪ኛ. ሕገ ኦሪት

፫ኛ. ሕገ ወንጌል ናቸው።

## ፩ኛ. ሕገ አበው (ሕገ ልቡና)

ሕገ አበው የምንለው በኦሪት ዘፍጥረት ከምዕራፍ ፩–፶ ተመዝግቦ የሚገኘው ነው። ኦሪት ዘፍጥረት ስለ ዓለማት አፈጣጠር፣ ስለ ሰው ዘር አመጣጥ፣ ስለ ኃጢአትና የውድቀት ኑሮ አጀማመርና እግዚአብሔር ከሰው ጋር ስላለው ግንኙነት ይናገራል።

ኦሪት ዘፍጥርት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደብ ይችላል:-

ሀ. ከምዕራፍ ፩ እስከ ፲፩ ያለው ስለ ዓለም አፈጣጠርና ስለ ሰው ዘር ቅድመ ታሪክ ይናገራል። ይህም ማለት የአዳምና የሔዋን፣ የቃኤልና የአቤል፣ የኖኅና የጥፋት ውሀ እንዲሁም የሰናኦር ግንብ ፍርስራሽ ታሪክ የሚገኘው በዚሁ ክፍል ነው።

ለ. ከምዕራፍ ፲፪ እስከ ፶ ያለውም ክፍል ስለ ቤተ እስራኤል ቅድመ አበው ታሪክ ይናገራል። ከእነርሱም መካከል የመጀመሪያው በእምነቱና ለእግዚአብሔር በነበረው ታዛዥነት ታዋቂ የነበረው አብርሃም ነው።

ከዚህም ጋር የአብርሃም የወንድሙን የሐራን ልጅ የሎጥን ታሪክ እንመለከታለን።

ሎጥ በከለዳውያን ዑር ተወልዶ ከአጎቱ ከአብርሃም ጋር ወደ ከነአን የተጓዘና (ዘፍ.፲፩፥፳፯፣ ፲፪፥፭፣ ፲፫፥፩) በዚያን ጊዜ ለምለም በነበረው በዮርዳኖስ ሜዳ ለመኖር የመረጠ (ዘፍ.፲፫፥፭–፲፩) ከፋትና ኃጢአት በመላበት በሰዶም ከተማ የተቀመጠ (ቁ.፲፪–፲፫)፣ በሰዶማውያን ኃጢአት ብዛት ሰዶምን ለማጥፋት የመጡትን መላእክት በቤቱ ተቀብሎ ያስተናገደ (ዘፍ.፲፱፥፩–፲፩)፣ መላእክቱም እግዚአብሔር አብርሃምን በማሰቡ ሎጥን፣ ሚስቱንና ሴቶች ልጆቹን ከሰዶም አውጥተው ከጥፋት ያዳኗቸው መሆኑ፣ የሎጥ ሚስትም የተሰጣትን መመሪያ ባለመቀበል በጉዞ ላይ እያለች ወደኋላ በመመልከቷ የጨው ሐውልት ሁና መቅረቷ (ዘፍ.፲፰፥፳–፴፫፣ ፲፱፥፲፯–፳፱)፣ በዚሁ ድርጊት መነሻነት ከጊዜ በኋላ በዘመነ ሥጋዌ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሎጥንና የሚስቱን ታሪክ ለፍርድ ማስጠንቀቂያ በማድረግ ጠቅሶ ማስተማሩን (ሉቃ.፲፯፥፳፰–፴፫) እንዲሁም የሎጥ ታሪክ እግዚአብሔር ጻድቃንን ከመከራ የሚያድናቸው መሆኑን የሚያስተምረንን በጴጥሮስ ሁለተኛ መልእክት በምዕራፍ ሁለት ከቁጥር አምስት እስከ አሥር ካለው እንረዳለን። በይቀጥላልም የአብርሃም የልጁ የይስሐቅ፣ የልጅ ልጁ ያዕቆብና የ፲፪ቱ የያዕቆብ ልጆች ታሪክ ይከተላል። እነዚህም ፲፪ቱ የያዕቆብ ልጆች ፲፪ቱን የእሥራኤል ነገዶች የመሠረቱ ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ኦሪት ዘፍጥረት ስለ ቤተ እሥራኤል ታሪክ በበለጠ የሚናገር ቢሆንም ከሁሉ በላይ የሚተርከው ግን እግዚአብሔር ስላደረገው ሥራ ነው። እግዚአብሔር ዓለማትን የመፍጠሩን ታሪክ መናገር ይጀምርና እሱ ለሕዝቡ ማሰቡን እንደ ማያቋጥር የሚያመለክተውን ተስፋ በመግለፅ ይጨርሳል። በመጽሐፉ ከዳር እስከ ዳር ዋናው ባለታሪክ ስሕተት በሚፈጽሙት ላይ ፍርድንና ቅጣትን የሚሰጠው፣ ሕዝቡን የሚመራውና የሚታደገው፣ የታሪካቸውንም ሒደት የሚያስተካክለው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ይገልፃል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ የሆነው ኦሪት ዘፍጥረት የተጻፈበት ዋናው ምክንያት ሕግ ከመሠራቱ በፊት የነበረውን የሕዝቦችን የእምነት ታሪክ ለመመዝገብና ያም የእምነት ታሪክ ሕያው ሆኖ እንዲኖር ለማድረግ ነው።

## ፪ኛ. ሕገ ኦሪት

የሰው ልጅ በተፈጥሮ በተሰጠው ነፃ የኅሊና ፈቃድ በመመራት ፈጣሪውን አውቆ፣ ሕገ አበውን በማፍረስና በመጠበቅ ለብዙ ዘመናት ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር በደብረ ሲና በአምሳለ ንጉሥ ተገልጦ ለዕውቀቱ አጋዥ ረዳት ይሆነው ዘንድ ሕገ ኦሪትን ማለት ዐሠርቱ ቃላትን በገበታ ላይ ጽፎ ሰጠው። ከዚህ በኋላ ዓለም በተጻፈ ሕግ ኢየተመራ እግዚአብሔርን መከተል ጀመረ።

በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፳ እንደተገለጸው ለሙሴ የተሰጠው ሕግ በዘመነ መሳፍንት፣ በዘመነ ነገሥት፣ በዘመነ ካህናት እስከ ሕገ ወንጌል መሠራት ድረስ የሃይማኖት፣ የምግባር፣ የአስተዳደር መመሪያ ሆኖ ኖሯል፤ ይኖራል።

ኦሪት ዘሌዋውያንም የሚያትተው ስለ አምልኮተ እግዚአብሔር ደንቦችና ስለ ሥርዓተ ሃይማኖት፣ እንዲሁም ሥርዓቱን ስለሚፈጽሙ ካህናት ሲሆን በዚህ መጽሐፍ ያለው ማዕከላዊ ዋና ነጥብ የእግዚአብሔርን ቅድስና የሚያወሳው ክፍል ነው። ከዚህም ጋር ቤተ እስራኤል ቅዱስ ከሆነው ከእስራኤል አምላክ ጋር የቅርብ ግንኙነት ይኖራቸው ዘንድ በእንዴት ያለ ሁኔታ ማምለክ እንደሚገባቸው ይገልጻል። ከመጽሐፉ የታወቀው ትእዛዝ ሁለተኛ ታላቅ ትእዛዝ ተብሎ የተጠቀሰው በምዕራፍ ፲፱ በቁጥር ፲፰ ላይ የሚገኘው «ሰውን ሁሉ እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ የሚለው ነው»

በኦሪት ዘኍልቁም እስራኤላውያን የሲናን ተራራ ከለቀቁበት አንሥቶ እግዚአብሔር ሊሰጣቸው ቃል ወደገባላቸው የተስፋይቱ ሀገር ምሥራቃዊ ወሰን እስከተቃረቡ ድረስ ዐርባ ዘመን ያህል የነበረውን የጉዞ ታሪክ የሚያወሳ ሲሆን የዚህ መጽሐፍ ዋና ነጥብ የሕዝቡ ሁለት ጊዜ መቆጠር ነው። «በዚህም ረጅም ጉዞ ችግር ሲገጥማቸው የሚፈሩና ተስፋ የሚቆርጡ፣ በእግዚአብሔርና መሪያቸው ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር በመረጠው በሙሴ ላይ የሚያምፁ ሕዝቦች እንደ ነበሩ ተገልጿል። ምንም እንኳ እስራኤላውያን ደካሞችና እምቢተኞች ቢሆኑም እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን በመጠበቅ ይንከባከባቸው እንደ ነበር ታሪኩ ያስረዳል።

በኦሪት ዘዳግም የተገለጸውም ዋናው ፍሬ ነገር በምዕራፍ ፮ ከቁጥር ፬ እስከ ፱ ያለው ነው። ይኸውም:-

«እስራኤል ሆይ! ይህን አስታውስ እግዚአብሔር አምላካችን አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኃይልህ ውደድ፤ ዛሬ የምሰጥህን እነዚህን ትእዛዛት አትርሳ፤ እነዚህኑ ትእዛዛት ለልጆችህ አስትምራቸው፣ በቤት ስትቀመጥም ሆነ በመንገድ ስትሔድ፣ ዕረፍት በምታደርግበትም ሆነ ሥራ በምትሠራበት ጊዜ ሁሉ እነዚህን ትእዛዛት ዘወትር አሰላስል፤ ማስታወሻ ይሆኑልህ ዘንድ በክንድህና በእግርህ ላይ እሰራቸው፣ በቤትህ ደጃፍ መቃኖችና በቅጽር በሮችህ ላይ ጻፋቸው» የሚለው ነው።

ከዚህ በላይ እንደታተተው እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በተጻፈ ሕግ ለመምራት፣ ለማስተዳደርና ለመርዳት በመፈለጉ ሕገ ኦሪትን ሰጥቶታል።

በኦሪት ዘጸአት በምዕራፍ ሃያ ከቁጥር አንድ እስከ ዓሥራ ስምንት ድረስ የተዘረዘሩት ዓሠርቱ ቃላት:-

፩. ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ፣

፪. በሐሰት አትማል፣

፫. ነፍስ አትግደል፣

፬. አትስረቅ፣

፭. አታመንዝር፣

፮. የወንድምህን ገንዘብ አትመኝ፣

፯. በሐሰት አትመስክር፣

እነዚህ ሕግጋት ሲሆኑ ትእዛዛቱ ደግሞ:-

፰. የእግዚአብሔር አምላክህን ሰንበት አክብር፣

፱. እናትህንና አባትህን አክብር፣

፲. ወንድምህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ የሚሉት ሲሆኑ መጽሐፈ ኦሪት የሚሰጣቸው ዓይነተኞቹ የትምህርት መመሪያዎች እነዚህ ናቸው።

## ፫ኛ. ሕገ ወንጌል

ወንጌል የሚለው ቃል ከግሪክ ቋንቋ የመጣ ሲሆን ትርጉሙም የምሥራች ማለት ነው። ወንጌል፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ፣ በሥጋ እንደ ተወለደ፣ ስለ ሰዎች ኃጢአትም በሥጋ እንደ ሞተ፣ ከሞተ በኋላም ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ውሎና አድሮ እንደ ተነሣ፣ ከዚያም በተነሣ በአርባኛው ቀን ወደ ሰማይ ማረጉን ያስትምረናል።

በሕገ አበው፣ በሕገ ኦሪት፣ በሕገ ወንጌል በሦስቱም ሕግጋት እግዚአብሔር አምላክ አንድ ነው። በዚህ ምክንያት ስለ እግዚአብሔርነቱ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረውን ሁሉ በልባችን የምናምንበት፣ በአፋችን የምንታመንበት መግለጫ፣ ሃይማኖት ይባላል። ሃይማኖት ማለት በዓይን የማይታየውን በእጅ የማይዳሰሰውን፣ የልዑል እግዚአብሔርን ነገር ይህ እንዴት ይሆናል ማለት ሳይኖር በሙሉ ልብ ማመን፣ በአፍም፣ በመጻፍም መመስከር ነው።

ከዚህም ጋር ለሕገ ወንጌል መሠረት የሆኑትን ፮ቱን ቃላተ ወንጌል ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፭ ከቁጥር ፳፩ እስከ ፵፰ ያለው እንደሚከተለው ይቀርባል።

### ፮ቱ ቃላተ ወንጌል

፩. ለቀደሙት አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል። የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፣ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፣ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።

እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፣ በዚያም ወንድምህ አንዳች ባንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፣ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፣ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ፣ አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ፣ ዳኛም ለሎሌው፤ ወደ ወኅኒም ትጣላለህ፤ እውነት እልሃለሁ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም።

፪. አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ወደ ሴት ያየ ሁሉ፣ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከርሷ ጋር አመንዝሯል። ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ካንተ ጣላት። ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና። ቀኝ እጅህም ብታሰናክልህ ቆርጠህ ካንተ ጣላት ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንዱ ቢጠፋ ይሻላልና።

፫. ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ። እኔ ግን እላችኋለሁ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።

፬. ደግሞ ለቀደሙት በውሸት አትማል፣ ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ከቶ አትማሉ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፣ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና። በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፣ በራስህም አትማል አንዲቱን ጠጉር ነጭ፣ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና። ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይንም አይደለም አይደለም ይሁን፣ ከእነዚህም የወጣ ከክፉ ነው።

፭. ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፣ እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት። ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሔድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሒድ፣ ለሚለምንህ ስጥ፣ ካንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል።

፮. ባልንጀራህን ውደድ፣ ጠላትህን ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል፣ እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁንም መርቁ፤ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፤ ስለሚያሳድዱዋችሁ ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና። በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናሙን ያዘንማልና። የሚወዷችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለም። ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ። የሚል ነው።

ሕገ እግዚአብሔር ይጠበቅ በሚል መነሻ ስለ ሕግ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን በጥቂቱ ለማዘከር ሞክረናል።

ከዚህ በላይ ከተገለጹት ከእነዚህ ሦስት ሕግጋት ሌላ:-

፩. በብትኑ የሚነገር ሕገ ስብእ የሚባል አለ።

፪. ፍጡር ሁሉ አውቆና ተረድቶ የሚሠራው መውለድ፣ መዋለድ፣ በየጥቂቱ ማደግ፣ መራብ፣ መጠማት፣ መብላት፣ መጠጣትና የመሰለው ሁሉ ሕግ ባሕርያዊ ይባላል።

፫. ፍጡር የሆነው ሁሉ ልማዱን፣ ፈቃዱን ግዳጁን የሚፈጽምበት ሕገ ሥጋ ተብሎ በመጠራት የታወቀ ነው።

ከቡራን፣ ክቡራት ቃሉን ለመስማት በዚህ የተገኛችሁ፣ ሁላችንም ከሕግ በታች መሆናችንን ስለምናውቅ

www.ethiopianorthodox.org

ሕግ በሰው ላይ ሥልጣን የሚኖረው ሰው በሕይወት እስከ አለ ድረስ ብቻ መሆኑን ደኅና አድርገን እንረዳለን።

እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አየ። እነሆም እጅግ መልካም ሆነ። (ዘፍ.፩፥፴፩) ከሚለው የቅዱስ መጽሐፍ ቃል እንደምንረዳው አምላካችን እግዚአብሔር በስድስቱ ቀናት የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም ሲሆን በተለይም የሰው ልጅ በሥላሴ አርአያና አምሳል የተፈጠረ ንውድ፣ ክቡር ሁኖ ሳለ ትእዛዘ እግዚአብሔርን በማፍረሱ የሞት ሞት ተፈረደበት። አዳም ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ ከኤደን ገነት እንዲወጣ ተገደደ። (ዘፍ.፫:፳፫) ሕማም፣ ጻዕር፣ ገዓር ወደሚበዛበት ምድረ ፋይድ ከወረደ በኋላ ቀዳማዊ አዳም በስህተቱ ተጸጽቶ በማዘኑ፣ በማልቀሱና ንስሐ በመግባቱ ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ንስሐውን ተቀብሎ የማዳን የቃል ኪዳን ተስፋ ሰጠው። ይሁንና ይህ የቃል ኪዳን ተስፋ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመንን አስቆጥሯል።

ሰው ይህን የቃል ኪዳን ተስፋ ቢሰማም ክፉ ሥራውን አስፋፍቶ በመቀጠሉና የዕድሜ ብዛትም የኃጢአትን ስፋት በማስከተሉ አዳም አንድ ሺህ ዘመን ሳይመላው በዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ዕድሜው የሞትን ጽዋ ተቀብሎ ወደ መሬትነቱ ተመለሰ። (ዘፍ.፫፥፲፱፤ ፭፥፭)

ከዚህ አንፃር እግዚአብሔር «መንፈሴ በሰው ላይ ለዘለዓለም አይኖርም እርሱ ሥጋ ነውና ዘመናቱም አንድ መቶ ሃያ ዓመት ይሆናሉ» አለ። (ዘፍ.፮፥፫) በዚያ ዘመን ምድር በእግዚአብሔር ፊት ተበላሽታ ታየች፣ ሥጋን የለበሰም ሁሉ በምድር መንገዱን፣ ሕይወቱን አበላሽቶ ታይቶ ነበርና። ስለዚህ «እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፣ በልቡም አዘነ፣ እግዚአብሔር የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ፣ ከሰው እስከ እንስሳ፣ እስከ ተንቀሳቃሽም እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቻለሁና» አለ። (ዘፍ.፮፥፮-፰)።

ለደጋጎቹ አበው ለእነማቱሳላ ተሰጥቶ የነበረው የዘጠኝ መቶ ስድሳ ዘጠኝ ዓመት ዕድሜ እየቀነሰ በመምጣቱ ሰው ከአንድ መቶ ሃያ ዓመት የበለጠ ዕድሜ እንደማይኖረው እግዚአብሔር መናገሩን ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል። (ዘፍ.፮፥፫)

ይሁን እንጂ አሁንም የሰው ልጅ የኃጢአቱን ሥራ አብዝቶ በመቀጠሉ በዚያን ጊዜ ከነበረው ትውልድ መካከል በደግነቱና በጽድቅ ሥራው ጸንቶ የተገኘ አንድ ሰው ብቻ ነበር፣ ይኸውም ለአዳም ፲ኛ ለሴት ፱ኛ ሐረገ ትውልድ የሆነው ጻድቁ ኖኅ ነበር።

በዚህ ጻድቅ ሰው ዘመን ኃጢአትን አብዝተው የሠሩ ሰዎችን ለመቅጣት እግዚአብሔር አምላክ መድርን በጥፋት ውሀ ማጥለቅለቁ ይታወቃል። (ዘፍ.፮፥፱፤ ፯፥፲)

በዚያን ጊዜ ከሰው ወገን የዳነ ቢኖር ጻድቁ ኖኅ ከነቤተሰብኡ ብቻ ነበር።

በዚህ ጻድቅ ሰው ዘመን ኃጢአትን አብዝተው የሠሩ ሰዎችን ለመቅጣት እግዚአብሔር አምላክ ምድርን በጥፋት ውሀ ለመደምሰስ ባለማቋረጥ ዓርባ መዓልትና ዓርባ ሌሊት ሙሉ የጥፋት ውሀውን ካወረደ በኋላ ሁሉም ጠፉ። ከሞት የተረፉት ኖኅና ከእርሱ ጋር በመርከብ የተሣፈሩት ብቻ ነበሩ። ያም የጥፋት ውሀ እስከ አንድ መቶ ሐምሳ ቀን ድረስ አልጎደለም ነበር። በመጨረሻው ጊዜ ጻድቁ ኖኅ የውሀውን መጉደልና አለመጉደል አይታ እንድትመጣ በመርከብ ከእርሱ ጋር ከሚገኙት በራሪዎች መካከል ርግብን ቢልካት ሔዳ የውሀውን መጉደል አይታ ወደ እርሱ በተመለሰች ጊዜ በአፏ ለምልማ የወይራ ቀምበጥ ይዛ በመምጣቷ «ሐፀ ማየ አይኅ፣ ነትገ ማየ አይኅ» በማለት ውሀው ፈጽሞ ጎደለ በማለት አብስራው ነበር። (ዘፍ.፯ ና ፰)

ከዚህም ጋር ስለ ሰዶምና ገሞራ መጥፎ የታሪክ ገጽታ ቀደም ሲል ለመናገር ሞክረናል።

ሰዶምና ገሞራ በዮርዳኖስ ሸለቆ አካባቢ የተቆረቆሩ አስማተ አህጉርና የኃጢአተኞች መናኸሪያ ከተማዎች በመሆናቸው በእነዚህም ከተማዎች የነበሩት ነውረኞች ወንድነታቸውን ክደው አጸያፊ የዝሙት ሥራ በመፈጸማቸው (ዘፍ.፲፫፥፲፤ ፲፬፥፩-፲፬) እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ወሰነ። (ዘፍ.፲፰፥፳፤ ፲፱፥፳:፱) ሁለት መላእክትም ሎጥን ከነቤተሰብኡ ከእነዚህ ከተሞች ካወጡ በኋላ እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን በእሳትና በዲን አጠፋ። (ዘፍ.፲፱፥፲-፳፮)

ሰዎች እግዚአብሔርን መፍራትና ማምለክ ሲተውና የዚህ ዓይነቱ አጸያፊ የዝሙት ሥራ ኃጢአትን የፈጸሙና የሚፈጽሙ ሁሉ በሙሴ ሕግ ያለምሕረት ይገደሉ እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። (ዘሌ.፳፥፲፫፤ ዘዳ.፳፫፥፲፯)

ሰዶምና ገሞራ አሁን በጨው ባሕር የተሸፈኑ የሎጥ ባሕርና ሙት ባሕር በመባል የታወቁ ናቸው።

በዚያ የመጥፎ ታሪክ መነሻነት ሰዶምና ገሞራ የክፋት ሁሉ ምሳሌ በመሆን ትምህርት የሚሰጥባቸው ሁነዋል። (ኢሳ.፩፥፱-፲፤ ሰቆ.፬፥፮፤ ሕዝ.፲፮፥፵፮፤ ማቴ.፲፥፲፭፤ ፲፩፥፳፫ ራእ.፲፩፥፰)

(ይቀጥላል)



# ትምህርተ ሃይማኖት

## ከሆሣዕና እስከ ትንሣኤ

የብፅር ቅኝት መምህር ዕንቁባሕርይ ተከሥተ

የኔታ ገብረ ሥላሴ ከዚህ በፊት ባቀረቡዋቸው የትምህርት ርእሶች በአጠቃላይ ስለ ሀልዎትና ባሕርየ እግዚአብሔር የገለጹበትን መሠረታዊ ትምህርት ለአንባብያን አቅርበናል። በዛሬ ዝግጅታችን ደግሞ ሆሣዕና ማለት ምን ማለት ነው? ዕለቱን በየዓመቱ እናከብረዋለን፣ ምን የተደረገበት ነው። የሰሙነ ሕማማት ምሥጢር ምንድነው? በጸሎተ ሐሙስ የተፈጸመው ሥርዓትስ፣

የዕለተ ዓርብ ታምራትና ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ስለሚባለው፣ ጌታ በመቃብር ስለቆየበት የሰዓት አቆጣጠር፣ እንዲሁም ጌታ «ወይቤ ተፈጸመ ኵሉ» ያለበት ምክንያት ምንድነው?

ቅዳሜ ሥዑር የተባለበት ምክንያትስ ዋና ትርጉሙ ምን ይመስላል? ትንሣኤ ክርስቶስና ትንቢቱ፣ የሚሉና የመሳሰሉ ነጥቦችን፣ ምሥጢሩ ተቀድቶ በማያልቀው ዕውቀታቸው በሰፊው አትተው አቅርበውልናል። እንደ ነዚህ ከመሰሉ ዓይነተኛ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ተከታትሎ መማርና ማወቅ ትልቅ ጸጋ ወይም ሀብት ነው። በዚህም መሠረት ከእኛ የሚጠበቀው ከሊቁ የተገኘውን ጥበብ በጥንቃቄ ማቅረብ ሲሆን ከአንባቢው የሚጠበቀው ደግሞ ጽሑፉን በጥንቃቄ አንብቦ ማወቅና መረዳት ነው።

### ሆሣዕና

ሆሣዕና ማለት መድኃኒት ማለት ነው። «ሆሣዕና በአርያም» በሰማይ በምድር ያለ መድኃኒት።

«አልቦ ካልዕ ስም ዘይትታወሀብ ለዕጓለ እመሕያው ዘእንበለ ስሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ» «መዳንም በሌላ በማንም የለም፣ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» ብሎ ሉቃስ በግብረ ሐዋርያት ገልጦታል። የሐዋ. ሥራ.፬፥፲፪። በሰማይ በምድር ሌላ ድኅነት የሚሰጥ የለም።

የትንቢቱን ለመፈጸም፣ «ነዋ ንጉሥኪ ይመጽእ እንዘ ይጼዕን ዲበ እድገት፣ ወዲበ ዕዋላ»

«እነሆ፣ ንጉስሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያም፣ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይምጣል» ብሎ ዘካርያስ ወልደ ሐዶ ከደቂቀ ነቢያት አንዱ ተናግሯል። (ዘካ.ምዕ.፱ ቁ.፱፤ ማቴ.፳፩፥፩-፲፩)።

ነቢዩ ኢሳይያስ ደግሞ በልዋ ለወለተ ጽዮን ነዋ ንጉሥኪ ይመጽእ፣ ዘይጼዕን ዲበ እድገት ወዲበ ዕዋለ እድግ «ለጽዮን ልጅ እነሆ ንጉስሽ በአህያይቱና በውርንጫይቱ ላይ ተጭኖ ይመጣል በሏት። (ኢሳ.፲፪፥፮)።

ዘካርያስና ኢሳይያስ የተናገሩትን ትንቢት ለመፈጸም በአህያ ተቀምጦ መጣ። እናቲቱ ቀንበር መጫን የለመደች ናት። የእስራኤል ምሳሌ፣ ሠረገላ ቀንበር መጫን የለመደች እንደሆነች፤ እስራኤልም ሕግ መጠበቅ የለመዱ ናቸውና።

ዕዋል (ውርጫይቱ) የአሕዛብ ምሳሌ፣ መጫን ያልለመደች እንደ ሆነች፣ ለሕዝብም ሕግን መጠበቅ ያልለመዱ ናቸውና።

አንድም እድገት (እናቲቱ የኦሪት ምሳሌ፤

ዕዋል (ግልገልዋ) የወንጌል ምሳሌ

ስለዚህ ትንቢቱን ለመፈጸም በአህያ እና በግልገልዋ ተጭኖ መጣ።

ከቤተ መቅደስ እስከቢታንያ ፲፩ ምዕራፍ ነው በእድገት ሆኖ ከዚያ ወርዶ በዕዋል (በግልገልዋ) ሦስት ጊዜ ቤተ መቅደሱን ዞሮ በቤተ እግዚአብሔር ገብቷል። በበለጠ (የማቴዎስ ወንጌል ምዕ.፳፩ አንድምታውን ተመልከት)

«ወበልዋ ለወለተ ጽዮን» ለጽዮን ልጅ ንገሯት የተባለች ቤተ እስራኤል ናት። የባሕርይ አምላክ ክርስቶስ መጥቷልና የነገራችሁን ስሙ ማለት ነው።

በዚሁ ዕለት ቅዱስ ያሬድ በሠራው መዝሙር «ወእንዘ ስሙን በዓለ ፋሲካ ቀርቦ አርዳኢሁ ለአምላክ ጽድቅ ኀበ ደብረ ዘይት ሙራደ ዓቀብ ሀገረ እግዚአብሔር»

በዚያ በዓለ ፋሲካ ሰሞን በደብረ ዘይት በአቀበቱ መውረጃ አጠገብ በእግዚአብሔር ሀገር የእውነተኛ አምላክ ደቀ መዘሙርት ቀረቡ ብሎ ይናገራል። በሌላ መልኩ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ የገባበት ዕለት ተብሎ ነው የሚነገረው፣ ይህ ሁሉ ትንቢትን ለመፈጸም የተነገረ ነው።



www.ethiopianorthodox.org



## የሆሣዕና ሥርዓት

የሆሣዕና ሥርዓት አከባበር ከመቼ ጀምሮ ነው ቢባል ከመጀመሪያው ጳጳስ ከአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ጀምሮ ነው።

በዚህ ጊዜ (ዕለት) ሊቃውንቱ ማኅሌተ እግዚአብሔር ቆመው አድረው፤ ከቅዳሴ በፊት «ወበልዎ ለወለተ ጽዮን» «ለጽዮን ልጅ ንገሯት» እያሉ ቤተ መቅደሱን ወይም ቤተ ክርስቲያኑን የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው በመዞር፣ ሥርዓቱ ዑደቱን ይፈጽማሉ። ምስባክ ይሰበካል፣ ወንጌል የአራቱ ወንጌላውያን ለዕለቱ ተስማሚ የሆነ ከየምዕራፉ ይነበባል። ይህም ምሳሌ አለው። አብርሃም ይስሐቅን በወለደ ጊዜ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዞ አመስግነዋልና ያንን ለመፈጸም ነው።

ስሌን እሳት አይበላውም ለብልቦ ይተወዋል፤ ክርስቲያኖቹም ባሕርይህ አይመረመርም ሲሉ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው በየዓመቱ «ሆሣዕና በአርያም» እያሉ ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ።

### በዚህ ዕለት ለምን ልዩ ጸሎተ ፍትሐት ይፈጸማል?

በዚህ ዕለት ጸሎተ ፍትሐት የሚፈጸመው በሰሙነ ሕማማት በሚገኙ ዕለታት ለሙታን፤ ፍትሐት ስለማይደረግ ነው። ካሣ የተፈጸመው ጌታ ተሰቅሎ ነፍሳትን ከሲኦል ነጻ ካወጣ በኋላ ስለሆነ ከዚያ በፊት ካሣ አልተፈጸመምና። ይኸውም በሰሙነ ሕማማት ለሙታን ፍትሐት እንዳይደረግ ካልዕ ሰላማ በግብረ ሕማም መጽሐፍ ስለአዘዘ፤ በዚህ ምክንያት የሆሣዕና ዕለት ጸሎተ ፍትሐት ይፈጸማል፤ እንጂ ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ለሞተ ሰው ጸሎተ ፍትሐት አይደረግለትም። በሆሣዕና ዕለት የሚደረገው ጸሎተ ፍትሐት ለዚህ ተብሎ ነው።

አሁን ያለነው ድርጊቱ (ካሣ) ከተፈጸመ የዛሬ ፲፱፻፷ ዓመት ነው። ይህ ዛሬ እንዴት እንደ አዲስ አድርጎ ሊፈጸም ይችላል? የሚል ካለ ያማ ጌታ የሠራውን ሥራ ሁሉ እስከ ዓለም ፍጻሜ ሥሩ ተብሎ የለ? ሥሩ ማለት እናንተ ስታልፉ (ስትሞቱ) ልጆቻችሁ ይስሩ ማለትኮ ነው።

### በሰሙነ ሕማማት ለምን መስቀል እንሳለምም?

### ሰላምታንስ ለምን እንለዋወጥም?

በሰሙነ ሕማማት መስቀል የማንሳለምበት ዋና ምክንያት ገና ጌታ ተሰቅሎ ካሳ አልተፈጸመም፣ ነፍሳት ከሲኦል አልወጡም ነበር ለማለት ነው። ዓርብ በሠርክ ነው የወጡ ለማለት ያንን ለማስታወስ መስቀል አንሳለምም። ካሣ ከመፈጸሙ መስቀል የድኅነት (የመዳን) ዓርማ (ምልክት) አልነበረምና ያንን ለማስታወስ ነው።

ሰላምም የማንባባልበት ምክንያት አይሁድ ጌታን ለመስቀል ሰኞና ማክሰኞ መከሩ፤ አልሆነላቸውም። ምክራቸው የተፈጸመው ረቡዕ ነው። ሉቃስ «ወአስተ ሐለፉ ነገረ» ብሎ ያነበዋል።

ስለዚህ እያንሾካሾኩ «እንስቀለው» «እንግደለው» ብለው ይማከሩ ነበር። ያንን ለማስታወስ ሰላምታ አንለዋወጥም፤ መስቀልም አንሳለምም። ባጭሩ ሳምንቱ የክፋት ምክር የተመከረበት እንጂ ሰላም የታየበት ሳምንት ባለመሆኑ ነው።

### ዕለተ ረቡዕ

ከሆሣዕና በአራተኛው ቀን የሚገኘው ዕለተ ረቡዕ የጌታ ምክረ ሞቱ የተፈጸመበት፤ የአስቆሮቱ ይሁዳ በ፴ ብር ጌታን ለማስያዝ ከሊቃነ ካህናቱ ጋር የተስማማበት ዕለት ነው። (ማር.፲፬ ቁጥር ፩፪፤ ማቴ.፳፮ ቁጥር ፩፱፤ ፳፯:፫፤ ሉቃ.፲፩፥፩፯)።

### ጸሎተ ኀሙስ

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚሁ ዕለት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙንም ለሐዋርያት የሰጠበት ዕለት ነው።

የአይሁድ ፋሲካ የነበረው ሐሙስ ነው። ከአይሁድ ጋራ በበዓል በጾም እንዳንገናኝ በኒቅያ ጉባኤ በድሜጥሮስ ቀመር እንዲሁም የአውሻኽር ሰዎች በአውሻህር፤ በባሕረ ሐሳብ በዚሁ ሁሉ ወስነውታል። «እመበ ዘይጸውም ጾሞሙ ለአይሁድ፤ ወያከብር በዓሎሙ ለአይሁድ ይሰድድ እምክርስቲያን»

«የአይሁድ ጾማቸውን የሚጾም፤ በዓላቸውንም የሚያከብር ካለ? ከክርስቲያንነት ይወገድ (ይባረር) ብሏል ሰለስቱ ምዕት በሃይማኖተ አበው።

በዚሁ ዕለት በማቴዎስ ወንጌል ምዕ.፳፮ ቁጥር ፳፮ እንደ ተገለጸው ጌታ ክቡር ሥጋውንና ደሙን ለሐዋርያት ሰጥቷል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ቁርባን የሚለው በዕለቱ ተለውጧል ወይ? ወይስ አልተለወጠም? በሌላ በኩል ጌታችን ለሐዋርያት የሰጣቸው «ሥጋዬ» ብሎ ሲሆን ይህ አማናዊ ነው ወይ? እንዴት ከመሰቀሉ በፊት «ሥጋዬ» ብሎ ሊሰጣቸው ቻለ? የሚሉ እንዳሉ ጥያቄ ሰምቼአለሁ።

መልሱ ግልጽና አጭር ነው። ይኸውም አማናዊ ነው። ነገ በቀራንዮ የሚሰቀል «ዝውእቱ ሥጋየ፤ ወዝውእቱ ደምየ» «ነገ በመስቀል የሚሰቀል ሥጋየ ይህ ነው፤ ነገ ኵናተ ሐራዊ የሚያፈሰው ደሜ ይህ ነው» ብሎ አክብሮ፤ ለውጦ፤ ትኩስ ሥጋ፤ ትኩስ ደም አድርጎ ሰጣቸው። ስለፈሩ «ጥዒም አጥዓሞሙ» አይዟችሁ አትፍሩ ብሎ ቀምሶ ሰጣቸው።

ጌታ ሳይቀበል አቀበሎአቸው ቢሆን ኖሮ፤ ዛሬ የሚቀድሰው ካህን አቀብየ ሳልቀበል ልውጣ ባለ ነበርና፤ ተቀብሎ ያቀብል ለማለት ለአብነት፤ የሠራው ሁሉ ለእኛ ነው።

«እስመ አልቦ ነገር ዘይሰዓኖ ለእግዚአብሔር» ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም። «እግዚአብሔር ይህ ሥጋየ» ነው ሲል ውሸት ነው አይባልም። የተናገረውን ሁሉ ማመን አለብን፤ ጥያቄው ሳይሰቀል ለምን ሥጋ ነው አለ ነው፤ ነገር ግን ነገ የሚሰቀለው ሥጋዬ ይህ ነው ሲል ተለውጦ ሥጋየ ወልደ እግዚአብሔር ሆነ ማለቱ እንደሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል። ያ የዕለተ ሐሙስም ሆነ ዛሬ ካህናት የሚያቀርቡት መሥዋዕት አማናዊ ሥጋውና ደሙ ነው።

ጠያቂዎቹ እንደምሳሌ አድርገው የሚያቀርቡት ጌታ ከመሰቀሉ በፊት ሥጋውና ደሙ ተበልቷል ወይስ አልተበላም እንዴት ጌታ ባይሰቀል ሥጋው ተበላ የሚል ጥያቄ ነው።

መልሱ፤ ነገ የሚሰቀለው ሥጋየ ይኸ ነው፤ ነገ የሚፈሰው ደሜ ይኸ ነው ሲል ቃሉ ለወጠው፤ ሥጋና ደሙ አደረገው። እኛ አምነን እንቀበላለን እንጂ አይደለም አይባልም። እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ አምነን መቀበል አለብን። እሱ ይህ ሥጋየ ነው ይህ ደሜ ነው እያለ አይደለም የሚል ካለ ሐሰተኛ ይሆናል። «እስመ አልቦ ነገር ዘይሰኖ ለእግዚአብሐር» እሩቅ ብእሲ ቢሆን ኖሮ አይሆንም ይባል ነበር። እግዚአብሔር ግን ያለው ሁሉ ይሆናል።

ከዚህ ጋር ተያይዞም በዕለተ ሐሙስ ሐዋርያት የታጠቡት ኅፅበት ስለ ትሕትና ወይስ ስለ ጥምቀት የሚል ጥያቄ አለ፤ ይህም:-

ሐዋርያት የታጠቡት ጥምቀት ነው። «እመ ኢሐፀብኩከ እገሪከ አልብከ ክፍል ምሳሌየ» ካላጠብኩህ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም» ሲል መልሶለታል። (ዮሐ.፲፫፥፯) ዕድል ፈንታ የለህም» ማለት ልጅነት አታገኝም ማለት ነው።

ጥምቀት እንዳንል ካሣ አልተፈጸመም የሚል ሐሳብ ካለ አስቀድሞ አጥቦ ወዲያው ሥጋና ደሙን ሰጣቸው። ዛሬ መጀመሪያ ሕፃኑን እናጠምቀዋለን፤ ኋላ ሜሮን ተቀብቶ ሥጋውና ደሙን ይቀበላል። ይኸ «ተሰዕሎተ ቢንያም» የሚባል ጥሩ አድርጎ ጽፎታል። ስለዚህ ሐዋርያት መቼ ተጠመቁ ቢባል በሕጽበተ እግር ጊዜ ነው። ይህም «እልብከ ክክፍል» «ዕድል ፈንታ የለህም» ባለው ይታወቃል።

ለጊዜው ሐዋርያት ዕግራቸው ብቻ እንደታጠቡ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ግማሹ አካላቸው ታጥበውስ እንዴት ጥምቀት ሆኖ ሊቆጠር ቻለ? ቢሉ? ያማ «ዘይውህጥ ርዕሶ» ብለው ሠለስቱ ምዕት የሕፃኑን ራስ በሚውጥ ባሕር ብቅ ጥልቅ ብቅ ጥልቅ አድርጉ ብለው በጥልቅ ባሕር፤ በማዕከላዊ ባሕር፤ በንዑስ ባሕር የተጠመቀ እንደ ሆነ ነው ብለው ጽፈው የለ። «ዘይውህጥ ርዕሶ» የሚጠመቀውን ሰው በፈሳሽ ወንዝ ብቅ ጥልቅ ብቅ ጥልቅ አድርገህ ታወጣዋለህ። ጴጥሮስ መላ አካላቴን እጠበኝ ባለበት ሰዓት ጌታ አይፈቀድልህም ያለው ይህ ለምንድነው ቢባል? እግሩን የታጠበ ሰው ሌላው ሊታጠብ አይፈልግም። አንዱ የሰውነት አካልህ ካጠብኩህ መላ ልጅነት ይሰጥሃል። ማለት ነውና በትልቁ ባሕር፤ በትንሹ ባሕር፤ በጳጳስ ቢጠመቁ አንድ ነው። «አሐቲ ጥምቀት» «አንዲት ጥምቀት (ኤፌ.፬፥፩)።

አንዳንዶም ሐዋርያት የተጠመቁት በውሃ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ነው የሚሉ አሉ። ለዚህም እንደ ማስረጃ የሚጠቀሱት መጥምቁ ዮሐንስ በማቴዎስ ወንጌል የንስሐ ጥምቀት በሚያጠምቁበት ጊዜ «እኔ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳት ያጠምቃችኋል» (ማቴ.፫፥፲፩)። ያለውን ይጠቅሳሉ።

ለዚህ መልስ የሚሰጠን በግብረ ሐዋርያት ጴጥሮስ ሲናገር «ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ የሚለው ነው። (የሐዋ.፪፥፴፰)

ሐዋርያት ሲያጠምቁ ቋንቋ ይገለጽላቸው ነበር መንፈስ ቅዱስ ያድርባቸው ስለ ነበር ተጠቀሰ እንጂ የሐዋርያትን መጠመቅ አያስመለክትም። ከዚሁ ባለተለየ መልኩ አብሮ የሚታየው አሪት አለፈች፤ ወንጌል ተተካች የሚባለው መቼ ነው ቢሉ፤ ከልደቱ እስከ ጥምቀቱ፤ ከጥምቀቱ እስከ ዕለተ ሐሙስ: ከዕለተ ሐሙስ እስከ ትንሣኤ ባለው ሰዓት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሲያስተምር እሷን ወደ ወንጌል እየሳበ ቆይቷል። መስዋዕትዋን የሻረው በዕለተ ሐሙስ ነው። በግ ይሰዋ ነበር፤ ቀርቷል መስዋዕትዋን አስለፈለፈው፤ የበሉትን ምግብ ከሆዳቸው በግብር አምላካዊ አጥፍቶ አማናዊ

www.ethiopianorthodox.org

ሥጋውን አማናዊ ደሙን ሰጣቸው። ሌላውን በየስፍራው ሲያስትምር አሳልፎታል።

ዐሠርቱ ቃላት ብቻ አላለፉም። ሌሎች ሥርዓቶች ግን አልፈዋል።

የወንድምን ሚስት ማግባት ቀርቷል፤ የበግ፤ የላም፤ የዋኖስ የዕጉሉ ግብ፤ መስዋዕትና ይህን የመሰለ ሁሉ ቀርቷል።

አንዳንድ ሰዎች ኦሪት ለምን አለፈች ይባላል? «ጌታ በወንጌል» ኢመጻእኩ እስዓሮሙ ለኦሪት ወለነቢያት አላ ከመእፈጽሞሙ» «ኦሪትንና ነቢያትን ሊሽራቸው አልመጣሁም፤ ልፈጽማቸው እንጂ» ብሎአልና አላለፈችም የሚሉ አሉ። ኢመጻእኩ ከመ እስዓሮሙ ለኦሪት ወለነቢያት ማለት፤

ኦሪት፤ ነቢያት የተናገሩትን ላስቀር አልመጣሁም፤ ይወርዳል ይወለዳል፤ ብለው የተናገሩትን ሁሉ ልፈጽም ነው የመጣሁ፤ ማለት እንጂ ኦሪት አላለፈችም ለማለት አይደለም።

«የውጣ» የተባለው ዐሠርቱ ቃላት ነው። ይኸውም እነሱ አልተሻሩም።

ኦሪት አለፈች የሚያሰኘው በግ፤ ላም መሠዋት፤ የወንድም ሚስት ማግባት፤ እጃቸው እስኪላጥ መታጠብ፤ ይህን የመሳሰለ ሁሉ አልፏል። ከአሥሩ ቃላት በቀር ሁሉም አልፏል። ዐሠርቱ ቃላት ግን በወንጌለ እንኳንስ ነፍስ መግደል፤ ወንድሙን የሰደበ ይፈረድበታል። ሲል ፈጽሞ እያበለጠው ሄደ፤ ኢትዘሙ ያለውን» ኢትሐውር ኀበ ብእሲት «ኢትዘሙ» ያለው «ኵሉ ዘርእያ ለብእሲት ወፈትዎ ዘመወ»

«ሴትን አይቶ የተመኛት አመነዘረ» ብሏል፤

እንኳንስ ከወንድ ሚስት መድረስ አይቶ የተመኘ በደለ፤ በማለት የኦሪትን ሥርዓት እየፈጸመው ሄደ፤

«አንሰ እብለከሙ፤ አንሰ እብለክሙ እያለ የተናገረው ሁሉ አሳለፈው ፈጸመው ማለት ነው።

## በዓለ ፋሲካ

በብሉይ የነበረ በግ ምሳሌ በብሉይ ኪ.ደን በጉ ዓመት የሆነው፤ ቀንዱ ያልከረከረ፤ ጥፍሩ ያልዘረዘረ፤ ዓመት የሞላው ጠቦት አይታችሁ ከ፲ እስከ ፲፬ ቀን በመዓልቱ በሁለት እጅ ብርሃን፤ ከሌሊቱ በአንድ እጅ ጨለማ ሰዉት ስትሰውትም ሰባት፤ አሥር፤ አሥራ ሁለት ሆናችሁ ሰውት ብሎአቸዋል።

በጉ ቀንዱ ያልከረከረ፤ ጥፍሩ ያልዘረዘረ መሆኑ፤ ጌታም ምክንያተ ኃጢአት የለበትምና ነው። ደሙን ስትቀቡት «ወሶበ ርእየ መልአከ ሞት ደመ በግዕ ለበወ ሞተ እግዚእ ፈርሐ ወኢቀርበ እንዲል «ይኸ የክርስቶስ ምሳሌ ነው ሲለው ነው፤ አባር ቸነፈሩ ከእስራኤል ቤት እንዳይገባ ይሆናል። ደመ በግውን ያየ መልአከ ሞትም እስራኤልን እያለፋቸው መሄድ ጀመረ። የግብጻውያን በኩር፤ በኩር ይገድላል። ያ የክርስቶስ ምሳሌ በመሆኑ የደመ በግው የደም ምልክት ያለው ቤት ሞት አይገባውም። በደመ ክርስቶስ የተዋጀ፤ በደመ ክርስቶስ መዳኑን ያመነ ሰውም ሞተ ነፍስ አያገኘውም። ላቱ እስከ ምጽአት የሚነሱ መምህራን፤ ጸጉሩ የመንፈስ ቅዱስ፤ ስለ ሀብቱ ብዛት፤ ቀንዱ የሥልጣነ እግዚአብሔር፤ ዓይኖቹ የነቢያት መሳሌናቸው።

በዚህ ዕለት በተለይ በምዕመናን የሚፈጸም ሌላ ድርጊት አለ። ይኸውም ዳቦ ይጋገራል፤ ንፍሮ ይነፈራል፤ ይኸ ልማደ ሀገር ቢሆንም የተቻለው ዓርብንና ቅዳሜን ያከፍል፤ ያልተቻለ ቅዳሜን ብቻ ያከፍል ብሏልና። ለአከፍሉት የሚስማማን ምግብ የሚጾም ሰው እንዳይደክም «ጉልባንን» አብዝቶ ይበላል።

ጾሙን የጀመረው «ያዕቆብ እኁኁ ለእግዚእነ» (የጌታ ወንድም ያዕቆብ) ነው። ይኸውም የጌታ ትንሣኤን ሳላይ አልበላም በማለት ጀምሮታል። ጌታ ከተቀበረ በኋላ ሐዋርያት እህል እንብላ አሉ። «የዕቆብ «በሦስት ቀን እነሳለሁ» ብሏል አይሆንም ቢላቸው እንግዲያስ እኛም እንጹም ብለው ጹመዋል። እኛም ያንን ይዘን እንጾማለን።

## ዕለተ ዓርብ

ክርስቶስ የተሰቀለበት ዕለት ዕለተ ዓርብ ይባላል። ይህ ዕለት ክርስቶስ ከተሰቀለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በክርስቲያኖች ዘንድ በጾምና በስግደት በየዓመቱ ይከበራል።

በመጀመሪያ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ የተሰቀለው ትንቢቱን ለመፈጸም ነው። ሙሴ «ስቅለተ ትሬእያ እስራኤል ለሕይወትከ ቅድመ አዕይንቲከ ወኢትትአመና»

«እስራኤል ሆይ ሕይወትህ (ክርስቶስ) በዓይኖችህ ፊት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ታየዋለህ። ግን አታምነውም።» (ዘዳግ.፳፰)።

ታላቁ ነቢይ «ኢሳይያስም መጽአ ከመ በግዕ ይጠባሕ ወከመ በግዕ ዘኢ.ይነብብ በቅድመ ዘይቀርጾ ከማሁ ኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ በቅድመ እለ ይረግዝዎ፤ ወበ ኃጢአተ ሕዝብየ በጽሐ እስከ ለሞት»፤ ነሥአ ደዌነ ወጾረ ሕማመነ»፤ አኮ በመልአክ ወአኮ በተንባል አላ ለሊሁ እግዚእ መጽአ ወአድኀነነ» ተብሎ በሰፊው ተናግሯል። ጥቅሶቹ ብዙ ናቸው።

ነቢዩ ዳዊትም «አገቱኒ ከለባት ብዙኃን፤ ወአዙኒ ማኅበሮሙ ለእኩያን» ቀነውኒ እደውየ ወእገርየ ወኖለቁ ኵሎ አዕጽምትየ» እንዳለው፤ ፮ ሺህ ፭፻፰፮ ጊዜ በገረፉት ጊዜ አጥንቱ ተቆጥሮዋል» ይኸ አስቀድሞ ቅዱስ ዳዊት የተናገረው ነው። ፮ ሺህ ፭፻፰፮ ጊዜ ለመገረፉ ግብረ ሕማማት ይገልጻል።

ክርስቶስ ለምን ሞቱ በመስቀል ሆነ? ከመስቀል በሌላ ማዳን አይችልም ነበር ወይ? ቢባል በዘመኑ የነበረው የበደለኛ አገዳደል ሥርዓት እንደ የሀገሩ ሁኔታ የተለያየ ነበር።

ለምሳሌ የሮማውያን ሥርዓታቸው መስቀል ነው።

የአይሁድ «ውግረተ ዕብን» ነበር።

የባቢሎናውያን እሳተ አንድዶ እዚያ መክተት ነው።

የፋርስ ለአንበሳ መጣል ነው።

ጌታም በሮማውያን ሥርዓት ተሰቅሎ ሞተ፤ ለዚህም ራሱ ጌታ ሞቱ በመስቀል እንደሚሆን አስቀድሞ ተናግሯል። (ዮሐ.፲፪፥፲፬)

ባይሰቀል፤ ጐኑ ባይወጋ ማይ ለሕጽበት፤ ደም ለጥምቀት ባልተገኘ ነበር። ብለው መምህራን ተርጉመዋል።

አይ፤ በውግረትም ደሙን አይታጣም ብለው ትንቢትን ለመፈጸም ተሰቀለ ብሎ አስታርቀውታል። እንጂ የአይሁድ ሥርዓት በድንጋይ ወግሮ መግደል ነው። ጌታ የተሰቀለው በሮማውያን ሥርዓት ነው።

«ኵሉ ሰቀል ዲበ ዕፀመስቀል ርጉም ውእቱ» ሠርቆ ቀምቶ የተሰቀለ ሰው የተረገመ ነው ትላለች ኦሪት።

ቅዱስ ጳውሎስም ወፀረ መርግማ ለኦሪት አለ።

ርጉም ተብሎ የአዳምን መርገም ለማጥፋት በአዳም የተፈረደው ሁሉ ተቀብሎ አዳምን ከመርገመ ነፍስ አዳነው። «ወሠዓረ መርገመ እምኔነ» ከእኛ መርገመ ኃጢአትን ደመሰሰ፤ አጠፋ» ያለው ስለዚህ ነው። ዛሬ ክርስቶስ ከተሰቀለ፤ ልጅነት ከተመለሰ ወዲህ ወደ ሲኦል መውረድ ቀርቷል። ይህም ዮሐንስ አፈወርቅ ገልጦታል። «እንከስ ኢንወርድ ታሕተ አላ ፈድፋደ ንተልዎ ለዘፈጠረነ ወንበውእ ኀበ ቦአ ሐዋርያነ ህየ ንበውእ ኩልነ» ይላል። መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ጠፋልን የተባለው አምኖ፤ ተጠምቆ፤ ጥሩ ሥራ ከሠራ ወደታች መውረድ የለም ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት ነው።

ቀድሞ በዘመነ ብሉይ መልካም ሥራ ቢሠሩም እነ አብርሃም ይስሐቅ፤ ያዕቆብ ሁሉ በሲኦል ነበሩ። የአዳምን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ አጠፋ የሚለው ስለዚህ ነው።

«ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ ወእድኀከ ውስተ መርህብከ ወእትቢዘወከ በሞትየ ወበ መስቀልየ» (ቀሌምንጦስ)

«ወለትከ» የተባለችው ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። (ገድለ አዳም ገጽ ፩፻፩/፩፻፳፩። መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ገጽ ፶፬–፳።

ቀደም ብሎ እንደ ተገለጸው «ከመይሥዓር መርግማ ለኦሪት» በተባለው መሠረት አዳም ተረግሞ ነበር ወይ? ሲባል መልሱ አዎ ነው።

ከገነት ሲኖር «ይችን ዕፅ የበላህ እንደሆን «ትመውት ሞተ» ሞትን ትሞታለህ» በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ፤ በርደተ መቃብር ርደተ ሲኦል ያገኝሃል ነው ያለው። «ወአልበሶሙ አእዳለ ማዕስ» ያብርሃን የነበረው፤ እንደ ብርሌ፤ እንደ ብርጭቆ ንጹሕ የነበረው እሾኽ እማይወጋው፤ እንቅፋት የማይመታው፤ እማያደማው፤ ብርድ የሌለበት የነበር በኋላ መርገም ሲያድርበት እሾክ የሚወጋው፤ እንቅፋት የሚመታው፤ ብርድ የሚሰማው ልጅነት የሌለው ቁርበት አለበሰው።

እሱ ባይረገም፤ ወደ ምድር ባይወርድ፤ በዘፍጥረት ፩፥፳፰ «ብዙ፤ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም» ብሎ ነበረ አዳም ባያጠፋ ኑሮ ሰው እንዴት ሊበዛ ይችል ነበረ ቢሉ? ይኸማ መጀመሪያ አዳም በሥልጣነ እግዚአብሔር ተገኘ እንጂ ከሴት አልተገኘም። ሔዋንም ያለ ወንድ በሥልጣነ እግዚአብሔር ተገኘች እንጂ ሴትና ወንድ ተገናኝተው አልተፈጠሩም። ባይበድሉ በሥልጣነ እግዚአብሔር ወንድም በአዳም አምሳል፤ ሴቱም በሔዋን አምሳል በሥልጣነ እግዚአብሔር እየተባዛ፤ ዕፀ ሕይወትን እየበላ ሺህ ዘመን ሲሞላው መንግሥተ ሰማያትን ሊገባ ተፈጥሮ ነበር።

እንግዲህ ለአዳም ዕፅዋትን ሰጠው፤ አንዱ የሚመገበው፤ በመዓዛው ይጠግባል፤ ሁለተኛው ሕግ ሊጠብቅለት ይችን ዕፅ አትብላ ብሎ፤ ሦስተኛው ሺህ ዘመን ኑሮ ያን ሲበላ ተሐድሶ መንግሥተ ሰማይ ሊገባ ፈጥሮት ነበር።

ይኸንንም ሰሎሞን ገልጦታል «እግዚአብሔርሰ ኢ.ገብረ ሞተ፤ አላ ረሲአን ሰብእ አምጽእዎ፤ በቃሎሙ ወዓርከ አምስልዎ» እግዚአብሔር ጥንቱን ሲፈጥረው፤ ሞት እንዲሞት፤ እንዲቀበር ወደሲኦል እንዲወርድ፤ አልፈጠረውም። ሕጉን እንዲጠብቅ ሺህ ዘመን በሕይወት እየተቀመጠ፤ ወደ መንግሥተ ሰማይ ሊገባ ተፈቅዶ ነበር። «ኢትብልዑ እምዕፅ» ይችን እንጨት አትብሉ ያለውን የዘነጉ አዳምና ሔዋን ሞትን፤ መቃብርን፤ ስበው ጐትተው አመጡት። «ወአረከ አምስልዎ» ወዳጅ አስመሰሉት አለ ወዳጅ እንዳይለይ እንዳይለይ አደረጉት። ቀጥሎ ልጆቻቸውን፤ ይህንም ቅዱስ ጳውሎስ ገልጦታል። «ወሳበ ኩነኔ ኃጢአት ወጽአ እምላዕለ አሐዱ ብእሲ ተቀሰፈ ባቲ ኵሉ ፍጥረት» (ሮሜ.፭፥፲፪)።



www.ethiopianorthodox.org

ከአንዱ አዳም የተገኘች ኃጢአት ሁሉን (መላውን) አደረሰች፤ ከአንድ ዛፍ በተቆረጠ ጨንገር ብዙ ሕፃናት እንደሚገረፉ ኃጢአትም ከአዳም ተገኝታ ሁሉን ያዘች። መባዛት በዘር በሩካቤ የሆነው ከመርገም በኋላ ነው። በገነት ሳሉ ወንድና ሴት መሆናቸው አይተዋወቁም። እዳም እኔ ብቻ ነኝ ሲል ረዳት እንድትሆነው ፈጠረለት እንጂ በዘር በሩካቤ ሊገናኙ አይደለም። ለምን ተባዙ አለ» በሥልጣኑ ያበዛቸዋል።

እግዚአብሔር ሁሉን አንድ አንድ ጊዜ ነው የተናገረው «ለታብቁል ምድር» አለ። ይኸ መሬት ሁል ጊዜ ታበቅላለች።

«ለያብርሑ ብርሃናት» አለ እነሆ ፀሐይና ጨረቃ፣ ከያለበት ሲያበሩ ይኖራሉ።

«ለታውጽእ ባሕር ዘቦ መንፈሰ ሕይወት» ሲል እዘ፣ ጉማሬ አንድ ጊዜ ሲባዙ ይኖራሉ።

## ዕለተ ኅሪት

ዕለተ ኅሪት ተብላ በኢሳይያስ የተጠቀሰችው በዘመኑ ብሉይ ዕለተ ኅሪት ዕለተ ዄዋዌናት፣ ኅሪት አላት «ወሶበ ይበዝኑ አውረከ ለትፍስሕት እንዲል፣ በሰባ ዘመን ትወጣላችሁ የሚለው ቃል ተስፋ ሰምተው ስለ ነበር ዕለተ ኅሪት አላት። ዕለተ መድኃኒት ዕለተ ሚጠት ከፋርስ፣ ከባቢሎን ሰባ ዘመን ኑረው የተመለሱበት ስለሆነች።

ዕለት ኅሪት በዘመነ ሐዲስ ዕለተ ጽንስ፣ ዕለተ መድኃኒት ዕለተ ልደት፣ ዕለት ኅሪት፣ ዕለተ ሥቅለት፣ ዕለተ መድኃኒት ትንሣኤ፣ ዕለተ ኅሪት ተስፋ ያለው ንስሐ የሚገባበት፣ ዕለተ መድኃኒት ዳግም ንስሐውን ጨርሶ ሲወጣ፣ ለበጎ ሁሉ የሚሆን እንጂ በጥቂት የሚወሰን አይደለም።

## ነፍሳት ከሲኦል የወጡ መቼ ነው

ነፍሳት ከሲኦል የወጡ ዓርብ በሠርክ ነው

ሐዋርያው ጴጥሮስ «ሰበከሎሙ ግዕዛነ» «ነጻነት አወጀላቸው» ይላል። ጌታ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ «ሰላም ለኩልክሙ» ሰላም ለእናንተ ይሁን እንዴት ሰነበታችሁ? አስታረቋችሁ ሲላቸው ነው። አዳም የተቀጠረች የድኅነት ዕለት ዛሬ ናት ተንሥኡ ለጸሎት ሲል ነፍሳትም ምስለ መንፈስከ አሉ።

ጌታም እለውስተ ጽልመተ ጻኡ ወእለ ውስተ ሲኦል ተከሠቱ ወርእዩ ብርሃነ በጽልመት ውስጥ ያላችሁ ውጡ፣ በሲኦል ያላችሁ ተገለጡ ብርሃንም እዩ» ብሎ እልፍ ፀሐይ ቢገባበት የማይለቅ የሲኦልንም ጨለማ ብርሃነ መለኮቱን ነዛበት ያኔ ጨለማው ለቀቀ የዚያን ጊዜ ወጉዩ ዓቀበተ ሥጋ መናፍስት (አጋንንት) በዚህ ጊዜ ነፍሳትን የተቆራኙ አጋንንት ሸሹ፣ እለ ውስተ ሲኦል ጻኡ፣ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሠቱ ብሎ ባሕረ እሳትን ከፍሎ፣ ወደ ገነት አገባቸው።

በዚያ በሲኦል ሳሉም «ነፍሰሙ ለጻድቃን ውስተ ዕደ እግዚአብሔር እንዲል «ያድነናል ብለው እንደ ነቢያት እንደ አብርሃም፣ ያሉ አበው ዕደ እግዚአብሔር አንደ አጉበር እንደ ድንኳን ሆኖ ይጠብቃቸው ነበር እንጂ እንደ ኃጥአን ስቃይ መከራ አይጸናባቸውም ነበር።

ፈያታይ ዘየማን ደግሞ «አንተ ትቀድሞ ለአዳም በዊአ ውስተ ገነት» «አንተ አዳምን ቀድመህ ወደ ገነት ትገባለህ» ብሎት ነበርና እሱ ተቀድሞ ሲገባ፣ አዳም ከእነ ልጆቹ ስብሐት ለእግዚአብሔር ዘአውርስነ መንግሥቶ ሰማያዊተ» ሰማያዊት መንግሥቱን ላወረሰን ለእግዚአብሔር ምስጋና የሁን» እያሉ ገብተዋል።

## በዕለተ ዓርብ ስንት ታምራት ታይቷል?

በዕለተ ዓርብ ጌታ በተሰቀለ ጊዜ የታዩት ታምራት ሰባት ናቸው።

በሰማይ ፀሐይ ጨለማ ሆነ፣ ጨረቃ ደም ሆነች፣ ከዋክብት ረገፉ፣

በምድር አዕባን ተፈተቱ፣ መቃብራት ተከፈቱ፣

አምስቱ ምእት ቢጽ የሚላቸው ሙታን ተነሡ፣

የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት ተከፈለ።

«ወወጽአ ሕሩይ መልአከ እማዕከለ ኵሎሙ መላእክት እንዘ ይእኀዝ ሠይፈ ከመያጥፍእሙ ለአላውያን፣ ወሶበ ከልአቶ ምሕረቱ ለአብ ወኂሩቱ ለወልድ ሜጠ ዝኩ መልአከ ሠይፈ ክሡተ ወዘበጦ ለመንጦላዕተ ቤተ መቅደስ ወሰጠጦ ወከፈሎ ለክልኤ።

መልአኩ ላጥፋቸው ቢለው ተው ካጠፋኋቸውማ እኔ አጠፋቸዋለሁ አይደል? ብሎ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ከለከሉት፣ መልአኩ ተናድዶ ሰይፉን ሲወረውረው የቤተ መቅደሱን መጋረጃ ለሁለት ከፈለው ብሏል። (ሃይማኖተ አበው ዘአትናቴዎስ)

## ለምን ፬፻፶ ጊዜ እግዚኦ ይባላል?

በዚሁ ዕለት በአራት መዓዝን እየዞርን ፬፻፶ ጊዜ ምሕላ እናደርጋለን፣ ምሕላ የምናደርገውም አምስት ሺሕ አምስት መቶ ዘመን የአዳም ልጆች በሲኦል ሆነው አቤቱ ይቅር በለን ብለው የለመኑትን ለማስታወስ ነው ከምሕላው በኋላ በወይራ እየተጠበጠቡ የንስሐ ስግደት እንደየአቅሙ ይሰጣል። ከምን የተነሣ ነው ቢባል የክርስቶስን መከራ እንቀበላለን፣ በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለናልና፣ የኛን መከራ ተቀብሎ እንዳዳነን እሱ የተቀበለውን መከራ እንቀበላለን፣ እንገረፋለን፣ አላውያን ነገሥታት፣ አላውያን መኳንንት ሃይማኖታችሁን ካዱ ቢሉን ቢገርፉን እንገረፋለን፣ በሰይፍ ቢመቱን፣ ቢሰቅሉን መከራውን በጸጋ እንቀበላለን ለማለት ነው። «ወዘኢጾረ መስቀለ ሞትየ ኢይጸመደኒ» እንዳለ ያለ ነው። እሱ የተቀበለው መከራ ተቀብሉ ተብሎ ታዟልና።

## በዕለተ ዓርብ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር የሚባለው ለምንድነው?

በስቅለት፣ ዓርብ ማታ ከእግዚኦታ (ምሕላ) በኋላ ንሴብሖ ይባላል። ምክንያቱም፣ እስራኤል በምድረ ግብጽ ፬፻፴ ዘመን በባርነት ቀንበር ሲገዙ ከነበሩ በኋላ በሙሴ መሪነት የኤርትራን ባሕር ስላሻገራቸው «ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሓ» እያሉ አመስግነውታል። እኛ ደግሞ ከአጋንንት አገዛዝ ነጻ አውጥቶ ባሕር እሳትን ከፍሎ ወደ ገነት ስለአገባን «ንሴብሖ» እያልን እናመሰግነዋለን።

ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ከተባለ በኋላ እግዚአብሔር ይፍታ ይባላል። እግዚአብሔር ይፍታ የሚባልበት ምክንያትም ካሣ ከተፈጸመ ወዲያ፣ ልጅነት የተመለሰ፣ ነፃነት የተገኘ፣ ነፍሳት ከሲኦል የወጡ ስለሆነ ነው።

## ቅዳሜ ሥዑር

እስከ ምሴተ ሐሙስ ወይም እስከ ሐሙስ ማታ ጌታ የኦሪትን ሥራ ይሠራ ነበር። ከምሴተ ሐሙስ ጀምሮ መስዋዕተ ብሉይን፣ ሥርዓተ ብሉይ አሳልፎ ላም፣ በግ፣ ፍየል እንዳይሰዋ ከለከለ። መስዋዕቱን በስንዴና በወይን አድርጎ። ቀጥሎ ደግሞ አይሁድ ቅዳሜን ያከብሩ እሑድን ይሽሩ ነበር። ስለዚህ ቅዳሜን ብቻ ሳይሆን መላ የኦሪት በዓል ተሽሮ በዚያ ተተክቷል።

ለምሳሌ:- በበዓለ መጥቅዕ ቅዱስ ዮሐንስ መስከረም ፩ ቀን ገባ፣

በሠርቀ ወርኀ ልደተ ክርስቶስ፣

በበዓለ መጸለት በዓለ ጥምቀት

በበዓለ ፍሥሕ ስቅለተ ክርስቶስ

በበዓለ ፋሲካ በዓለ ትንሣኤ

በበዓለ ሠዊት በዓለ ጰራቅሊጦስ

በጾመ አስቴር ጾመ ረቡዕ

በጾመ ዮዲት ጾመ ዓርብ

በጾመ ሙሴ ጾመ እግዚእነ

በቅዳሜ ዕለተ እሑድ ተክቶበታል።

ስለዚህ ነው ተሻረ ያሰኘው። ቅዳሜ የምትቆጠረው ከዐሠርቱ ቃላት ነው። እንዴት ተሻረች ይባላል የሚል ካለ? «አክብር ሰንበቶ «ስለ በማለቱ እሑድን ተካ እንጂ ከዓሠርቱ ቃላት አልጐደለም። አንድ ምሳሌ ጥቀስ አንድ ሰው አንድ ብር ተበድሮ ይሄዳል፣ ተመልሶ የሰጠኝ እንደሆን ጐደለ ያሰኛል ወይም ብሩ ጐደለ ይባላል አይባልም። እንደዚሁም በቅዳሜ ፈንታ እሑድን ተካባት እንጂ አላጐደላትም «ሠለስቱ ምእትም» ወሠዓሩ ለሰንበተ አይሁድ ወሠርዐ ህየንቴሃ ዕለተ እሑድ ቅድስት «ሰለ ቅዳሚት ፈንታ እሑድን ሠራ መላው በዓል ተተክቶበታል ማለት ነው። ሰው ግን በልማድ እሺ አይልም። በሕንጸ መነኮሳት ዓመት እስከ ዓመት ጾም እንድትጾም አዘውባታል። «ወኢይደሉ ይጹሙ በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት እስከ ዕርበተ ፀሐይ አው እስከ ስድስቱ፣ አው እስከ ሰብዓቱ ሰዓት፣ «በቀዳሚት ሰንበት እስከ ዕርበተ ፀሐይ ወይም እስከ ስድስት ወይም እስከ ሰባት ሰዓት ሊጾሙ አይገባም። በሰባት ሰዓት በልቶ ቤተ እግዚአብሔር ሲያገለግል ይደር ተብሎ ተሠርቷል።

ሠለስቱ ምእትም በሃይማኖተ አበው ኢይደልዎሙ ከመያጽርኡ ተገብሮ በዕለተ ቀዳሚት ሰንበተ ከመ አይሁድ።

ክርስቲያኖች በዕለተ ቀዳሚት እንደ አይሁድ ሥራ መፍታት አይገባቸውም። ጌታችንም ሲያስተምር ደቀ መዛሙርቱ እሸት ቀጥፈው ሲበሉ ፈሪሳውያን ርኢ ዘይገብሩ አርዳኢከ ዘኢይከውን ገቢረ በዕለተ ሰንበት ደቀ መዛሙርቶችህ በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት ሊደረር የማይገባውን ሲያደርጉ አታይምን ብለው ቢጠይቁት ጌታም ሲመልስ ለምን ነው እሸት አሽተው ቢበሉ የምትፈርድባቸው? ሶበሰ ተአምሩ ምንት ውእቱ ዘይቤ ምፅዋተ አባድር እመሥዋዕት እምኢኰንንክምዎሙ ለእለ ኢይኤብሱ እስመ እግዚእ ውእቱ ለሰንበት ወልደ እጓለ እመሕያው» «ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም። ያለው ምን እንደ ሆነ ብታውቁስ ኃጢአት የሌለባቸውን (ሐዋርያትን) ባልኮነናችኋቸው ነበር የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና ብሎአቸዋል። (ማቴ.፲፪)።

ቀጥሎ ደግሞ እነሱ መንገድ አይሄዱም ጌታ ግን «ወበውእቱ መዋዕል ወፈረ ኢየሱስ በሰንበት ማዕከለ ገራውኅ» በዚያው ወራት ኢየሱስ በሰንበት ከእርሻ መካከል ሲያልፍ ደቀ መዛሙርቱ እየሄዱ እሸት ይቀጥፉ ነበር (ማር.፪፥፳፫)።

በዮሐንስ ወንጌል «አኮ ዘይሥዕር ሰንበተ ባሕቲቶ ዓዲ አባሁ ይሬስዮ ለእግዚአብሔር...» ሰንበትን ስለሻረ ብቻ አይደለም ነገር ግን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ እግዚአብሔር አባቱ ነው ስለ አለ...» ወኢያብኡ ጾረ ክቡደ ውስተ ኀዋኅዊሃ ለኢየሩሳሌም በነፍስከሙ» (ኤርምያስ) ያለውን ይዘው በሰንበት አይሸከሙም።

ጌታ ግን ሰላሳ ስምንት ዘመን የታመመውን መጻጉዕን «ንሣዕ ዓራተከ ወሑር» «አልጋህን ተሸክመህ ሂድ» አለው። አልጋው የብረት ነው፣ አልጋውን ተሸክሞ ሄዷል።

ጌታ ሳዓሬ ሰንበት የተባለበትን ዕለት፣ አከብራለሁ ማለት ያው የአይ

www.ethiopianorthodox.org

ሁድ ረዳት መሆን ነው። «ይከውንኑ ገቢረ ሠናይ በሰንበት?» በቀዳሚት ሰንበት፣ በጎ ሥራ መሥራት ይገባ ልን። «ሠናይ» እርሻ ብሎታል። ወአ ትሐተ መትከፎ ከመ ይትቀነይ «ይት ጌበራ» ያለውን ሠናይት አላት። አን ዳንዱ ደግሞ ቅዳም ሥሁር የተባለው ዲያብሎስ የተሻረበት ነው በማለት የሚናገሩ አሉ። የዲያብሎስ መሻር ከዚህ ጋር የሚገናኝበት የለም። ዲያብ ሎስ የተሻረ ዓርብ ዕለት ነው። ወተ ርፈ ውሳጤ ነፋሳት ዘኢይክል ያንቀ ልቅል፣ ወዲያና ወዲህ ማለት ዲያብ ሎስ አቅቶት ተሰቅሎ የዋለ ዓርብ ዕለት ነው እንጂ ቅዳሜ ዕለት አይደለም።

## ካህናት ቤተ ምዕመናን እየዞሩ ለምን ቈጤማ ያድላሉ?

ካህናት በቅዳሜ ሥዑር ነግህ (ጧት) በየቤቱ እየዞሩ ቈጤማ (ግጫ) የሚያድሉበት ምሳሌ አለው።

ማየ አይኅ በወረደ ጊዜ መርከቢቱ እየተንሳፈፈች አራራት ላይ አረፈች። ኋላ ኖኅ ርግብን ላካት ግጫ ይዛ መጣች። የምሥራች ውሃው ደረቀ ስትል። ያ ቀደም ብሎ የተላከው ቁራ ከዚያው ቀረ፣ የሰይጣን ምሳሌ ነው፤ ርግብ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ፣ ግጫው ውሃው ጐደለ ና ከመርከብ ውጣ፣ ብላ ሰጠችው። እኛ ደግሞ የምሥራች መርገመ ኃጢአት ተሽሮ፣ ሞተ ነፍስ ጠፍቶ ባሕረ እሳት ተከ ፍሎ ነፍሳት ገነት ገቡ ሰው ከፈጣሪው ጋር ታረቀ፣ ዲያብሎስ ተሻረ ገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ እያልን ቈጤማ ይዘን የምሥራች እንናገራለን።

### ገብረ ሰላመ

ገብረ ሰላመ ማለት ሰባቱ መስተ ጻርራንን አስታረቀ ማለት ነው

ሰባቱ መስተጻርራን የተባሉት፤

ሰውና እግዚአብሔር
ሰውና መላእክት
ሕዝብና አሕዛብ

ነፍስና ሥጋ፣ እነዚህ ለ፭ ሺህ ፭፻ ዘመናት ተለያይተው ይኖሩ ነበር።

«ወነሠተ ዓረፍተ እንተ ጽልእ በሥጋሁ።»

ሰባቱን መስተጻርራን አስታረቀ ሲል «ገብረ ሰላመ» ሰላምን አደረገ አለ።

ሰውና እግዚአብሔር በአዳም ምክንያት ተጣልተው ስለ ነበር።

ሰውና መላእክትም መላእክት ነፍሳትን ወደ ገነት እያገቡም ነበር ወደ ሲኦል እንጅ ወደ ገነት የሚገባ አልነበረም። ዛሬ ግን የጻድቅ ነፍስ መላእክት በይባቤ ይዘዋት ወደ ገነት ሲገቡ፣ በመዓዛ ገነትን ትለያለች።

ሕዝብና አሕዛብ «ኢይባእ ሞአባዊ ወአሞናዊ» «ሞአባዊእና አምናዊ አይገባ» ባለው መሠረት ከአብርሃም ልጆች በቀር ቤተ መቅደስ አያስገቡም ነበር። አሁን ግን «ዘአምነ ወዘተጠምቀ ይድኅን የአመነና የተጠመቀ ይዳን ብሎ ለመላው ለአዳም ልጅ ድኅነቱን ሰጧል።

ነፍስና ሥጋ፣ ዲያብሎስ ነፍሳትን በሲኦል ተቆራኝቼ እኖራለሁ ሲል ከሲኦል አወጣበት። ሥጋም አበስብሼ አስቀራለሁ ብሎ ነበር። ጌታ አምስት መቶ ቢጽን አስነሳበት። ተንሥአ እግዚእነ ከመይምሐረነ በተንሥኦ ሥጋቲነ እንዳሶ የእኛን ትንሣኤ በእሱ ትንሣኤ አስረዳ።

### ትንሣኤ ክርስቶስ

ስለ ክርስቶስ መነሣት አስቀድሞ ትንቢት ተነግሯል።

ይህም ዳዊት «ይትነሣዕ እግዚአ ብሔር ወይዘረው ጸሩ ወይጉየዩ ፀላ ዕቱ እምቅድመ ገጹ እግዚአብሔር የነሣ፣ ጠላቶቹም ይበተኑ፣ የሚጠ ሉትም ከፊቱ የሸሹ። (መዝ.፷፯፥፩) ወተንሥአ እግዚአብሔር ከመዘንቃህ እምነዋም ወ[illegible]መ ኃይል ወኅደገ ወይን ወቀተለ ፀሮ በድኅሬሁ» እግዚአ ብሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነማ፣ የወይን ስካር እንደተወው እንደኃያል ሰው ጠላቶቹንም በኋላ ቸው መታ (መዝ.፸፯፥፷፭)።

በደቂቀ ነቢያት:- በሠኑይ ዕለት ይቀስፈነ ወበሠሉስ መዋዕል ይሠርየነ ወየሐይወነ» አመሣልስት ዕለት ይትነሣእ ወንቀውም ምስሌሁ።

በአሪት አንበሳ ዕጓለ አንበሳ ስከ ብከ ዕርግ እምንዝኅትከ እየተባለ በብሉይ በሐዲስ በብዙ ዓይነት ተነግሯል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን በሞቱ ድል አድርጎ ተነሣ ማለት መግነዝ ፍቱልኝ፣ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ዝም ብሎ ድንጋዩ እንደ ተገጠመ ተነሥቶ ሄደ። ከዚያ በማርቆስ ወንጌል እንደ ተጻፈው ሴቶች ወደ መቃብሩ ሂደው «መኑ ይከሥትለነ» «ድንጋዩን የሚገ ለብጥልን ማነው?» ሲሉ መላእክት አነሱላቸው (ማር.፲፮፥፩–፰፤ ማቴ. ፳፰፥፩–፰፤ ሉቃ.፳፬፥፩–፲፤ ዮሐ. ፳፥፩)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮ ንቶስ ክታቡ «ክርስቶስ ላንቃላፉት በኵር ሆኖ ተነሥቷል» ይላል ይህም ማለት መጀመሪያ ትንሣኤ ዘጉባኤ የተ ነሣ እሱ ነው። ሌላ ገና አፈር ሆኖ ለመነሣት ዕለተ ምጽአትን ይጠ ብቃል፤ «ተንሥአ እግዚእነ ከመይ ምሐረነ በተንሥኦቱ እንከሰ ዳግመ ኢይመውት «ከእንግዲህ ወዲያ ሁለ ተኛ አይሞትም» እነ አልአዛር ቢነሱ ተመልሰው ሞተዋል፤ ትንሣኤ ዘጉ ባኤን ይጠብቃሉ።

ጌታችንና እመቤታችን ግን ተመ ልሰው አይሞቱም። እንዲህ ያለው ትንሣኤ ዘጉባኤ ይባላል። «ቀደመ ተንሥአ እምኵሉሙ ሙታን» ከሙ ታን አስቀድሞ ተነሣ የተባለው ስለዚህ ነው። እስከ አሁን ሁለቱ ብቻ ናቸው ትንሣኤ ዘጉባኤ የተነሡት። ከዚህ ጋር አብሮ ሊታይ የሚገባው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣ ማርያም መግደላዊት ቀርባ ልት ነካው ባሰበች ጊዜ ገና ወደ አባቴ አላረኩምና አትንኪኝ ብሎ እንደ ነገራት በዮሐንስ ወንጌል ተጽፎ እና ገኘዋለን። የዚህ ዋና ትርጉሙ ጌታችን ሲት እንዳትነካው (ንቆ) ሳይሆን ማርያም መግደላዊት የሚያ ርግ መስሏት ስለ ነበር ገና ፴ ቀን እቆ ያለሁ ለማለት ነው።

ወንጌላዊው ዮሐንስ በሌላ ምዕ ራፍ «አኀዘ እገሪሁ ወሰገዳ ሎቱ» እግሮቹን ይዘው ሰገዱለት» ይላል።

አሁንም በዚሁ ምዕራፍ ፳ ቁጥር ፳፬ «ከአሥሩ ሁለቱ አንዱ ዲዲሞስ የሚባለው ቶማ፡ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከእነርሱ ጋር አልነበረም ምልክት ከእጆቹ ካላየሁ፣ ጣቴንም በችንካሩ ም[illegible] በጎኑ ካላገባሁ አላምንም» [illegible] ያስረዳል። በእርግጥ ቶማስ ጌታ ከሙታን ተነሥቶ በዝግ ቤት ገብቶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰላም ለእናንተ ይሁን ሲላቸው አልነበረም በዚህም ምክንያ[illegible] ተጠራጥሮአል።

ጌታ ደግሞ ለምን ተጠራጠርከ ካልዳሰስኩህ አላምንም ብለሃል። በልና የተወጋው ጐኔን እይ፤ የተቸ ነከረው እጄን ተመልከት። ብሎ እንዲ ዳስሰው ፈቀደለት። ቶማስም ሲዳስስ እሳተ መለኮት ቀኝ እጁን አቃጠለው።

«እግዚእየ ወአምላኪየ» ፈጣርዩ አምላኪ» አምላኪየ «መዳሰሱ ሲያይ» እግዚእየ» ማቃጠሉን ሲያይ አምላኪየ አለ። ይኸንን «እግዚእየ ወአምላኪየ» ያለውን ወስዶ በሃይ ማኖተ አበው «አንተ ቀዳማዊ፡ ወእ ንተ ደኅራዊ» አንተ መጀመሪያ አን ተም መጨረሻ ነህ» ብሎ ተርጉ ሞታል። (ኤራቅሊጦስ)

ይህች ገቦ መለኮት የዳሰሰች እጅ ሳትሞት ሕያዊት ሆና በሕንድ ሀገር ከታቦት ጋር ትኖራለች። ጥር ፳፩ ቀን የአስተርእዮ ዕለት በዓሉ ይከበራል። ይኸ ታሪኩ የሚገኘው መጽሐፈ እንድ ልስ በሚባለው ነው።

ቅዱስ ያሬድ «ይትፌሣሕ ሰማይ ወትትሐሰይ ምድር ወይንፍሑ ቀርነ መሠረታተ ኅምዝ» ያለው ትሑታኑ ደቂቀ አዳም፣ ልዑላኑ መላእክት ጌታ አስታረቃቸው። ሁሉም ደስ አላቸው ማለቱ ነው ሰማያውያንና ምድራ ውያን በክርስቶስ አንድ ሆነአልና። ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ፣ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ «ምድርም በክርስቶስ ደም ተቀድሳ የክርስቶስን ትንሣኤ ታከብራለች።

አንድም ያመኑ ምዕመናን ሁሉ በክርስቶስ ደም ነጻ ወጥተው በዓለ ትንሣኤን ያከብራሉ መጽሐፍ ለግ ዕዛን ሰጥቶ መናገሩ የተለመደ ነው።

«ትባርኮ መድር ለእግዚአ ብሔር» ምድር እግዚአብሔርን ታመ ሰግናለች ይህ ማለት ማኅበረ ምዕ መናን እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ማለት ነው። ክብር ምስጋና ይግባውና መድኃኔዓለም ክርስቶስ ሦስት መዓ ልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር በመቆየት ሙስና መቃብርን አጥ ፍቶ፤ ሞትን ድል ነስቶ ተነሥቶልናል።

### ሠሉስ መዋዕለ ወሠሉስ ለያልየ

የሚለው በሰዓት ሲቆጠር አይሞላም ይህ እንዴት ነው? ቢሉ? እንግዲህ ጌታ በምሴተ ሐሙስ ሦስት ሰዓት አሳልፎ ነው መከራ መቀበል የጀመረ። ሥጋወደሙ ለሐርያት የሰጣቸው በዕለተ ኀሙስ ነው።

ስለዚህ «መዓልት ይስሕቦ ለሌት፣ ወሌሊት ይስሕቦ ለመዓልት» «ቀን ሌሊቱን ይስበዋል፣ ማለት መዓ ልተ ዓርብ ሌሊተ ኀሙስን፣ መዓልተ እሑድ ደግሞ ሌሊተ እሑድን ሲስ በው፣ ቅዳሜ መዓልትና ሌሊት፣ ሲቀ መር ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት የተባለው ይኸ ነው። ✣

### ለብፁዕ አቡነ ቊርሎስ ሊቀ ጳጳሳት

ወመትልወ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የቀረበ አጭር ታሪካዊ ጋዜጣ

ብፁዕ አባታችን በዓለም ላይ የሠሩት ትሩፋት የአደረጉት ተአምራት እጅግ በጣም ብዙ ነው። ነገር ግን የተቻለንን ያህል እንናገራለን ይልቁንም በሙቂት ወረዳ ውስጥ በሚገኘው ታላቅ ገዳም ደብረ አቡነ አሮን መንክራዊ በዓሉን ለማክበርና ለጉብኝት በመጡ ጊዜ የሠሩት ተአምራት:-

፩ኛ. ሥርዓተ ቡራኬ ከፈጸሙ በኋላ እንደ ኤልያስ ከሰማይ ዝናም ወርዶላቸው በድርቅ የተጐዳው ሕዝብ በጠላ ረድኤታቸው በረከት አግኝቷል።

፪ኛ. ይህ ብፁዕ አባታችን የአደረጉት ትሩፋት ለገዳማትና ለአድባራት ገንዘብ በመለገስ የፈረሱትን በማደስ የተዳደፉትን በመቀደስ ደግሞም ለመምህራን በጀት በመበጀት ለልዩ ሠራተኞች የደመወዝ እድገት በመሥጠት ይገኛሉ። ይሁንና በጣም አስደናቂ ተግባራቸው የሙቂት ወረዳ ቤተ ክህነት የመሰብሰቢያ አዳራሽ አለመኖሩን በማሰብ የካህናትንና የመምህራንን ችግር በመገንዘብ በታውን ባርከው ወርድና ቁመቱን ለክተው ከዚህ ይሠራ ብለው ከስድስት ሺህ ብር በላይ በመለገስ ተሠርቶ እንዲፈጸም አዘዙ። እነሆ የቤቱ ምርቃን ደረሰ መልካሙ አዳራሽ ታደሰ።

በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ
አንድ አምላክ በሆኑ ሥላሴ ሥሉስ
አምኘ በቅድሚያ ጋዜጣ ልድረስ
ክብር ለሚገባው ብፁዕ ቊርሎስ
በነቢያት አድሮ ትንቢት ያናገረ
በሐዋርያት ላይ ምሥጢር ያስተማረ
ለሌሎቹም ሁሉ ጸጋን ያልሠወረ
ቸሩ ፈጣሪያችን በእኛ ላይ ጀመረ።
ነቢይ ተቀብሎ የነቢዩን ዕድል
ጻድቅን አክብሮ የጻድቁንም ገድል
ዋጋውን ያገኛል ባልኸን ቃል
አሁን ልጀምር ነው የቅዱሱን ዜና
ገድላቸው እንዲጻፍ ታሪኩ እንዲጠና
በአምላካዊ ቃል አዘዙናልና
የብፁዕ ቊርሎስ አያልቅም ታሪኩ
ብዕር ቢቀርፁ ብራና ቢለኩ
ረጅም ነው ጉዞው ሠፊ ነው መድረኩ
እስኪ ትንሽ ላስታውስ ከሠሩት ትሩፋት
በሰሜን ወሎ በዋድላ በዳውንት
ቅዱስ ላሊበላ በሸደሆ ሙቂት
በምድረ ተከዚ በእግራቸው ሲጓዙ
ሲደክሙ የሚያርፉበት መኪና ሳይዙ
ታላቅ ሰማዕትነት በላባቸው ገዙ
ዓቢይ ሐዋርያ ቃል ኪዳን ብዙ
ሕዝብ ሲያስተምሩ ገዳም ሲጐበኙ
ቀን ዕረፍት የላቸው በሌሊት አይተኙ
እንዲህ ያሉ ብፁዕ ከቶ የት ተገኙ
እንደ ኖኅ ቅንነት እንደ ኢዮብ ትዕግሥት
እንደ ሴም ቡራኬ ጸጋና ትንቢት
መርቆ ሰጣቸው አምላክ እንደ ሀብት
ፍቅረ ማሕሌትን እንደ መላእክት
ቅዱስ ስቡሕ ሊሉ ቀንና ሌሊት
ከሰዓት በኋላ ለሰንበት ትምህርት
እኛም አንመኘው የርስዎን ዕረፍት
በሥውር ይኑሩ በእግረ ገነት
እንደነ ኤልያስ እንደ ነቢያት
እንዳያገኝዎት ያ መልአከ ሞት
ዘውገ መልከ ጼዴቅ የዓለም ካህን
መትልወ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን
ሐውልት ዘኢያሱ ዘሳሙኤል ቀርን

ወደ ሽፋን የውስጥ ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# እኔም ወጣት ነበርኩ

## የልማት አባት

(የብዕር ቅኝት በመምህር ዕንቁባሕርይ ተከሥተ)

ብዙዎች ብፁዕ አቡነ መቃርዮስን የሚያውቋቸው በቤተ ክርስቲያን ሊቅነታቸው፣ በልማት እንቅስቃሴያቸው እና በአርቆ አስተዋይነታቸው ነው። ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ቀደምት ከሆኑ አባቶች ግርማ ሞገሳቸው የሚያስገርም፣ ፍትህ አዋቂና ብዙ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን ለእውቀት ለሙያ፣ ያበቁ አባት ናቸው።

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የሴንተራል (ማዕከላዊ) ኮሚቴ አባል በመሆን ከ፲፬ ዓመታት በላይ አገልግለዋል። እንደዚሁም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ወክለው ብዙ ዓለማትን ዞረዋል፣ የቤተክርስቲያናችን እምነትና ትምህርትም አስፋፍተዋል።

ዛሬ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የ፸፰ ዓመት አዛውንት አባት ናቸው። እንደዚያ ሆኖ ግን በእሳቸው ዘንድ ድካም ብሎ ነገር አይታወቅም። በአሁን ጊዜ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የሊቃውንት ጉባኤ ሊቀ መንበር ናቸው። መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ መች ይደርስ ይሆን? እያለ የሚጠባበቀው የመጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት በእሳቸው መሪነት ሥራው ሌት ተቀን እየተካሄደ ይግኛል። አንባቢዎች ከእኚሁ ታላቅ አባት ያደረጉት ውይይት ለንባብ በሚመች ሆኖ ተዘጋጅቷልና እንከታተል።



በተያዘው ቀጠሮ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስን ለማነጋገር በሄድኩበት ጊዜ በጣም ዝናም ስለ ነበረ ከተያዘው ቀጠሮ ዘግይቼ ነበር የደረስኩት። ብፁዕነታቸው ግን ሲቀበሉኝ ፈገግታ በተሞላበት አቀባበል ነው።

በዚያ ደርባባው ትከሻቸው ነጭ ጋቢያቸውን ተጎናጽፈው በመንበረ ክብራቸው ቁጭ ብለው እኔ ለምጠይቃቸው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንደ ተዘጋጁ ቶሎ ስለገባኝ፣ እኔም ማስታወሻዬን አወጣሁና በመጀመሪያ ያቀረብኩላቸው ጥያቄ ብፁዕ አባታችን ከቤተሰብ እስከ ቤተ ጉባኤ የነበረ ዕድገትዎን ቢገልጹልኝ በማለት ነበር።

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የተወለድኩ በ፲፱፻፲፰ ዓ.ም ከመምህር ወልደ ሥላሴ እና ከወ/ሮ መልከአ ማርያም ነው። የተማርኩትም ከተለያዩ ሊቃውንት ነው። ይህም ከፊደል እስከ ዳዊት በበጋ ገዳም፣ ጽዋትወ ዜማ ጭህ ከሚባለው ታላቅ ገዳም፣ መጽሐፍተ ብሉያትና ሐዲሳት በጐንደር ከተለያዩ ሊቃውንት፣ ቅኔና አቋቋም በመጀመሪያ እንደርታ ከነበሩ ከየኔታ አዛርያስ ነው። ፍትሐ ነገሥትም በደብረ ኃይል ወደብረ ጥበብ በዓታ፣ ማዕርገ

ምንኩስና የተቀበሉ መቼና የት ነው? ለሚለው ጥያቄም ሲመልሱ መዓርገ ምንኩስና የተቀበልኩት በጋ ገዳም መምህር ዘሚካኤል ከሚባሉ አበው ነው። ከሀገር ቤት ወደ ጐንደር የመጣሁትም በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም ነው ብለዋል።

### ጉዞ ወደ አዲስ አበባ

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ በጐንደር ርእሰ ከተማ ከታወቁ ሊቃውንት የመጻሕፍት ትርጓሜን ለብዙ ዓመታት ተምርው ካጠናቀቁ በኋላ የተቀረውን ትምህርት በአዲስ አበባ ከሚገኙ የአብነት መምህራን ትምህርት ለመቅሰም ወደ አዲስ አበባ አምርተዋል። ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ከመንፈሳዊ ትምህርት ባሻገር ከፍተኛ ትምህርት ለመማር በ፲፱፻፵፰ ዓ.ም በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ፈቃድ ወደ ኢየሩሳሌም ተልኬ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከሚባለው የእንግሊዝ ኮሌጅ ለ፪ ዓመታት በመማር ዲፕሎማ ተቀብየ ወደ ቅድስት ሀገሬ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሻለሁ።

ከኢየሩሳሌም መልስ በኋላም የተመደብኩት በቆሞስነት በጅማ ዞን ነው። በዚህ ሀገረ ስብከት ለ፰ ዓመታት አገልግያለሁ። የፈራረሱት አብያተ ክርስቲያናትን በማሳደስ፣ በልማት በኩልም ለአካባቢው ተስማሚ የሆነው ቡና፣ ማንጎ፣ ዘይቶና...ወዘተ ብዙ የልማት ሥራዎችን አከናውኛለሁ።

ከዚህ በኋላ ከአምስት ኤጲስ ቆጶስ ጋር የካቲት ፰ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ስድስት ኤጲስ ቆጶሳት ስንሾም እኔም፣ የከፋ ሀ/ስብከት ጳጳስ በመሆን ተሾሜያለሁ። በዚያም ለጥቂት ጊዜያት ከቆየሁ በኋላ ወደ ሸዋ ሀገረ ስብከት በመዛወር ሰበካ ጉባኤን በማቋቋሙ ረገድ ከፍተኛ አገልግሎት አበርክቻለሁ። ይህ ሁሉ ሥራ ታይቶ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እንደራሴና የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኜ እንድሠራ ተደርጓል።

ከዚህም ባሻገር የልማትና ተራድኦ ኮሚሽን የቦርድ ሊቀመንበር በመሆን ለብዙ ጊዜ አገለግያለሁ። በመቀጠልም፣ ወደ ባሌ ሀገረ ስብከት ተዛውሬ ለ፪ ዓመታት አገልግያለሁ።

### በጐጃም ሀገረ ስብከት

ብዙ ጊዜ የልማት አባት ተብሎ የሚነገርላቸው ብፁዕነታቸው ከሌሎች ከፍላተ ሀገራት ከሠሩት በከፍተኛ ደረጃ በዚሁ ሀገረ ስብከት ብዙ ቋሚና መሠረታዊ የሆኑ የልማት ሥራዎች መሥራታቸውን እንዲህ በማለት ይገልጹታል። ወደ ጎጃም ሀገረ ስብከት የተዛወርኩት በ፲፱፻፸ ዓ.ም ነው።

በዚሁ ሀገረ ስብከት የሰበካ ጉባኤ አስተዳደርን በመላ ጐጃም አቋቁመዋል። በዚህ ጊዜ ሀገረ ስብከቱ ለብዙ ጊዜ ከሌሎች አኅጉረ ስብከቶች አንደኛ ሆኖ ወጥቷል። ከዚህም ሌላ የጐጃምና የጐንደር ካህናት የሚሰለጥኑበት፣

የካህናት ማሠልጠኛ በባሕር ዳር፣

የሕፃናት ማሣደጊያ ድርጅት በባሕር ዳር ከተማ በሽምብጥ /ቅ/ሚካኤል ገዳም፣

በሞጣ ቅ/ጊዮርጊስ፣

በደብረ ማርቆስ ጣቢያዎች እንዲቋቋም አድርጌአለሁ።

የሴቶች ገዳም በባሕር ዳር አቡነ ገሪማ ገዳም፣

የወንዶች ገዳም በባሕር ዳር ከተማ የአቡነ አረጋዊ ገዳም፣

በደብረ ማርቆስ ገዳመ አስቄጥስ ከእነ መላ ንብረቱ ተቋቁመዋል።

### የልማት እንቅስቃሴ በጐጃም

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ በልማት እንቅስቃሴ በኩል አሉ ከሚባሉ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በግንባር ቀደምትነት የሚገኙ አባት ናቸው።

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ በጐጃም ሀገረ ስብከት የሠሯቸው ሥራዎች በገዳመ አስቄጥስ የንዋያተ ቅዱሳት ማስፋፊያ የሸመና ማሽን፣ የእንጨት ማሽን፣ ፪ የእህል ወፍጮ አቋቁመዋል። ሌላውን ብፁዕነታቸው እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል።

በባሕር ዳር ከተማ አቡነ ገሪማ የሴ ቶች ገዳም የሸመና ሥራ፣ የዓሣ ማስ ገሪያ የተለያዩ ጀልባዎች፣ ቤተመ ጻሕፍት አቋቁሜአለሁ።

በባሕር ዳር ዙሪያ የሚገኙ ጥንታውያን ገዳማት ባሕር ዳር ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ሽምጥ ቅዱስ ሚካኤል፣ ደጋ እስጢፋኖስ፣ ክብራን ገብርኤል ለእነዚህ ሁሉ ጀልባዎች ተሰጥቶአቸው፣ ገዳማቱ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በጀልባው ተጠቃሚ ሆኖአል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ዲያቆናትና መነኮሳት ወደ ሆላንድ እየላክን በማሠልጠን ቤት ክርስቲያናችን፣ በሠለጠነ ሰው በኩል ራሷን ለማስቻል ከፍተኛ ጥረት አድርጌያለሁ። በባሕር ዳር የካህናት ማሠልጠኛ ፪ አዳራሽ ከ፰፭ ክፍል በላይ ተሠርቷል።

ከዚህም ሌላ ከባሕር ዳር መስተዳድር ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤትና መንበረ ጵጵስና ቦታ ተረክበን ከ፯ መቶ ሺህ ብር በላይ ወጪ በማድረግ ፪ ትላላቅ አዳራሽና የተለያዩ ቢሮዎች ፲፩ ክፍል የሊቃነ ጳጳሳት ማረፊያ አሠርቻለሁ።

www.ethiopianorthodox.org



የልማቱ አድማስ በማስፋፋት ለደብረ ማርቆስ እና በደብረ ማርቆስ አካባቢ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት፣ የተግባረ ዕድ ማሽን፣ የጫማ ማሽን፣ ለደብረ ወርቅ የከብት እርባታ ለሞጣ ጊዮርጊስ ፫ ወፍጮና የከብት ርባታ፣ ለአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን የሽመና ማሽን፣ ለመርጡለ ማርያም ዳቦ መጋገሪያ እና ወፍጮ፣ ለፍኖተ ሰላም ጊዮርጊስ ዘመናዊ ክሊኒክና አዲስ የቤተ ክህነት መሥሪያ ቤት፣ በዳንግላ ቅ/ማርያም የአውራጃው ቤተ ክህነት ከእነ ሙሉ ድርጅቱ፣ በቡሬ ከተማ የአውራጃው ቤተ ክህነት ከእነ ሙሉ ድርጅቱ አቋቁመናል። አደራጅተናል። ምናልባት፣ በጐጃም ክፍለ ሀገር ውስጥ ያልተጐበኙ አብያተ ክርስቲያናት ካሉ እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ከዚህ በኋላ የተዛወርኩት ወደ ትግራይ ሀገረ ስብከት ነው።

## የብፁዕ አቡነ መቃርዮስ አገልግሎት በትግራይ ሀ/ስብከት

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ጀምሮ ወደ ትግራይ ሀገረ ስብከት ተመድበው ከሄዱ ጀምሮ የተለመደው ሐዋርያዊ ትምህርታቸውንና ልማታዊ እንቅስቃሴያቸውን ቀጠሉበት። በዚህም በመጀመሪያ በመቀሌ መንበረ ጵጵስና ትልቅ አዳራሽ አሠርተዋል። በመላ የትግራይ አውራጆች ሐዋርያዊ ጉዞ በማድረግ ሰበካ ጉባኤ እና የአውራጃዎች ቤተ ክህነት አጠናክረዋል።

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ዋልድባ ገዳም ድረስ በእግራቸው በመሄድ ቀድሰው በማቁረብ አበውን በመጐብኘት የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ ናቸው። ሰጠ ኢላላ በሚባለው ሜዳ መሬት ከመንግሥት ተረክበው በጋ ከክረምት የማያቋርጥ ልማት አትክልት ልዩ ልዩ ፍራፍሬ የሚሰጥ ልማት አሠርተዋል።

### አዲስ አበባ

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ከትግራይ ወደ አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ከተመለሱ በኋላ በአዲስ አበባ በርካታ አብያተ ክርስቲያንእንዲሠሩ አድርገዋል።

### የመጻሕፍት ኅትመት

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ከጵጵስና በፊትና በኋላ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ጽፈዋል። እነሱም:-

፩ኛ. ሐዋርያዊ ጉዞ

፪ኛ. እስከ ማዕዜኑ ተሐንክሱ በክል ኤሆን ጌጋያቲከሙ

፫ኛ. መንገደ ሰማይ እና

፬ኛ. መጽሐፈ ገነት የሚሉ ናቸው።

የአሁንና የቀድሞ የሰንበት ት/ቤቶች እንቅስቃሴ እንዴት ያዩታል? ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ሲመልሱ አሁን ያለው የሰንበት ት/ቤት በጣም የሚደግፍ ነው። እየኽ በውጪ ዓለማት ሰንበት ትምህርት ቤት ሠልጥነው እስከ ጵጵስና ደርሷል። ከዚያም ደረጃ በደረጃ ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ናቸው። ቤተክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጣቶችን በሚገባ እያስተማረች በዚህ ብትቀጥል የበለጠ ይሆናል በማለት በአንክሮ ገልጸውልኛል።

ከዚህ ጋር አያይዤ የጠየኳቸው በአሁን ጊዜ የግእዝ ትምህርት እንደ ቀድሞ አይደለም፣ ትኩረት የተነፈገው ይመስላል? ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ታሪክ በግዕዝ የተጻፈ ነው። ጉዳዩ ከዚህ ከቀጠለ አሳሳቢ ይሆናልና መፍትሔው ምን ይመስልዎታል ብዬ ነበር።

ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ በመገረም ሲመልሱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሊቃውንት አሏት መዋዕለ ንዋይ ስለሌላት ግን በአፈጻጸም ላይ ፈተና ይገጥማታል። እየኽ ትምህርት ቤት ቆመ ማለት ብቻ ጥቅም የለውም። ከትምህርት ቤቱ ጋር የመማሪያ መጻሕፍት የግዕዝ ቋንቋ ትምህርት ያስፈልጋል።

መንግሥት ከገጠሩ ጀምሮ ትምህርት ቤቶች እያስፋፋ ነው ቤተክርስቲያኒቱ የምትሠራቸው ትምህርት ቤቶች ግዕዝና ግብረገብ መሠረት አድርገው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል። የትምህርት ቤቶች መማሪያ መጻሕፍት ዝግጅትን በተመለከተ የሊቃውንት ጉባኤው ብዙ ሊቃውንት ስለአሉት በቂ በጀትና ድርጅት ሆኖ ከተደራጀ መጻሕፍቶቹን ሊያዘጋጅ ይችላል። በአጠቃላይ ግን የግዕዝ ት/ቤት ራሱ የቻለ ተቋም ሊኖር ያስፈልጋል ሲሉ ነግረውኛል።

በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልእክት መንድነው? ብየ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ፣ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ እንዲህ ይላሉ። ዛሬ ያለንበት ዘመን ፈተና የበዛበት መጻሕፍት ሁሉ እንደሚገልጹት የሕይወት እንቅፋት እንዳለ ጉርፍ፣ የመሬት መሸርሸርና መንቀጥቀጥ፣ እሳት ፍንዳታ የበዛበት ...ወዘተ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ የሕይወት ፈተና የሆነው እንደ ሰደድ እሳት ሕዝቡን እየፈጀ ያለው ኤድስ ነው። ሕዝቡ ይህን አውቆ በሕግ እንዲጠበቅ፣ አንድ በአንድ ተወስኖ እንዲኖር፣ ሕገ እግዚአብሔርን እንዲያከብር ነው። መልእክቴን የማስተላልፈው ሲሉ አባታዊ ምክራቸውን አስተላልፈዋል። ✣





# ጾም በመጽሐፍ ቅዱስ

በሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ዋና ኃላፊ

ጾም ማለት፣ ጥሉላት መባልዕትን ፈጽሞ መተው። ከመብልና ከመጠጥ በመከልከል ሰውነትን መግዛት፣ መቆጣጠር፣ በንስሐ ታጥቦ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ፣ እግዚአብሔርን ደጅ መጥናት፣ ማረኝ ይቅር በለኝ እያሉ የፈጣሪን ምሕረት ለመቀበል መዘጋጀትና የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን በእግዚአብሔር ፊት መምበርከክ ነው። (መዝ. ፴፬፥፲፫፣ ዳን.፲፥፪–፫)።

### ሀ. ጾም በብሉይ ኪዳን

ጾም የሚጾመው ከእግዚአብሔር ሊያገኙት የሚገባ ጸጋንና በረከትን፣ ይቅርታንና ምሕረትን ለማግኘት ነው፤ ሙሴ በደብረ ሲና ፵ ቀን እና ፵ ሌሊት ጾም በአጻብዐ እግዚአብሔር (በግብር አምላካዊ) የተጻፉ ዐሠርቱ ቃላትን ተቀብሎአል። (ዘጸ.፴፬፥፳፰፣ ዘዳ.፱፥፱–፲፪)።

ጾም ጸሎትና ስግደት ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ የሚነጋገሩበት ቋንቋ በመሆኑ፣ በንጽሕናና በቅድስና የሚፈጸም ሥርዓት ነው። (ነሕ.፱፥፩–፫)።

ጾም፣ ከትንኮል፣ ከክፋትና ከመሳሰሉት የሰይጣን ሥራዎች ሁሉ ርቆ ስለ ራስና ስለ ሕዝብ ሥርየተ ኃጢአትን፣ ሰላምንና በረከትን ለመለመን ፊትን ወደ እግዚአብሔር ማቅናት ነው፤ በማለት መጻሕፍት ይገልጹታል (ዳን.፱፥፩–፲፱፣ ፮፥፲፰)።

የጾምና የጸሎት ውጤትም ለዚያ በንጹሕ ልቡና እና በቀና ኅሊና ለሚጾመው ሰው በመላእክት አማካይነት ይገለጻል (ዳን.፱፥፳)።

ጾም ወደ እግዚአብሔር አቤቱታ የማቅረቢያ መንገድ በመሆኑ ያልታሰበ ችግርና ፈተና ሲያጋጥም፣ ሕዝብ እንዲጾም፣ እንዲጸልይ፣ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን እንዲያዋርድ አዋጅ ይነገራል።

«ወሰበኩ ሎሙ ጾመ በኀበ ፈለገ አህዋ ከመ ናሕምም ርእሰነ ቅድመ አምላክነ ወከመ ይሥራኅ ለነ ፍናተነ ወለዉሉድነ ወለኵሉ ፍጥረትነ። በፈጣሪያችን ፊት ሰውነታችንን እናዋርድ (እናሠቃይ) ዘንድ ጐዳናችንንም ያቃናልን ዘንድ ልጆቻችንና ለፍጥረቱም ሁሉ ጐዳናቸውን ያቃናላቸው ዘንድ አህዋ በሚባል ወንዝ ጾምን እንጹም ብዬ አዋጅ ነገርኩኝ» (ዕዝ. ፰፥፳፩፣ አስ.፬፥፫፣ ኤር.፴፮፥፱፣ ኢዮ.፩፥፲፫፥፲፬)።

ወእመ ተስዑ ለጸልመት ውእቱ ወርኅ ተጋብኡ ደቂቀ እስራኤል ወጾሙ፣ ወለብሱ ሠቀ፣ ወወደዩ ሐመደ ዲበ ርእሶሙ...ወቆሙ ወተጋነዩ በእንተ ጌጋዮሙ ወበእንተ ኃጢአቶሙ ...በዚያ ወር ጨረቃ ሠርቅ ባደረገች በዘጠነኛው ቀን የእስራኤል ልጆች ተሰብስበው ጾሙ፤ ማቅ ለበሱ፤ በራሳቸውም ላይ አመድ ነሰነሱ፤ ስለ በደላቸውና ስለ አባቶቻቸውም ኃጢአት ቆመው ሲናዘዙ ሁሉም በየመዓርጋቸው ቆመው የፈጣሪያቸው የእግዚአብሔርን ሕግ አነበቡላቸው፤ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ ተናዘዙ» (ነሕ.፱፥፩–፫፤ አስ.፩፥፲፬–፵፪)።

ጾም ለተርእዮ የሚፈጸም ከሆነ ትርጉሙም ከሊታወቀ ጥቅሙ ይቀራል፤ ይልቁንም ያስከስሳል ያስወቅሳል፤ ያስፈርዳልም። በእግዚአብሔር ዘንድ የተፈቀደ ጾም፤

- የበደለን አሥራት በመፍታት፤
- የቀንበርን ጠፍር በመልቀቅ፤
- የተገፋውን አርነት በማውጣት (በመስደድ)
- እንጀራን ለተራብ በመቁረስ
- የተራቆተውን በማልበስ ነው።

በዚህ ሥነ ምግባር የሚገለጽ ጾም፣ ብርሃኑ እንደ ንጋት ብርሃን በአምላክ ፊት የሚያበራ ውጤትን ያስገኛል። ፈውስንና ጽድቅንም ፈጥኖ ያስገኛል፤ ተብሎ ተጽፎአል። (ኢሳ. ፶፰፥፩–፲፪)።

ጾም የራስን በደል አምኖ ተቀብሎ፣ ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ፣ በድያለሁ ማረኝ በማለት የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለማግኘት የሚረዳ መሣሪያ ነው (ሳሙ.፯፥፰–፮)።

የጾም ጥቅሙና አገልግሎቱ በጥንት ከአበው ጀምሮ በግልጽ የታወቀ እንደ ነበረ ቅዱሳት መጻሕፍት በሚገባ ያስረዳሉ። በሙሴ ዘመን ጾም ብዙን ጊዜ የተገለጸው የተቀደሰ ጉባኤ ወይም ራስን ማስጨነቅ በሚል አነጋገር ነው (ዘሌ.፲፯፥፳፱፣ ፳፫፥፳፯፣ ዘኍ.፳፱፥፯)።

ከዚህ በሕግ ከተወሰነው ጾም ሌላ ደግሞ፣ ጾመ ፈቃድ በሚባል የሚታወቅ የግል ጾም ነበር። ለዚሁም የነቢዩ እግዚአብሔር የቅዱስ ዳዊት ጾም ቋሚ ማስረጃ ይሆናል (ነገ.ካል. ፲፪፥፳፪)።

እስራኤላውያን (ዕብራውያን) የ፬ኛውን ወር

የአምስተኛውን ወር

የሰባተኛውን ወር

የዐሥረኛውን ወር ይጾሙ ነበር። ጾማቸውም የተድላ የደስታና የሐሴት በዓል ነበር (ዘካ.፰፥፲፰–፲፱)።

ይህ ጾም እሥራኤል የተወረረችበትን፣ ቤተ መቅደሱ የተመዘበረበትን በመታሰቢያነት በመጠቀም ነው (፪ኛነገ.፳፭፥፩–፱፣ ኤር.፶፪፥፯–፯)።

### ጾም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው።

«በጽዮን መለከትን ንፉ፣ ጾምንም ቀድሱ፣ ጉባኤውንም አውጁ፣ ሕዝቡንም አከማቹ፣ ማኅበሩንም ቀድሱ፣ ሽማግሌዎችን ሰብስቡ፣ ሕፃናትንና ጡት የሚጠቡትን አከማቹ። ሙሽራው ከእልፍኙ ሙሽራይቱም ከጫጉላዋ ይውጡ። የእግዚአብሔ



www.ethiopianorthodox.org

ርም አገልጋዮች ካህናት ከወለሉና ከመሠዊያው መካከል እያለቀሱ፣ አቤቱ ለሕዝብህ ራራ፣ አሕዛብም እንዳይነቅፉቸው ርስትህን ለማላገጫ አሳልፈህ አትስጥ፣ ከአሕዛብ መካከል፣ አምላካቸው ወዴት ነው? ስለ ምን ይላሉ? ይበሉ» (ኢዩ.፪፥፲፭–፲፯)።

## ጾም እግዚአብሔርን በማገልገል ራስን ለማገልገል የሚፈጸም ሥርዓት ነው

«ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢይት ነበረች። እርሷም ከድንግልናዋ ጀምራ ከባልዋ ሰባት ዓመት ኖረች። እርሷም ሰማንያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና በጣም አርጅታ ነበር። በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር» (ሉቃ.፪፥፴፮–፴፯)።

## ለ. ጾም በሐዲስ ኪዳን

በሐዲስ ኪዳን ጾምን በትእዛዝና በተግባር ያጠናከረልን፣ ለጾማችንም አርአያ የሆነን ክብር ምስጋና ይግባውና አምላካችን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ነው። መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ እከብር አይል ክቡር፣ እጸድቅ አይል ጻድቅ አምላክ፣ ንጹሐ ባሕርይ፣ ሆኖ ሳለ ሠራዔ ሕግ ነውና በመዋዕለ ስብከቱ ጾምን የመጀመሪያ ሕግና ሥራ አድርጎ ጀምሮአል።

ሳይበላ ሳይጠጣ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ሙሉ በመጾም ክብረ ጾምን አስተምሮናል። በመፈተኑም አባታችን አዳምን ድል የነሣ ጥንተ ጠላት ዲያብሎስን ድል ነሥቶልናል። ዲያብሎስን ድል መንሣት የምንችለው በጾም በጸሎት መሆኑን በተግባር አሳይቶ አስተምሮናል።

«ወእምዝ ወሰዶ መንፈስ ገዳመ ለእግዚእ ኢየሱስ ከመ ይትመከር እምዲያብሎስ፤ ወጾመ አርባዓ መዓልተ ወአርባዓ ሌሊተ ወእምድኅረዝ ርኅበ ከዚህም በኋላ መንፈስ (ፈቃዱ) ጌታችን ኢየሱስን ከዲያብሎስ ሊፈተን ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፤ አርባ ቀን አርባ ሌሊትም ጾመ። ከዚህም በኋላ ተራበ...» እንዳለ መጽሐፍ (ማቴ.፬፥፩–፲፩፤ ማር.፩፥፲፪–፲፫፤ ሉቃ.፬፥፩–፲፫)።

ጾም ኃይለ አጋንንትን ያደክማል፤ ጸብአ አጋንንትን ያበርዳል፤ አጋንንትንም ያስወግዳል። «ዝንቱ ዘመድ ኢይወፅእ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት፤ እንዲህ ዓይነቱ ግን (ጋኔን) በጾምና በጸሎት ካልሆነ በቀር አይወጣም አላቸው» (ማቴ.፲፯፥፳፩)።

መድኃኔታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰጠን መመሪያ የምንረዳው ታላቅ ቁም ነገር ጾምና ጸሎት ምን ያህል ዐቢይ ኃያል መሆኑን ነው፣ በሌላ ኃይል ድል መንሣት ያልተቻለን ጠላት በጾም በጸሎት ድል የመንሣቱን ጉዳይ ስንመለከትም፣ የጾምን ረቂቅ ኃይልና ጉልህ ጠቀሜታ እንገነዘባለን።

በእርግጥ፣ ይህን ያህል ታላቅ ክብርና ጸጋ በጾም በጸሎት አማካይነት ከእግዚአብሔር እናገኛለን ስንልም አብሮ መታየት ያለበት አንድ ዐቢይ ቁም ነገር እናገኛለን፤ ይኸውም ከሁሉም በፊት የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ሃይማኖት በልባችን መኖርዋን ማረጋገጥ ነው። ሃይማኖት የሁሉም ነገር መነሻና መሠረት፣ የበረከት የጸጋና የክብር ምንጭ ነው። ለዚህም ነው «አማን እብለክሙ እመ ብክሙ ሃይማኖት መጠነ ኅጠተ ሰናፔ ወትብልዎ ለዝ ደብር ፍልስ እምዝየ ኀበ ከሐ ይፈልስ፤ ወአልቦ ዘይስአነክሙ እውነት እላችኋለሁ የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል ሃይማኖት ካላቹሁ ይህን ተራራ ከዚህ ወደዚያ ተንቀለህ ኺድ ብትሉት ይፈልሳል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም» ተብሎ በመድኃኔዓለም ክርስቶስ የተነገረን (ማቴ.፲፯፥፳)።

## ጾም በሐዋርያት ዘንድ

ጾም ኃይለ መንፈስ ቅዱስ ወይም የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የሚቀበሉበት ኃይል በመሆኑ አበው ሐዋርያት ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ሲሾሙ በጾም በጸሎት ነበር። ለዚሁም መጽሐፍ እንዲህ ይላል «...እነዚህም እግዚአብሔርን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፣ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያ ጊዜም ከጾሙ ከጸለዩም፣ እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው» (የሐ.ሥራ.፲፫፥፩–፫)።

«...በየቤተ ክርስቲያኑም ቀሳውስትን ከሾሙላቸው በኋላ ጾመውም ከጸለዩ በኋላ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡአቸው» (ግብ.ሐዋ.አ፲፬፥፳፩–፳፫)።

## ሐ. ጾም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን

ጾም በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪደን እንዴት እንደሚፈጸምና ጥቅሙና ውጤቱም ምን እንደሚመስል ባጭሩም ቢሆን በግልጽ ተመልክተናል። አሁንም የቤተ ክርስቲያናችን አበው ቅዱሳን፣ የሠሩትን የአፈጻጸም ሥርዓትና በቀኖና ቤተ ክርስቲያናችን አጽዋማት የሚባሉትን እንመልከት።

«ጾምሰ ጸባሕተ ሥጋ ውእቱ፤ በከመ ምጽዋት ጸባሕተ ንዋይ ይእቲ፤ ጾምስ የሥጋ ግብር ነው፤ ምጽዋት የገንዘብ ግብር እንደ ሆነች» (ፍት.ነገ.አንቀጽ ፲፭፥፭፻፷፫)።

በቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና መሠረት አጽዋም፣ «ሰብዓቱ አጽዋማት በመባል ይታወቃሉ። እነዚህም:-

፩. ዐቢይ ጾም

፪. ረቡዕና ዓርብ

፫. ጾመ ነነዌ

፬. ገሃድ

፭. ጾመ ነቢያት

፮. ጾመ ሐዋርያትና

፯. ጾመ ፍልሰታ ለማርያም ናቸው። (ፍት.ነገ.አንቀጽ ፲፭፥፭፻፷፯–፭፻፸፩)።

## ዐቢይ ጾም

ዐቢይ ጾም፣ ክብር ምስጋና ይግባውና መድኃኔዓለም ክርስቶስ የጾመው ጾም ሲሆን ቁጥሩም ፵ ቀን ብቻ ነው፣ ነገር ግን ከዚህ ጾም አብረው እንዲጾሙ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተፈቀዱ አጽዋማት አሉ፣ እነሱም ጾመ ሕርቃልና ሰሙነ ሕማማት ናቸው። እነዚህ ሦስቱ አጽዋማት ሲደመሩ ፶፭ ቀናት ይሆናሉ። በአጠቃላይም ይህ ጾም፣ ዐቢይ ጾም፣ ጾመ ኢየሱስ እና ጾመ ሁዳዴ በመባል ይታወቃል። (ፍት.ነገ. አንቀጽ ፲፭፥፭፻፷፭)።

ከላይ እንደ ተጠቀሰው ፵ው ቀን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጾም ሆኖ ከሱ በፊት ያለው የዘወረደ ሳምንት ጾመ ሕርቃል ይባላል፤ በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ እንደሚታወቀው፣ ሕርቃል ማለት በ፯ኛው ክፍለ ዘመን፣ የቤዛንታይን ንጉሥ የነበረ ታላቅ ሰው ነው። ይህ የዘወረደ ሳምንት በዚህ ታላቅ ሰው ስም እንዲጠራ ወይም ሳምንቱ ለዚህ ታላቅ ሰው መታሰቢያ እንዲሆን የተደረገበት ምክንያትም፣ በዘመኑ የነበረ የፋርስ ንጉሥ ኢየሩሳሌምን መዝብሮ መስቀለ ክርስቶስንና ሌሎችንም ንዋየ ቅዱሳትን ከመውሰዱም ሌላ፣ በክርስቲያኖች ላይ ግፍና መከራ ስላጸናባቸው ክርስቲያኖቹ በደላቸውን ለዚህ ንጉሥ ነገሩት፣ እሱም ስመ እግዚአብሔር ጠርቶ እግዚአብሔርን ጋሻ መከታ አድርጎ ቢዘምትበት ዓመፀኛውን የፋርስ ንጉሥ ድል አድርጎ በክርስቲያኖች ላይ ነፃነትን አወጀ፤ መስቀለ ክርስቶስንም ራሱ ተሸክሞ ወደ ኢየሩሳሌም መለሰ። ክርስቲያኖችም በንጉሥ ሕርቃል አማካይነት ከስደትና ከጥፋት ዳኑ፤ ነፃነትንና ሰላምን አገኙ። በዚህ ምክንያት ይህ ጾም ለሱ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በቀኖና ገብቶ ከጾመ ኢየሱስ ጋር እንዲጾም ተወስኖአል (ፍት.ነገ.አንቀጽ ፲፭፥፭፻፷፯)።

ሦስተኛውና የመጨረሻው የዐቢይ ጾም ክፍልም ሰሙነ ሕማማት ነው። የሰሙነ ሕማማትን ጾም የጀመሩትም ሐዋርያት ናቸው። የሚጾመውም መድኃኔዓለም ክርስቶስ የተቀበላቸውን ጸዋትወ መከራና ነገረ መስቀሉን በማሰብ በመሆኑ፤ በከባድ ስግደት፣ በጽኑ ጾም፣ በብርቱ ጸሎትና በዓንብዓ ንስሐ ሱባኤው ይፈጸማል (ፍት.ነገ.አንቀጽ ፲፭፥፭፻፶፮)።

ጾም ራስን አዋርዶ፣ የግል ኃጢአትን! በደልን! አምኖ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ መዘጋጀት መሆኑ ከታወቀ ዘንድ ኅሊናን በማሸነፍ፣ በተሰበረ መንፈስ የሚፈጸም ሊሆን ይገባል (መዝ.፶፥፲፯)።

በግብዝነት ለታይታ ራስን በውዳሴ ከንቱ ለመካብ፣ ማን እንደኔ በሚል ስንፍና የሚፈጸም ጾም ትርፉ ድካም ብቻ ይሆናል። ተአምኖ ኃጣውእን በማስቀደም፣ ከፈጣሪ ዋጋ አገኛለሁ ብሎ በማመንና ተስፋ በማድረግ መጾም፣ አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን መረዳቱ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው።

«ስትጦሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፉሉ። እውነት እላችኋለሁ። ዋጋቸውን ተቀብለዋል፤ አንተ ግን ስትጦም በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ፣ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ያስረክብሃል» (ማቴ.፮፥፲፮–፲፰፤ ሉቃ.፲፰፥፱–፲፬)።

እዚህ ላይ ኃይለ ቃሉን ስንመለከት ማለትም ራስን የመቀባትና ፊትን የመታጠብ ጉዳይ ሲወሳ መቀባቱና ፊት መታጠቡ በጾማችን ጊዜ ደስተኞች መሆንን፣ ለውዳሴ ከንቱና ለታይታ ከሚፈጸም ዋጋ አልባ ሐሳብ መራቅን፣ ፍቅርንና ትሕትናን ገንዘብ ማድረግን፣ የልብ ንጽሕና ማስቀደምን እንደሚጠበቅብን የሚያስተምረን መሆኑን ልናስተውል ይገባል እንጂ በቅቤና በዘይት ወይም በሳሙና እና በውሃ ስለሚገኝ የፊት ንጽሕና ብቻ ማሰቡና መጨነቁ የሚጠቅመን አይሆንም።

ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ም.፩፥፳፯ ላይ፣ «እመቦ ዘይመስሎ ከመ ዘይትሐረም ለእግዚአብሔር ወኢያለጉሞ ለልሳኑ ወአስሐቶ ለልቡ፣ ለዘከማሁ ከንቱ ሕርመቱ። እንደበቱን ከሐሜት ከፅዕለት፣ ከቧልት፣ ያልከለከለ፣ ልቡናውን ዓለምን ልግዛ ሀብት ላብዛ ከማለት ያልተገታ፣ በሐሜት በፅዕለት በቧልት ያሳተ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ብሎ ትሕርምት የያዘ (የጾመ) የሚመስለው ሰው ቢኖር እግዚአብሔር ያዘዘለትን ምግብ ትቶ የሰይጣንን ምግብ ከተመገበ እንዲህ ያለ ሰው ሕርመቱ (ጾሙ) ከንቱ ነው።

ወሕርመትሰ ንጽሕት እንተ እምኀበ እግዚአብሔር አብ ዛቲ ይእቲ፣ ከእግዚአብሔር አብ ዘንድ የተገኘች ንጽሕት (የምትገባ) ትሕርምትስ (ጾምስ) ይህች ናት ከፈቃደ ሰይጣን ሰውነታችሁን ጠብቃችሁ ሳትጣሉ፣ ሳትሳሱ፣ ሰውነታችሁን ከፍቅረ ንዋይ ከልክላችሁ እናት አባት ያጡ ሕፃናትንና ረጂ ልጅ የሌላቸው ባልቴቶችን በችግራቸው ጊዜ ትረዱአቸው ዘንድ ነው። ሲል የገለጸውን ቅዱስ ያሬድም፣ «ይጹም ዐይን ይጹም ልሳን፣ እዝንኒ ይጹም እም ሰሚዐ ሕሱም በተፋቅሮ» «ማለት፣ ፍቅርን ገንዘብ በማድረግ፣ ዓይን ክፉ ከማየት፣ አንደበት ክፉ ከመናገር፣ ጆሮም ክፉ ነገርን ከመስማት ይጹም (ይከልከል)» ብሏል።

እንግዲህ የጾም ክብሩ፣ አገልግሎቱና ጥቅሙ ከፍተኛ መሆኑን ከተገነዘብን፣ አምላካችን መድኃኔዓለም ክርስቶስ አርብዓ መዓልት አርብዓ ሌሊት ጾሞ፣ በሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ተፈትኖ፣ ማለትም፣ ስስትን በትዕግሥት፣ ትዕቢትን በትሕትና፣ ፍቅረ ንዋይን በጸሊአ ንዋይ፣ ዲያብሎስን ድል እንደነሣልን ሁሉ እኛም ይህን አብነት አድርገን ልንጾም ይገባናል። ጾማችን ዲያብሎስን ድል መንሻ የኃጢአት መደምሰሻ የመንግሥተ ሰማይ መውረሻ ሊሆን የሚችለው ክብረ ጾምን ተገንዝበን በአግባቡ መጾም ስንችል ነው። በንጽሐ ልቡና ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ እሱም ያበራልናል (መዝ.፴፫፥፭)። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# ከወጣቱ ለወጣቱ

## የመናፍቃን ድብቅ ዓላማ ሲጋለጥ

ክፍል ሁለት

በአበበ ዳዊት ከሀገረ ጀርመን ስቱትጋርት ከተማ

ይህ ጽሑፍ ከፈለገ ጥበብ ቁጥር ፳ ገጽ ፳፮ ላይ የመናፍቃን ድብቅ ዓላማ ሲጋለጥ ከሚለው የቀጠለ ጽሑፍ ነው።

በአውሮፓ የሚገኙ ሀገሮች እንዲሁም በአሜሪካ በተለያዩ ሰዎች ላይ በሃይማኖት ስም የተሠራውን ወንጀልና ማታለል መንግሥት አጋልጦታል። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያ ሕዝብ መሃከል፣ በፊት በተለያየ የአምልኮ ስም መጠሪያዎች ወይም (ቤተ ጣኦት) ኡቃቤ ቃልቻ እያለ ሕዝብን ማታለያ መንገድ የነበረ፣ በባህላዊ ደረጃ ተቀባይንትን ያገኘ የሕዝብ ማታለያና ግለሰቦችን እንደ ሮቦት የመጠቀሚያው መንገድ፣ ዛሬ ደግሞ ያበር በመዘጋቱ ሕዝቡ እንደ ገና በሀገሩ፣ ለወገኑ፣ ለቀጣዩ ትውልድ በሃይማኖቱ በባህሉ በቴክኖሎጂ እንዳያድግ፣ በተቃራኒው ደግሞ ወደ ስሕተት መንገድ እንዲሄድ፣ ክርስትና ያለውን ሕዝብ ክርስትናን እንስጥህ በማለት በተለያየ ዓይነት መንገድ ሰዎችን ማስቸገር፣ ሰዎችን ማታለል፣ እንዲሁም ማኸል ሆኖ ደግሞ ቢቻል የተወሰነ ዓመታቶች ሕዝብን በዚህ ዓይነት መንገድ እያታለሉ ለመኖር የሚደረገውን ጥረትና ሙከራ ያሳያል።

ወደ ራሴ ታሪክ ልመለስና በእኔ ላይ ካላገባህ ተብዬ በተኛሁበት በክፉ መንፈስ እድስቃይ ከተደረገ በኋላ በጣም በመታመም እነሱ የሚፈልጉትን ጋብቻ እንድፈጽም የተደረገው ማስፈራራትና ዛቻ ሕዝብ በመስማቱ እና በእኔ ላይ የደረሰው የማሰቃየትና የማስጨነቅ ተግባር መልኩን እየቀየረ የመጣ ሲሆን፣ ምንም እንኳን ሁሉንም ነገር ሰይጣን ይሆናል ያደረገው ማለት ቢቻልም፣ ማንም ሰው ዓላምንም፣ አልቀበልም፣ አልከተልም፣ ባለ ቁጥር በማሳመም በኃይል እንደ ተደረገ ሁሉ የእኔም ስቃይ እየቀጠለ መጣ። በዚህ ወቅት ነበር አንዳንድ ኢትዮጵያውያን በስቱትጋርት የሚኖሩትን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን ወንድሞቼ ችግሬን ደረጃ በደረጃ በመንገር፣ በጀርመን ሀገር ወደምትገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመመለስ ሂደቱን እየጀመርኩ መጣሁ። የመመለሱ ሕይወት በጀመርኩበት ጊዜ ማለትም ወደ መናፍቃን እምነት ገብቼ የደረሰብኝን መከራና ሥቃይ ለወገኖቼ ከነገርኳቸው በኋላ በአጠቃላይ ወደ ሕዝብ ጆሮ ደረሰ።

ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ወንድማዊና እኅታዊ ፍቅራቸውን አሳዩኝ። በሃይማኖት ስም የደረሰብኝን መከራና ስቃይ ለመናገር በመቻሌ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ።

ከነዚሁ ከመናፍቃን ከወጣሁ በኋላ ያለውን ሕይወቴን እንዴት እንደነበርና በምን ሁኔታ ላይ እንደ ምገኝ ለማካፈል እወዳለሁ። ከመናፍቃን ድርጅት የለቀቁት እነሱም እንደሚያውቁት በማጭበርበር በሐሜት ወይም በሌላ መንገድ ሳይሆን ጉዳዩ ከኢትዮጵያ በሚገኙ ቤተሰቦቼ፣ በእኔ ላይ በሚደረገው ማስፈራራት እየከፋና እየጨመረ ሲመጣ፣ በወቅቱ እኛ የኢየሱስ አማኞች ነን በሚሉ ሽማግሌዎችን ሰብስቦ በማነጋገርና የድርጅቱ ዋና ኃላፊ ጋር በመገናኘት፣ በግልጽ ካላገባህ ብሎ ችግር መፍጠር ምን የሚሉት ነው? በማለትና እንዲሁም ሌሊት እንቅልፍ እየነሳ የሚያስቸግረኝን በእግዚአብሔር ስም ሰበብ እየደረሰብኝ ያለውን ሁኔታ ከምን የመጣ እንደሆነ ጠየቅሁት።

እርሱም በእነሱ ሽማግሌዎች ከሚሏቸው ጋር ተሰብስቦ ከተነጋገሩ በኋላ እኔንም ቀጥረውኝ አብረን ተሰብስበን ከተነጋገርን በኋላ እንግዲህ ለአንድ ሳምንት ጾም ጸሎት ይዘን ከእግዚአብሔር ከተናገርን በኋላ የሚሆነውን እናደርጋለን። አሉኝና ለሳምንት ቀጠሩኝ። በቀጠሮውም ቀን ሂጄ እንዴት እንደ ሆነ ጠየቅኋቸው፣ በእርግጥ በአንተ ላይ ያለው ችግር እዛ ቤተ ክርስቲያን እያለህ ያልተወገደልህ ቢሆንም፣ አሁንም በድጋሚ በነገሩ እንጸልይበታለን ብለው ቀጣይ ቀጠሮ ሰጡኝ። በቀጣዩ የቀጠሮ ቀንም ሂጄ ዋና የሚባሉት ሌላ የምትሉኝ ነገር አለ? ብዬ ስጠይቃቸው ያንኑ የተለመደውን ጌታ ይፈታዋል፣ ጌታ ያድንሃል፣ ጌታ ይፈውስሃል፣ በማለት ሲጸልዩልኝ ነገሩ ሁሉ ስላልተዋጠልኝና ልድንም ስላልቻልኩ፣ በእነሱ እምነት መቀጠል እንደ ማልፈልግ በመንገር የወጣሁ ሲሆን፣ በምወጣበትም ሰዓት የቤተ ክርስቲያኑ አንድ ኃላፊ እግዚአብሔር በሕልም ወደ አንተ ጋር ልኮኛል፣ አንድ ሚስትም ሰጥቶሃል። አንተ ግን በልብህ ሌላ ነገር አስበሃል፣ ይህንንም ብታደርግ ችግርና አደጋ ይገጥምሃል፣ እኔ የተናገርኩትን ነገር እግዚአብሔር ይፈጽመዋል የሚል ያው የተለመደውን የማስፈራራት ቃል የተናገረኝ ሲሆን። እኔም በዚያ ወቅት ለምትገኘው እህት የእግዚአብሔር ቤት የፍቅር የርኅራኄ እንጂ እግዚአብሔር ሚስት ካላገባችሁ እገላችኋለሁ እያለ የሚያስፈራራ አምላክ አይደለም፣ በማለት ከዚያ ቀን ጀምሮ ወደ እነሱ መሄዴን በማቆም በሽቱትጋርትና አካባቢ በሚኖሩ ሰዎች ግንኙነት በማድረግ በጀርመን በምትገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የሚያስፈልግውን የንስሐና ከስህተት መንገድ ወደ እውነት መንገድ የሚመልሰውን ትምህርት ተምሬ ዛሬ የነገርኋችሁን ችግር ሁሉ ተወጥቼ በመልካም ሁኔታ ላይ እገኛለሁ።

እኛ እግዚአብሔር ነን የሚሉት ሰዎች ተማሪዎችን ከትምህርታቸው፣ ሠራተኞችን ከሥራቸው፣ ወጣቶችን በደካማ ጐናቸው እየገቡ በማሳበድ (እራሳቸውን እንዲስቱ) በማድረግ፣ በሃይማኖትም እየመጡ ያሉትን ሰዎች በፈርድ ቤት እንደ ሌባ ተጋልጠው የተባረሩና ማንነታቸው የታወቁ ብዙ ድርጅቶች በፊት ይመሯቸው የነበሩ የእነዚህ ዓይነት መሪዎች መጨረሻ በነበሩበት ጴንጤ ቆስጤ ብለው መሄድም ስለሚያቅታቸው እኛ (Dinomination) የለንም ብለው ማንነታቸውን ለመደበቅ የሚጥሩ ሲሆን በእኛም ሀገር በሰፊው በመሠራጨት ላይ መሆናቸውን ሊታወቅ ይገባል። ሕዝባችንም ራሱንና ወገኑን ከመናፍቃን ሤራ መጠበቅ ይገባል። ዛሬ በቸልተኝነት የታለፈ ነገ የሀገርንና የቤተ ክርስቲያንን ነቀርሳ ይሆናል።

እግዚአብሔር ትዳር ካልያዝክ ብሎ ሰውን የሚያጠፋ አምላክ አይደለም፣ ይህ ተግባር ሰዎች ከራሳቸው (ከልቦናቸው) ያመነጩት የግል ሐሳብ እንጂ የአምላክ ትእዛዝና መመሪያ አይደለም። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በዓለማችን ብዙዎች እንደ እነዚህ የመሰሉ አታላዮች የተፈረደባቸው የተቀጡ በተለይም በምዕራቡ ዓለም በስፋት ማንነታቸው ጐልቶ በመንግሥት ደረጃ አስፈላጊውን ቅጣት እያገኙ መሆናቸውን ዕለት በዕለት የምንሰማው ጉዳይ ሆኗል። ዛሬ በሀገራችን በኢትዮጵያ ብዙዎች እራሳቸውን መከላከል የማይችሉ፣ የሚደረግባቸውን የማያውቁ፣ ብዙ ወገኖቻችን በሃይማኖት ሰበብ የመናፍቃን ጥቃት ተጠቂ ሲሆኑ፣ ለዚህ ጥያቄ በዋናነትና በግንባር ቀደምትነት እየታገለች ያለች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት።

፩. መናፍቃኑ የሚንቀሳቀሱት ከራስ ጥቅም አኳያ ነው። ይኸውም በአብዛኛው የመናፍቃን አባላት የሚያደርጉት ታላቅ አደርግሃለሁ የሚለው ሲሆን፣ ይህ ቃል ማንም ሰው ታላቅ የሚሆን ሠርቶ የማግኘት፣ የማደግ፣ ራሱን የመምራት፣ ቤተሰቡን የማሳደግ፣ የማስተዳደር ፍላጐት አለው። ይህ የሰው ልጅ መሠረታዊ የሆነ ፍላጐት እግዚአብሔር መሥርቶ ያስቀመጠው ሆኖ ሣለ፣ ዛሬ በሀገራችን የኢኮኖሚ ችግር እፈታለሁ፣ በማለት ሃይማኖቶች እራሳቸውን እያስፋፉ ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ የውጭ እድል እንድታገኝ ወረቀት እሰጥሃለሁ፣ ከበሽታ እፈውስሃለሁ፣ በሚል ማጭበርበር ከመነጠቅ አውቆ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

፪. ዛሬ በዓለማችን እንደምናውቀው ከአንድ ቡድን አንድ ሰው ወጥቶ ቢሄድ ምስጢራችንን ያወጣብናል፣ ለሕዝብ ማንነታችንን ያሳውቃል። በማለት ያንሰው እንደሚያሳድዱ ሁሉ ከእነዚህ ከመናፍቃንም ድርጅት አንድ ሰው ወጥቶ ቢሄድ የዚሁ ዓይነት መከራና ስቃይ ይደርስበታል። ምክንያቱም ምስጢራቸውን ስለሚያወጣባቸው ወደ ሕዝብ ጆሮ ስለሚያደርስባቸው ቀን ጠብቀው የመግደል ሙከራ የማድረስና የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም ለማጥቃት ወደ ኋላ አይሉም።

፫. በዓለማችን ያሉ መናፍቃን ታሪክ አያውቀንም ማንነታችንን አይታወቅም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ በዚህ አሰራር እንሠራለን፣ ይህ አሰራር ደግሞ ሲታወቅ ሌላ ዓይነት የአሠራር ስልት እንከተላለን፣ ወይም በአንድ ወቅት በበጴንጠ ቆስጤ የሃይማኖት ድርጅት በኃላፊነት ቦታ ሲሠሩ የነበሩ በጀርመን በአሜሪካ ወዘተ በአስራት፣ በኵራት ከሕዝቡ በሚሰበስቡት ገንዘብ ሀብታም ሲሆኑና ኑሮአቸውን ሲያመቻቹ ትንሽ ቆየተው በኋላ ላይ ምስጢሩ ሲጋለጥ በሕዝብ ፊት በወንጀል ተከሰው በሃይማኖት ስም በማጭበርበራቸው ፍርድ ቤት እየቀረቡ ሲፈረድባቸውና ሕግ ሲጠይቃቸው እኛ (Dinomination) የለንም እያሉ ሲያታልሉ፣ ያም አላስኬድ ሲላቸው አካባቢና መኖሪያን በመቀየር በሰበሰቡት የሕዝብ ገንዘብ የተለያዩ እንዱስትሪዎችን በማቋቋም የግል ጥቅማቸው ሲያሳድጉ ይታያሉ። ይህ እንግዲህ እኛ የእግዚአብሔር ወገን ነን የሚሉ ነገር ግን እግዚአብሔርን የማያውቁና ፍቅሩም እምነቱም እንደሌላቸው ያመለክታል።

እንግዲህ ምዕመናን ሁሉ ማወቅ ያለባቸው ነገር ቢኖር የእግዚአብሔርን የከበረ ሥራ በረከሰ ምግባር የሚያጠፉትን ሁሉ ለይቶ፣ አውቆ ሁሉም እራስን ቤተሰቡን አካባቢውን እንዲጠብቅና እንዲጠነቀቅ ማንም ተፈወሰ፣ ዳነ፣ ከሞት ተነሣ፣ ቢላችሁ ለምትሐታዊ ሥራ ሳትደነቁ እራሳችሁን እየጠበቃችሁ ከእናት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር ሆናችሁ እምነታችሁን እንድታጸኑ በቅዱሳን አምላክ በእግዚአብሔር ስም አሳስባችኋለሁ። በአደባባይ ቆሜ ይህንን የምስክርነት ቃል እንድሰጥ የፈቀደ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን። ✣

www.ethiopianorthodox.org

# ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

## «ዕድሜአችሁ እንዲረዝም እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ጠብቁ»

ከመጋቢ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



ለዚህ ርእስ መነሻ የሆነኝን ሙሉ ንባብ እንደሚከተለው አነባለሁ።

«እግዚአብሔር አምላካችሁ ያዘዛችሁን ጠብቁ። ከትእዛዙ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ አትበሉ። በሕይወት እንድትኖሩ፣ መልካም እንዲሆንላችሁ፣ በምድርም ላይ ዕድሜያችሁ እንዲረዝም እግዚአብሔር አምላካችሁ ባዘዛችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ።» (ዘዳ.፭፥፴፪–፴፫)

እግዚአብሔር መሐሪና ሩኅሩኅ ስለሆነ የሰው ልጅ በጤናማ ሕይወት እንዲኖር እንጂ በሕማምና በስቃይ እንዲኖር አይሻም። ምን ጊዜም ቢሆን ደስታውን እንጂ ኀዘኑን፣ መከራውንና ጭንቀቱን አይፈቅድም።

በመሆኑም እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ከሕማምና ከሥቃይ፣ ከኃዘንም ከሞትም ነፃ አድርጎ ፈጠረው። ይህንም እውነት ከብሉይ ኪዳን እንደሚከተለው አነባለሁ:-

«እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረም፤ የሰዎች ጥፋት ደስ አያሰኘውም፤ ሕያው ሆኖ ይኖር ዘንድ ሰውን ፈጠረ፤ የዓለም ተፈጥሮ ለሕይወት ነበረ። በውስጡም የጥፋት መርዝ (በሽታ) አልነበረም። ...ነገር ግን ሰዎች ራሳቸው ሞትን በእጃቸው (በቃላቸው) ጠሩት። ወዳጅም አስመሰሉት። በእርሱም ጠፉ። (ጥበበ ሰሎሞን ፩፥፲፫–፲፮)

የሰው ልጅ ስለ ሕይወቱ የተሰጠውን የሕይወት መመሪያና ትእዛዝ በመተላለፍ ራሱን በራሱ ለሕማምና ለሞት ዳርጓል። በተድላና በደስታ እንዲኖርባትና እንዲጠብቃት፣ እንዲንከባከባትም የተሰጠችውን ምድር እንድትረገምና በጭንቀት እንድትሞላ አድርጓታል። ለረዥም ዕድሜ እንዲኖር የተሰጠውንም ሕይወት አበላሽቷል፤ ዕድሜውንም አሳጥሯል።

ይሁን እንጂ ሰው በራሱ ላይ ይህን ሁሉ ችግር ቢያመጣም ሕይወቱ እንዲታደስ፣ ተስፋም እንዳይቆርጥ የተለያዩ ማስጠንቀቂያና ማጽናኛ መመሪያዎች ከእግዚአብሔር ተሰጥተውታል። ከእነዚህም አንድ መመሪያ ትእዛዝ:-

«ዕድሜያችሁ እንዲረዝም እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ጠብቁ» የሚለው ነው።

በመሠረቱ የሰው ልጅ ዕድሜ በጣም ረዥም ነበረ፣ ስምንት መቶና ዘጠኝ መቶ ዓመታት የኖሩ ሰዎች እንደ ነበሩ ተጽፏል። ከዚያም በኋላ የሰው ልጅ ዕድሜ ወደ መቶ ሃያ፣ ወደ ሰማንያና ሰባ አቆልቁሏል፤ ይህንም የሚኖሩ በጣም ዕድለኞች ናቸው፤ ዛሬ ደግሞ የሰው ልጅ ዕድሜ ከወራት ጀምሮ እስከ ሃያ ዓመት ብቻ የሚቆጠር እየሆነ መጥቶአል። እግዚአብሔር አምላክ ግን «ዕድሜአችሁ እንዲረዝም ትእዛዜን ጠብቁ» ይላል።

የእግዚአብሔር ትእዛዝ:-

«አታመንዝር፤
አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ይጽና
አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ትጽና፣
ከጋብቻ በፊት፣ በጋብቻም ላይ
ከዝሙት ራቁ» ይላል።

ዛሬ በዓለም ላይ እንደ ሰደድ እሳት የተቀጣጠለው የ(H.I.V.) ኤድስ በሽታ መነሻ ምክንያቶች ብዙዎች እንደሆኑ በሀዋቆች ቢነገርም ዋናውና አውራው ምክንያት:-

አንድ ለአንዲት አለመወሰን፣ የጋብቻን ክቡርነት በማቃለል ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በአመንዝራነት መኖርና ሌላም ሕገ ወጥ የሆነ ግብር መፈጸም ነው።

ሰዎች ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ከውጭ በሚገፋፋ ሌላ ኃይል ሳይሆን በራሳቸው ነጻ ፈቃድና ስሜት መሆኑ ግልጥ ነው።

እግዚአብሔር:- ማንኛውንም ፍጥረት ያለ ስሜት አልፈጠረውም። ሁሉም ተቃራኒውን ለማግኘት ስሜትና ፍላጎት አለው። ሰው ይህን ስሜት ራሱ በራሱ ነፃ ፈቃድ ለመግታት ሥልጣን ተሰጥቶታል። ይህን ለማድረግ ካልቻለ ግን እጅግ በከፋ አደጋ ላይ ይወድቃል፤ እየወደቀም ነው።

ሰው ነፃ ስሜቱን በነፃ ፈቃዱ ለመግታት ሳይችል ቀርቶ በአደጋ ላይ በወደቀ ጊዜ በእግዚአብሔር ማንጎራጎር ወይም እግዚአብሔር ከዚህ አደጋ እንዲያድነው መለመን ለምን ስሜተቢስ አድርገህ አልፈጠርኸኝም? ማለት ይሆናል።

እግዚአብሔር ግን ሁሉንም:- ስሜትንና ስሜትን የመግታት ሥልጣንን አስተካክሎ ስለሰጠው የሰው ልጅ ሁሉንም በአግባቡ ለመጠቀም መቻል አለበት።

እርግጥ ነው የወንድና የሴት መፈላለግ እግዚአብሔር የፈጠረው ስሜት በመሆኑ እንደ ኃጢአት አይቆጠርም፤ ነገር ግን ይህን ስሜት በማይገባ መልኩ መጠቀም ሕገ እግዚአብሔርን መተላለፍ ስለሆነ በተፈቀደው የጋብቻ ሥርዓት ሊፈጸም ይገባዋል።

«...በቃልና በምግባር፣ በፍቅርና በሃይማኖት፣ በንጽሕናም ለምእምናን ምሳሌ ሁናቸው» የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር በመከተል በዚህ አስጊና አሰቃቂ በሆነው የኤድስ ዘመን የሚኖሩ ወጣቶች ሁሉ ክቡር ድንግልናዊ ሰብእናንና ንጹሕ ልብን ይዘው ወደ ቅዱስ ጋብቻ መቅረብ አለባቸው።

ያላገቡ ወንዶችና ሴቶች ጋብቻ በሙከራ የሚደረግ ሥርዓት አለመሆኑን ተገንዝበው ከጋብቻ በፊት ንጽሕናቸውን በመጠበቅና በመተማመን ቅዱስ ጋብቻቸውን መመሥረት ያስፈልጋቸዋል። ይህንም ማድረግ ያለባቸው በሽታን በመፍራት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን በመፍራትና በማመን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በማክበር፣ ምክረ ካህን በመስማትም ነው።

ሁላችንም የምናውቀው አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አለ፤ ይህም የማየ አይኅ (የጥፋት ውኃ) ታሪክ ነው።

የሰው ልጆች ኃጢአት በበዛ ጊዜ እግዚአብሔር በምድር ላይ የጥፋት ውሃን አዘነበ፣ በዚያም የጥፋት ውሃ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ መርከብ የሠሩ ስምንት ሰዎች ብቻ ሲተርፉ ያን ጊዜ የነበሩ የሰው ልጆች ሁሉ ተደመሰሱ። እነዚያም ስምንት ሰዎች አራቱ ወንዶች አራቱ ሴቶች ነበሩ። ይህም ቁጥር የሚያመለክተን «አንድ ለአንድ» የሚለውን ሕገ እግዚአብሔርን ነው። ያን ጊዜም ሆነ ዛሬ አንድ ለአንድ ለሚለው የከበረ ሕግ ሁል ጊዜ የሚጠቀሱ እነዚያ ስምንት ሰዎች ናቸው። ከጥፋት ውሃ በኋላ የሰው ዘር ሊበዛ የቻለው ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው ከተገኙት ከእነዚያ ከስምንቱ ሰዎች ብቻ ነው።

እነሆ ዛሬም በዘመናችን የምንኖርባት ዓለም በከባድ የጥፋት ማዕበል እየተናጠች ናት። የዓለም ሕዝቦችም በጥፋት ውሃ ዘመን እንደ ነበሩት ሰዎች በማዕበሉ እየተገፉ ናቸው። እየሰጠሙም ናቸው። ይህ ማዕበል ዓለምን በስጋት ላይ የጣለው፣ ቀሳፊው የኤድስ በሽታ ነው።

ማየ አይኅ በአንድ አካባቢ ብቻ እንዳልወረደ፣ የተለያዩ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም እንዳጠፋ ይህ ቀሳፊ በሽታም የወረደው በአንድ አካባቢ ብቻ አይደለም፤ በአፍሪቃችን ብቻ አይደለም፤ በኤሽያም ብቻ አይደለም፤ በጠቅላላ የሰው ልጆች የሚኖሩበትን ዓለም ሁሉ እየወረረ መሆኑ ተረጋግጦአል።

እንግዲህ ከሁሉም አቅጣጫ እንደሚሰማው በዓለማችን የሰው ዘር እንዲተርፍ እንደ ስምንቱ ሰዎች በሕገ እግዚአብሔር መጽናት አስፈላጊ መሆኑን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የጽድቅ ሰባኪ እንደ ተባለው እንደ ኖኅ ለትውልዱ ድምፅዋን ታሰማለች።

ዛሬ በዚህ መቅሠፍት ከመመታት የሚያድን ሌላ መርከብ የለም። ዓለም ቢባል አስተማማኝ አለመሆኑ እየተነገረ ነው። ሁሉም ከዚህ ቀሣፊ በሽታ ለማምለጥ የሚችልበት መርከብ ሕገ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ስለዚህ ሁሉም ወደ መርከቡ ወደ ሕገ እግዚአብሔር ይግባ፤ «ዕድሜአችሁ እንዲረዝም እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ጠብቁ» የሚለውን ትእዛዝ ይስማ!

ቤተ ክርስቲያን ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ብቻ ሳይሆን ከሞት በፊት ስላለው ሕይወትም ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ዘወትር ታስተምራለች። ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው፤ ስለሆነም ቅዱስና ንጹሕ እንዲሆን ያስፈልጋል።

የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የቤተ ክርስቲያን ተግሣጽና ምክር ጤናማዎች ከበሽታው እንዲጠነቀቁ ብቻ አይደለም። ለበሽተኞችም ጥንቃቄና እንክብካቤ እንዲያደርጉላቸው፣ አስፈላጊ የሆነውንም አገልግሎት እንዳይነፍጓቸው ትመክራለች። ጤናማዎች የኤድስ በሽተኞችን ከመተቸት ይልቅ እንዲያዝኑላቸውና እንዲራሩላቸው፣ ከሌላውም ኅብረተሰብእ ተለይተው ይቅርታ የማይገባቸው እግዚአብሔር ከሌላው ለይቶ የረገማቸው ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ አድርገው እንዳይመለከቱአቸው መገንዘብ እንደሚገባ ታስተምራለች።

ቤተ ክርስቲያናችን ለበሽተኞችም የምታስተላልፈው መልእክት አላት:- ጤናማዎች በሽተኞችን ማፍቀርና መንከባከብ እንደሚገባቸው፣ በሽተኞችም ጤናማዎችን ሊያፈቅሩ ይገባል።

በማናቸውም መተላለፊያ መንገዶች የበሽታው ተጠቂዎች በሽታው በራስ ብቻ እንዲያበቃ፣ ሌላው በእነሱ በሽታ እንዳይጠቃ መጠንቀቅና ማስጠንቀቅ ታላቅ ፍቅር መሆኑን ሊያውቁ ይገባል። በሽታው ከእነርሱ ወደ ሌላው እንዳይተላለፍ ከማድረግ የበለጠ ፍቅር ፈጽሞ የለም። ይህንም ሁሉ ማድረግ የሚቻለው ሁሉም ለእግዚአብሔር ሕግ ተገዢ ሲሆን ነው። ስለሆነም:-

«ዕድሜአችሁ እንዲረዝም እግዚአብሔር የሚያዝዛችሁን ጠብቁ» የሚለውን ሕገ እግዚአብሔር ሁሉም ያክብር። አሜን።

በኤች አይ ቪ. ኤድስ በመያዝ ምክንያቶች ከሆኑት ነገሮች አንዱ ሰው ሊታገሠው የማይችለው በተፈጥሮው ውስጥ ያለ ጾታዊ ጠባይዕ ነው ይህን ጠባይ ለመለወጥ በየጊዜው የሚሰጠውን ትምህርት፣ ምክርና ተግሣጽ መቀበል ያስፈልጋል።

አኩቴት ለእግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

# መግረሬ ፀር

ይህ ዓምድ መናፍቃንንና ስጽራረ ቤተክርስቲያንን የሚያጋልጡ ጽሑፎች የሚቀርቡበት፣ የአመቤታችን፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ አማላጅነትና ተራዳኢነት የሚተነተንበት ስለሆነ መግረሬ ፀር ተባለ።

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ርእስ መነሻነት ስለመንፈሳዊ አገልግሎት ሰፊ ትምህርት የሆነውን በአጭሩ ነጥቦቹን በረድኤተ እግዚአብሔር አጋኝርነት ቀርቧል።

አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሚሾመው (የሚመረጠው) ምዕመኑን በቅንነት ጎንበስ ቀና ብሎ በትህትና እንዲያገለግል ነው። ትህትና እስከ መሬት ነው እንዲሉ አበው ማር.፫፥፲፫ የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ እነርሱም ሄዱ ይለናል። እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሲጠራን እርሱ የጠራን እኛ ከማንም በላይ ጻድቅ ስለሆንን ሳይሆን ከቸርነቱ ብዛት የተነሳ ስለ ወደደን እንድናገለግለው (በእኛ ለመመስገን) ፈቃደኛ ስለሆነ ነው። ሐዋርያትንም ለእርሱ እንዲሆኑ ከጠራቸው በኋላ የመረጣቸው ወንጌልን እንዲሰብኩ ብቻ ሳይሆን አብረው ለዘለዓለም ከርሱ ጋር እንዲኖሩም ጭምር ነበር። (ማር.፫፥፴)።

ወደ አገልግሎት ስንመለስ ዛሬ ሰዎች እጅግ አቅቶን በቤቱ መቀመጥ እንደ ኮሶ መርጋን ገሚሱ እንደ ይሁዳ ሲክድ፣ ገሚሱ እንደ መናፍቃን ኑፋቄ ሲዘራ፣ ገሚሱ ደግሞ እንደ ዴማስ እኔ ምን ገዶኝ ሲል አለምን የሙጥኝ ብሎ ቤተ ክርስቲያን ላለመምጣት ምክንያት ደርዳሪ እየሆነ ይታያል። ዛሬ ዛሬማ ኑ ሰ/ት/ቤት ተማሩ ሲባል ሥራ ይበዛብኛል፣ አይመቸኝም...ወዘተ የሚለው መብዛቱ። ለመሆኑ ቤተ ክርስቲያን የሚሄደው ሰው ሥራ ፈት ነውን? ክርስትናም ደግሞ ሲመችም ሳይመችም ነው በማር.፲፥፵፭ ላይ እንደ ተገለጸው ማንም ሰው ለአገልግሎት ሲጠራ ለሥልጣን እንዳልሆነ ይልቁንም መከራ መስቀሉንም ሊሸከም ጭምር መሆኑን መረዳት አለበት።

## አንድ የሰ/ት/ቤት አገልጋይ ከማገልገሉ/ሏ በፊት ሊያሟላው (ልታሟላው) የሚገባ ነገር ቢኖር፣

፩. ዓላማ ሊኖረው(ራት) ይገባል። ያለ ዓላማ አገልግሎት መጀመር ልክ በባህር እንደ ተለቀቀ ኩበት መሆን ነው። ለምሳሌ በገ.ሐዋ.፱፥፩ ጀምሮ ታሪኩ የተነገረለት ቅዱስ ጳውሎስ ለወንጌል ዓላማ ከተጠራ በኋላ ትልቅ ዓላማ ነበረው። ይኸውም የእግዚአብሔር ስም በአህዛብ እንዳይሰደብ ታላቅ ቅናትና ዓላማ ነበረው። ይህም ብቻ ሳይሆን ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ በ፪ኛ ቆሮ.፲፩፥፳፱ እንደ ተጠቀሰው ለሚያገለግላት ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ፍቅርና ቅናት ነበረው እለት እለት የአብያተ ክርስቲያናት ነገር ያሳስበው ነበር። ማነው ዛሬ ለሚያገለግላት ቤተ ክርስቲያን ፍቅር ያለው? ስሙ በኢአማንያን፣ በመናፍቃን ጭምር ሲሰደብ ቤተ ክርስቲያን ወራሪዎች በዝተው እጃቸውን ሲቀስሩ እጃችንን አጣምረን የምንገስቅ ትውልዶች ሆንናል። ሌላው ቅዱስ ጳውሎስ ከዚህ ሁሉ የተነሳ የመጨረሻ ዓላማው ሰማያዊትን ኢየሩሳሌምን የመውረስ ጽኑ ዓላማ ነበረው። (ፊል.፫፥፲፰) በዚህ ሁሉ ምዕራፍ ያየነው የክርስትናን ጉዞ የጀመርን በአገልግሎት ያለን ሁሉ በስሜት ሳይሆን ዓላማ ሊኖረን ይገባል።

ይኽ ሁሉ እንዳይሆን ለአገልግሎት የመጣ አገልጋይ ሊያጤነው የሚገቡ ቁም ነገሮች

፪. ማንን ነው የማገለግለው? መዝሙሩ አጥኑ እንዘምርም፣ ወንጌል ኑ ተማሩ አን ታዘዝም ወይም ደግሞ እከሌ ለምን ያዘኛል ከማን በልጦ? እከሌ ቢሆን ግን እሄድ ነበር... ወዘተ እንዲህ ዓይነት ሰዎች የሚያገለግሉት ማንን እንደ ሆነ ገና ያልተረዱ እናም የሚያገለግሉትም ሰውን እንጂ እግዚአ ብሔርን እንዳልሆነ መረዳት ይገባቸዋል። ማንን እንደሚያገለግል የተረዳው ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ሞትም ሕይወትም ለእኔ ምንም አይደለም ይል ነበር። ለምን ማንን እንደ ሚያገለግል ያውቅ ነበርና በዚህም ልሄድ እናፍቃለሁ ካለ በኋላ ለወንጌል (አገልግሎቱን) ስል ከእናንተ ጋር መኖርን እናፍቃለሁ ይል ነበር። ዛሬ ሰዎች ትንሽ የመከራ ንፋስ በነፈስ ቁጥር የሚያስፈራው የሚያገለግሉትን ባለማወቃቸው ነው።

፫. ለምንድነው የማገለግለው? ለምን እንደሚያገለግል የማያውቅ ሰው ሁል ጊዜ አስቸጋሪ ነው። ስብሰባ ቢጠራ አይመጣም። ቢመጣም ለምን እንደሚሰበሰብ ስለማያውቅ አቋርጦ ይሄዳል። ዛሬ ምዕመናን ለምንድነው የምናገለግለው ሲባል የመጀመሪያው ለራሳችን በረከት ለማግኘት እንጂ እግዚአብ ሔር እኛ ባናገለግለው አይጎዳም ብዙ አገልጋይ አለው።

፬. እስከ መቼ ነው የማገለግለው? ብዙ ጊዜ (በተለይ) ለአገልግሎት ስንመጣ ሰ/ት/ቤት እስከ ፲፪ኛ ክፍል ድረስ ብቻ ሲያገለግሉ ይታያል፤ እነርሱም የበረቱት ናቸው። በርግጥ ከዛም በላይ ብዙ ጊዜ እድሜያቸውን የኖሩበት ሊኖሩ የቻላሉ። አገልግሎት ታዲያ ለ፫ ወር? ለ፩ ዓመት? ለ፲፪ ዓመት? እስከ መቼ ነው ማገልገል ያለብን ያልን እንደ ሆነ በሰ/ት/ቤቶችም መድረክ ሆነ በማንኛውም መንፈሳዊ ጉዞ መልሱ (ራእ.፪፥፲) እስከ ዕለተ ሞት ነው። አባቶች መጀመር እያስመሰግንም መፈጸም እንጂ ይላሉ (ሰ... ፍጻሜውን ሳታይ አታመስግነው) ጌታም እስከ መጨረሻ የሚጸና ይድናል አለ እንጂ እስከዚህ ዓመት (ወር) የቆየ አላለም።

አንድ አገልጋይ ለመመረጥ ሊኖረው የሚገባው ነገሮች

፩. ትህትና (ማቴ.፲፥፴፰) መስቀሉን ይዞ ይከተለኝ ራሱን ይካድ የሚሉ ቃላት እናገኛለን። ከዚህ ምንባብ እንደምንረዳው መስቀሉን ለመሸከም ራስን መካድ ለዚህ ደግሞ ትሁት መሆን የግድ ነው። አልያ ትህትናን ጥለን በዓለም ያለንን ፀባይ ይዘን ከመጣን ከመንገድ ወድቆ መሰበር አለ እና እናስብበት። በአገልግሎት ጸጋ ያስፈልጋል ለምን በግድ ካላደረግሁ ካልፈጸምኩ ማለት ጸጋው ሳይሰጥ አይቻልም። መጥምቁ ዮሐንስም ሲሰብክ እርሱ ማን እንደሆነ ሲጠይቁት እኔ የጫማውን ጠፍር እንኳ ልፈታ የማይገባኝ አለ። እቤት እኛ ብንሆን እንደ መጥምቁ ማን እንበላችሁ? ተብለን ቢሆን ኖሮ መልሳችን እበልጣለሁ እንጂ አንሳለሁ የሚል ትውልድ ዛሬ መቼም የለም። እና ትህትና አስፈላጊ ነው።

## እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን

### የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ። ራእ.፪፥፲

፪. ታማኝነት (ማቴ.፳፭፥፲፬) በተሰጠን አገልግሎትተጠቅመን ከታመንን የተሻለ ይሰጠናል ቅዱስ ዳዊት በጎችን በሥነ ሥርዓት ስለጠበቀ የእግዚአብሔርን በጎች እስራኤልን እንዲጠብቅ አደረገው (አነገሠው)። ሙሴም በዮቶር ቤት በግ ጥበቃ ስለታመነ የቤተ እስራ ኤል ጠባቂ አደረገው። ዛሬ ዓለም በሙሉ በአንደኛ የበላይ መሆን ይፈልጋል። ታላቅ ለመ ሆን ግን መጀመሪያ አገልጋይ መሆን እንዳለብን መጽሐፍ ያስተምረናል። ከዚህ ሁሉ በፊት ግን እኛ የምናገለግለው ልናውቅ ይገባናል። በመጨረሻም ለአገልግሎት ያለን ሁሉ ለዚህ ጨለማ ዓለም እንድናበራለት ስለሆነ የተጠራንለትን ዓላማ ልንፈጽም ሲገባን ወደ ኋላ መተውና መሰናከያ መሆን ግን ያስጠይቀናል። (ማቴ.፭፥፲፬) ዛሬ ችግራችን በ፩ጢሞ.፬፥፲፪ ላይ ምሳሌ እንድንሆን ተመርጠን ሳለ መሆን አለመቻላችን ስለሆነ እናስብበት።

ለዚህ ሁሉ የቅዱሳን ምልጃና ጸሎት ያሻናልና ምልጃቸው ከኛ ጋር የሁን አሜን።

ዲ.ደስታ ወ/ሰንበት ዘሀገረ ጅማ



# ቤተክርስቲያናችን ኤድስን በመከላከል ያገኘችው ዓለም አቀፍ እውቅና

በአምባሳደር ጥበቡ ሺፈራው

እኔ ባጭሩ ለማቅረብ የምፈልገው ቤተ ክርስቲያናችን ኤድስን በመከላከል ረገድ የምታደርገው እንቅስቃሴ ዓለም አቀፍ ዕውቅናና ድጋፍ እያገኘ መምጣቱን ነው። ለዚህም በማስረጃነት የሚከተሉትን ለመጥቀስ እወዳለሁ።

ቤተ ክርስቲያናችን ኅብረተሰቡ ከበሽታው ራሱን እንዲጠብቅ ስለም ታደርገው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ባደረባቸው ከፍተኛ ግምት ሐርቫርድ ዩኒቨርስቲ ዓለም ባንክና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ባቀረቡት ጥያቄ ከተቋማቱ ጋር በመተባበር በአፍሪቃ አዳራሽ እ.አ.አ.ኖቬምበር ኅዳር ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ ለ፩ ሳምንት የተካሄደውን ቁጥራቸው ከ፫፻ በላይ የሆነ የዓለም ሊቃውንት የተሳተፉበትን የመጀመሪያውን ዓለም አቀፍ ኤድስ ጉባኤ በኢትዮጵያ አዘጋጅታለች። በአዲስ አበባ ስታዲየም የተካሄደውን ከፍተኛ ሕዝባዊ ስብሰባም መርታለች። በሁለቱም ጉባኤዎች ላይ ቅዱስነታቸው ጠቃሚ መልእክቶች አስተላልፈዋል።

በአዲስ አበባ ስታዲየም በተካሄደው ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ በኤድስ ወላጆቻቸውን ስለ ተነጠቁ ሕፃናት ሲናገሩ፣ «በጨቅላ ዕድሜ፣ ባልጠነከረ ጉልበት የሚድሁና የሚውተረተሩ እኒህ አሳዛኝ ሕፃናት ወላጅን ያህል መከታ፣ ቤተሰብን ያህል አለኝታ ሲያጡ ኑሮ የቱን ያህል እንደ ሚጨልምባቸው መውጪያ መግቢያው እንደሚደናገራቸው መገመት አያዳግትም» በማለት በተለይ «ሕፃናትና ወጣቶች ከወላጆቻቸው ሊወርሱት የሚገባው ጤናን፣ ጽኑ ሃይማኖትን፣ የሀገርና የቤተሰብ ፍቅርን፣ ርኅራኄን የኃላፊነትን ስሜት እንጂ ኤድስን፣ ጥርጥርን፣ ጥላቻን፣ አለጊዜ ሞትን፣ ቀቢፀ ተስፋን፣ ባዕድ ባህልንና ሃይማኖትን ሊሆን አይገባውም» ሲሉ ተናግረዋል።

በሽታው የቱን ያህል አሰቃቂ እንደ ሆነ ሲገልጹም «በጥልቅ ላስተዋለው ኤድስ ከሞት ጋር የተያዘ ቀጠሮ ነው ማለት ይቻላል። እንደ ሚታወቀው ይህ ቀጠሮ መች ደርሶልኝ እየተባለ በናፍቆትና በጉጉት የሚታሰብ የእናትና የልጅ ቀጠሮ ሳይሆን ሰዎች በሰቀቀንና በፍርሃት ተውጠው የሚጠብቁት ነው። ይህ የሞት ቀጠሮ ቅስምን እየሰበረ፣ የመኖርን ተስፋ እያደበዘዘና ሕልውና እያሰለሰ ቀስ በቀስ እየገደለ ከመቃብር ጽልመት የሚከት ነው ብለዋል።

ስለ መፍትሔውም ሲያስረዱ «በአማኞች ዘንድ ኤድስን ለመከላከል ፍቱን የሆነው ብቸኛ መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠበቅ በቅድስና ሕይወት መመራት ነው። እግዚአብሔር አምላክ በደነገገው ሕግ መሠረት አንድ ወንድ በአንዲት ሴት አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ተወስነው በመተማመን መጽናት ነው። ሕይወትን በሥርዓት መምራት፣ አንደበትን መልክ ማስያዝና ራስን ለሕገ እግዚአብሔር ማስገዛት ነው። በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ፣ አስተዋይ ልቦና የተሰጠው ሰው በደመ ነፍስ እንደሚመሩት እንስሳት ሊሆን አይገባውም።» ካሉ በኋላ የራስንና የሀገርን ክብር መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን ሲያስገነዝቡ «ከአበው የወረስነውን ቀና ሃይማኖት፣ በጎ ምግባር፣ አኩሪ ባህልና መልካም ስም እያጣጣልን ሀገራችንን በኤድስ በሽተኞች ማጎደር ማስመዝገቡ በእጅጉ የሚያሳፍርና የሚያሳዝን ነው። የኢትዮጵያዊነታችንንም ክብር በእጅጉ የሚነካ ነው» በማለት ተናግረዋል።

አዲስ አበባ በሚገኘው በተባበሩት መንግሥታት አዲሱ የስብሰባ ማዕከል በተካሄደው ዓለም አቀፍ የኤድስ ጉባኤ ላይ ቅዱስነታቸው ባሰሙት የመክፈቻ ንግግር «የኤድስ ሕሙም ያለበትን የመንፈስ ጭንቀት ሲገልፁ፣ የኤድስ በሽተኛ ኅብረተሰቡ አግልሎኛል በሚል የጭንቀት ስሜት ሁል ጊዜ ይዋጣል። የሥነ ልቦና ጭንቀት ያሸብረዋል። ኅብረተሰቡ አርቆኛል አግልሎኛል የሚል ስሜት ስለሚበረታበት በራስ የመተማመን ስሜቱና ሰብአዊ ክብሩ ይሟሸሻል» ብለዋል።

ቅዱስ ጋብቻን ሕግ በማክበር ከጋብቻ በፊት ድንግልናን መጠበቅ ተገቢ ስለ መሆኑ ሲናገሩ፣ ቀደም ባለው ዘመን ከጋብቻ በፊት ድንግልናን ጠብቆ መገኘት የመልካም ጠባይ ምልክት የነበረ ከመሆኑም በላይ በወላጆችም ሆነ ወጣቶች ዘንድ እንደ ክብርና ኩራት ይቆጠር ነበር። የዲሲፕሊን መለኪያ፣ የታማኝነት መገለጫና የቅዱስ ጋብቻን ሕግጋት የማክበር ማረጋገጫ ተደርጎ ይወሰድ ነበር፣ ብለዋል።

በዚሁ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ መፍትሔውን አስመልክተው ሲናገሩ «ኤድስን ለመከላከል ብቸኛውና አስተማማኙ መፍትሔ የሚገኘው



www.ethiopianorthodox.org

ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ሆነ አጥ ብቀን እናምናለን። የሰው ልጅ በትሁት ልቦና በተሰበረ መንፈስና በአ ስተዋይ አእምሮ ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለበት። ልባችንንና አእም ሮአችንን ወደ እግዚአብሔር መልሰን ሕግጋቱን ብናከብር እግዚአብሔር አምላክ ይህን አስከፊ መቅሰፍት ከም ድረ ገጽ ሊያጠፋው ይችላል። እርሱ ዘላለማዊ እግዚአብሔር የደግነትና የርኅራኄ ምንጭ ስለሆነ ሕግጋቱን ካከ በርን እንድንሰቃይ አያሻመ» በማለት አስረድተዋል።

ኤድስን በመከላከል ረገድ የቤተ ክርስቲያኒቱን የጎላ አስተዋጽኦ በመገንዘብ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት የነበሩት ክቡር ሚስተር ክሊንተን ባደ ረጉላቸው ጥሪ መሠረት ቅዱስነታ ቸው ብፁዓን አባቶችን አስከትለው ዋሽንግተን በመገኘት በዓለም ኤድስ ቀን ስብሰባ ላይ ከኅዳር ፳፭–፳፪ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ተሳትፈዋል። ስብሰባው የተካሄደው በኋይት ሐውስና በሃዋ ርድ ዩኒቨርስቲ ሲሆን ቁጥራቸው ከ፵ በላይ የሆነ ከመላው ዓለም የተውጣጡ የታወቁ የሃይማኖት መሪዎች ተሳት ፈዋል። ቅዱስነታቸው በስብሰባው ላይ ባስተላለፉት መልእክት «በኢ ትዮጵያ ፫ ሚሊዮን ያህል ሰዎች በበሽ ታው እንደተያዙ ሲገመት ይህም በሦ ስተኛ ደረጃ ላይ ያስቀምጣታል። ይህም ቁጥር በዓለም በኤድስ ከተያዙ ሰዎች ዘጠኝ በመቶ መሆኑ ነው። በየቀኑ ኤድስ ፮፻፶ ኢምራች ዜጎቻችን በሞት ይቀጥፋል። ከዚህም በቀር በኢ ትዮጵያ በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ፩.፪ ሚሊዮን ሕፃናት እንደሚገኙ ሲገመት ይህም በዓለም ሦስተኛ ትልቁ አሃዝ ነው» ብለዋል።

ከዚህም በማከል ሲገልጹ «ለአ ንድ በኤድስ ለተያዘ ምእመን የሥጋ ምትን ከማሰብም ይልቅ በበሽታው ስያዝ ኃጢአት ስለ ፈጸምኩ ዘለ ዓለማዊ ሕይወትንም አጣለሁ ብሎ እንደ ማሰብ አስደንጋጭ ነገር የለም። ቤተ ክርስቲያን ሕሙማንን በማጽ ናናትና ሥርየትን እንዲያገኙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ልታደርግ ትችላለች። ቤተ ክርስቲያን ሰፊ መዋቅር፣ በር ካታ የሰው ኃይልና በሕዝቡም ዘንድ ተደማጭነት ስላላትና በከበሬታ ዓይን ስለምታታይ የበሽታውን መስፋፋት በመግታት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ልታ በረክት ትችላለች። ቤተ ክርስቲያን በሽታውን አስመልክቶ ያለውን ፀጥታ ለመስበር ትፈልጋለች» በማለት አስረድተዋል።

እንደዚሁም «ከሰሐራ በታች ላሉት ሀገሮች ኤድስን ለመከላከል ከ፪ እስከ ፫ ቢሊዮን ዶላር እንደሚያ ስፈልግ ሲታወቅ አሁን የተመደበው ግን ፮፪ ሚሊዮን ብቻ ነው። ስለዚህ ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ድጋፉን ከፍ እንዲያደርግ እንጠይቃለን። የዓለም ኅብረተሰብ በተለይ መድኃኒት ቀማሚ ፋብሪካዎች የሕክምና መድ ኃኒት ለዓለም ድኃ ሀገሮች እንዲደርስ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ሰዎችን ለመርዳት እየተቻለ ሰዎቹ ሲሞቱ ማየት በሞራል አንፃር ተቀባይነት የለውም»

ከቅርብ ጊዜ በፊት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ሚስተር ጆርጅ ቡሽ ለቅዱስነታቸው በላኩት መልእክት ላይ ቅዱስነታቸው ኤድስን በመከላከል ረገድ ለሚሰጡት አመራር አድናቆታቸውን ገልፀዋል። የመልእክቱ የአማርኛ ትርጉም የሚከተለው ነው።

## ከፕሬዚደንት ጆርጅ ቡሽ

## የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የተላከ መልእክት

ማርች ፳/፪ ሺህ ፩

መጋቢት ፲፩/፲፱፻፺፫

ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ብፁዕ ወቅዱስ ሆይ!

ፕሬዚዳንት ሆኜ በመመረጤ ስለ ላኩልኝ ጥልቅ የእንኳን ደስ ያለህ መልእክት ላመሰግንዎት እወዳለሁ። ድጋፈዎን በከፈተኛ ደረጃ የማየውና ክብደት የምሰጠው ነው።

በሚቀጥሉት አራት ዓመታት፣ በሀገሮቻችን መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት ለማሳደግ ከርስዎ ጋር ለመሥራት እሻለሁ። ኤድስን በተመለከተ ትምህርት በመስጠት ረገድ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ መሆንዎን ተረድቻለሁ። በአፍሪቃ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን ከሚያተ ኩርባቸው ከፈተኛ ግቦች መካከል ይህን በሽታ መዋጋት አንድ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ለሚያሳዩት አመራር አክብሮቴን እገልፃለሁ።

ሀገሬንና የአሜሪካንን ሕዝብ ለማ ገልገል ዕድል በማግኘቴ ኩብር ይሰ ማኛል፣ አስተማማኝ ሰላም ያለውና በይ በልጥ የበለጸገ ዓለም ለመገንባት እንዲ ቻል ከርስዎ ጋር አብሬ እሠራለሁ። ✣

ከአክብሮት ጋር

(ፊርማ አለው)

ጆርጅ ዳብልዩ ቡሽ



# ዜና መጽሔት

## ሕይወት ሳይኖር ሌላ ጉዳይ የለም

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢ ትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእ ጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት መመሪያ ሰጭነት፣ በሰንበት ትምህ ርት ቤቶች ማደራጃና ማስተባበሪያ መምሪያ አዘጋጅነት መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ከጧቱ ፪:፴–፯:፴ ድረስ በዓይነቱና በአቀራረቡ ልዩ የሆነ የኤድስን ስርጭት እንዴት መግታት ይቻላል በሚል ዙሪያ «ሕገ እግዚ አብሔር ይጠበቅ» በሚል ታላቅ ትም ህርታዊ ጉባኤ ተካሂዷል።

በዚህ ጉባኤ የተገኙ የትምህርታዊ ጉባኤው ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ ኦር ቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚ ተዳደሩ ድርጅቶች እና የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሠራተኞች፣ የ፹ አብያተ ክር ስቲያናት የቢሮ ሠራተኞች፣ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት የሰንበት ት/ቤቶች የሥራ አመራርና አባላት በሙሉ ተሳታፊ ሆኖአል።

ጉባኤው የታጀበው በመንበረ ጸባ ኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የሰንበት ት/ቤት መዘምራን ባቀረቡት መዝሙር ነው።

በዚህ ታላቅ ትምህርታዊ ጉባኤ በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎች ቀርበዋል።

ለምሳሌ:- «ሕገ እግዚአብሔር ይጠበቅ» በብፁዕ ዶክተር አቡነ ገሪማ፣ «መዳን በእግዚአብሔር ነው» በሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለ ማየሁ፣ «ዕድሜያችሁ እንዲረዝም እግዚአብሔር ባዘዛችሁ መንገድ ሂዱ» በመጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፣ «ልትድን ትወዳለህን» በመልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን፣ «ቤተ ክርስቲያናችን ኤድስን በመከ ላከል፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያገኘ ችው እውቅና» በአምባሳደር ጥበቡ ሽፈራው፣ የቀረቡ ሲሆን ከሊቃነ ጳጳሳትም ትምህርታዊ ምክር ያስተ ማሩ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ እና ብፁዕ አቡነ እንድርያስ አስተምረዋል። በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳ ሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክ ሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይ ማኖት ሰፊና ጥልቅ ትምህርት አስተምርዋል።

እጠቅሳለሁ «ሕይወት ሳይኖር ሌላ ጉዳይ የለም። የዓለም ሊቃውንት በዚሁ ጉዳይ ብዙ ደክመዋል። የተረ ዳነው ግን አለመቻላቸው ነው። መድ ኃኒት የሌለው በዓለም ላይ አንዳችም የለም። ኤች አይቪ ኤድስ መድኃኒት ያለው በሽታ ነው። እሱም በእግ ዚአብሔር ሕግ ተወስኖ መኖር ነው። ከሁሉም በላይ ተወዳዳሪ የሌለው እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን እግዚ አብሔርም እግዚአብሔርነቱን እንዲ ያምኑለት ይፈልጋል። ዓለም ግራ የተ ጋባው የእግዚአብሔርን ሕግ በመ ተው ነው። በዚህ እየተጐዳ ይገኛል። ስለዚህ ሌላ መንገድ የለውም በሕጉ ጸንቶ መኖር ብቻ ነው መፍትሔው።

ይህ ጉባኤ የተጀመረው ዛሬ አይ ደለም ይህን የመሰለ ጉባኤ በመላ ሀገሪቱ ተካሂዷል። ትምህርቱ እየተ ሰጠ ነው። ተገልጋዩ (ሕዝቡ) ግን በት ክክል አልሰማም የተነገረው በውስጥ ገብቶ ካልተረጐመው ጥቅም የለ ውም። ይህ ችግር ቤተ ክርስቲያን ሳሚዎች ናቸው? የሀብታም ልጆች፣ የድኃ፣ የመኳንንት ልጆች አይልም። ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ያጠቃ ልላል። ንስሐ መግባት ያለበት ሁሉም ነው። የበሽታው አስከፊነት የምና ውቃቸው ወገኖቻችን ደህና ዋሉ እያ ሉን ናቸው። ዓለም በሙሉ ታሟል፣ ዓለም የየራሱ እየረዳ ነው፣ እኛም ወገ ኖቻችንን እንርዳ። በታመመ ኅብረ ተሰብ መካከል ጤነኛ ሆኖ መኖር አይችልምና።

ሁሉም የሚሮጠው ወደ ወገኑ ነው። ካለተጠሩ መምጣት አይችሉም ይሆናል። ግን ጥሪያችን መድረስ አለ በት። አባቶች፣ እናቶች፣ ጧት፣ ማታ፣ ልጆቻችሁን ምከሩ አስ ተምሩ፣ የከፋ ነገር ውጤቱ ሞት ነውና ያ እንዳይከሰት መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ወጣት ልጆቻችንም የተማራ ችሁት በተግባር ማዋል እንጂ መስ ማቱ ብቻ በቂ አይደለም። ሌሎችን ለማስተማር ተዘጋጁ በትምህርት ቤት፣ በኳስ ሜዳ፣ በማኅበራዊ እንቅ ስቃሴ የምታገኙዋቸውን ንገሩ አስተ ምሩ፣ ራሳችሁን ጠብቁ ለወደፊትም የተለየ በዓል መኖር አለበት፣ ከዛሬ ጀምሮ በየሆኑ ያሉት ወጣቶች ተማ ሪዎች በኅብረት መማር አለባቸው። የተራቀቁ የመንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች ሊቃውንት፣ የሰንበት ትም ህርት ቤቶች አባላት የሚያስ ትምሩበት ወቅቱ አሁን ነው» በማለት ሰፊ ትምህርትና መመሪያ ሰጥቷል።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- የቅዱስነታቸው ትም ህርት ሙሉ ቃል በሚቀጥለው እትም የምናወጣው መሆኑን ከወዲሁ እንገልጻለን።



www.ethiopianorthodox.org

# የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ በጀርመን ዋና ከተማ በበርሊን ፓስትዳም ከተማ ተካሄደ

ኢ.አ.አ ከጥር ፳፱ ቀን እስከ የካቲት ፮ ቀን ፪ ሺህ ፩ ዓ.ም በጀርመንዋና ከተማ በበርሊን ፓስትዳም ከተማ በተካኼደው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ የተሳተፉ አባላት ፩፻፶፰ ተወካዮች ሲሆኑ:-

ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተወከሉ ልዑካን

፩. ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ

የሰሜን ወሎና የዋግ ኅምራ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤

፪. መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን የጠቅላይ ቤተ ክህነት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ናቸው።

በዚህ ስብሰባ በርካታ ዓለም አቀፍ አር እስተ ጉዳዮች የተነሡ ሲሆን የጉባኤው ውይይትና ውሳኔ እንደሚከተለው ባጭሩ ቀርቧል።

## የስብሰባው ውይይትና ውሳኔ

ስብሰባው በጸሎት ከተከፈተና እንዲሁም የምደሬተሩ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አራምና የዋና ጸሐፊው ዶ/ር ኮንሬድ ሬይዘር ሪፖርት ከተሰማ በኋላ ጉባኤው በሚከተሉት አርእስተ ጉዳዮች ላይ በመነጋገር ውሳኔ አሳልፏል።

፩. ስብሰባው «ዕርቅና ሰላም» በሚል መርሕ ላይ በማተኮር በዓለም ላይ ዕርቅና ሰላም ይሰፍን ዘንድ መታገል የወቅቱ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዐቢይ ተግባር መሆን እንዳለበት ተነጋግሯል። ይህን ተልዕኮ ለመፈጸምም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ «አደጋንና አደገኛነትን» የመከላከል ወይም ድል የመንሣት ዘመን (አሥርት ዓመት) በሚል መፈክር ሥር ለመንቀሳቀስም ወስኗል።

፪. በመላው ዓለም በተለይም በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ጦርነትና የእርስ በርስ ግጭት የሚካሄድባቸውን አገሮች በስም በመጥቀስ በእነዚህ ሀገሮች ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን የተባበሩት መንግሥታት የሚያደርገውን ጥረት በማገዝ አብያተ ክርስቲያናት በዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ደረጃ ጥረት እንዲያደርጉ ጉባኤው በሙሉ ድምፅ ወስኗል፤ ለሚመለከታቸው ወገኖች የዕርቅና ሰላም ጥሪ ደብዳቤ እንዲተላለፍም ተስማምቷል።

፫. የኢትዮ –ኤርትራ ጉዳይ በስብሰባው ላይ በአጀንዳ ባይቀርብም ግጭቱ ከምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች የሃይማኖት ድርጅቶች ኃላፊዎች ጋር በመተባበር እስከ አሁን ያደረገችውን ጥረት የሚገልጽ አጭር ዘገባ እንድናቀርብ ስለተፈቀደልን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት መሪነት የሚካሄደው የሰላም ኮሚቴ ከኤርትራ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር በስንት ቦታና ስንት ጊዜ ተገናኝቶ የዕርቅና ሰላም ጉባኤ እንዳካሄደና ያም ጥረት አሁን ለሚታየው መልካም ውጤት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልዑካን ተገልጸዋል። የጉባኤው ተሳታፊዎችም የቤተ ክርስቲያኒቱ ጥረትና አሁን የሚታየው የሰላምና የዕርቅ ጉዞ እጅግ እንዳስደሰታቸው ገልጸዋል። ከልዑካኑ የቀረበውም መግለጫ በስብሰባው ቃለ ጉባኤ እንዲያዝ ተደርጓል።

፬. አደጋና አደገኛነት ከዓለም ተወግዶ ሰላምና ፍትሕ እንዲሰፍን አሁን በተጀመረው ክፍለ ዘመን አሥርት ዓመት የተቻለውን ሁሉ ተልዕኮ እንደሚፈጽም ድርጅቱ ያለውን ቁርጥ ዓላማ ለመግለጽ ያህልም የጉባኤው ተሳታፊዎች በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በቦምብ ፈርሶ ሳይጠገን በመዘከርነት በተቀመጠ አንድ የበርሊን ከተማ ቤተ ክርስቲያን በመገኘትና መብራት በማብራት የሰልፍ ጉዞ አድርገዋል።

፭. በድርጅቱ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት አባላት መካከል የተነሣውን አለመግባባት በሚመለከት በሁለቱ ወገኖች መካከል ለተፈጠረው አለመግባባት መነሻ የሆኑ ነገሮችን ከነመፍትሄያቸው አጥንቶ እንዲያቀርብ ተወስኖ የነበረ ሲሆን የተጨበጠ ጥናት አድርጎ ባለማቅረቡ የኦርቶዶክሱ ክፍል ተሳታፊዎች ቅሬታቸውን ገልጠዋል። ለተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በግልጽ በማስቀመጥና እንዲሁም የተመሠረተበትን ዓላማ በመከተል በድርጅቱ አወቃቀርና የአሠራር ሂደት ላይ ሊኖር የሚገባውን ለውጥ በአሳብ ደረጃ አጥንቶ ለሚቀጥለው ስብሰባ እንዲያቀርብ ጥብቅ መመሪያ ተሰጥቷል።

፮. ዝምባብዌ ላይ በተካሄደው ስምንተኛው የድርጅቱ አጠቃላይ ስብሰባ የተከሠተውን ልዩነት ለመመርመርና መፍትሔም ለማምጣት የተቋቋመው ኮሚሽን ጥናት ቀርቦ ከአንድ ውሳኔ ላይ እስኪደርስ ድረስ የሥራ ጊዜያቸው ያለፈው የዋና ጸሐፊው የዶ/ር ኮንሬድ ሬዘር መቆየት አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ምርጫው ለአንድ ዓመት እንዲራዘም ተደርጓል።

፯. ዘጠነኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አጠቃላይ ጉባኤ በ፪ ሺህ ፮ ዓ.ም እንዲካሄድ ተወስኗል ቀኑና ቦታው ግን ወደ ፊት በድርጅቱ ጽ/ቤት ተጠንቶ እንዲቀርብ ኃላፊነት ተሰጥቷል።

፰. የሚሽንና ኢባንጀሊዝም ጉባኤ በ፪ ሺህ ፬ ወይም በ፪ ሺህ ፭ ዓ.ም መጀመሪያ ላይ እንዲካሄድ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

፱. በ፪ ሺህ ፪ ዓ.ም የሚካሄደው የማዕከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ በአካል ጉዳተኞች (አቅመ ደካሞች) ላይ ያተኮረ እንዲሆን ተጠቁሟል።

፲. ጉባኤው በዐቢይነት የተነጋገረባቸው እነዚህ ሲሆኑ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተነጋገረውም ቡድን በመከፋፈልና በአጠቃላይ ስብሰባ በመወያየት ነው። የዚህ ስብሰባ ውሳኔዎች ሁሉ የተላለፉት በድምጽ ብልጫ ሳይሆን በአብዛኛው በሙሉ ድምፅ ስምምነት ስለሆን እንደ ጠንካራ ጎን ታይቶ ተደንቋል።

በቤተ ክርስቲያናችን ልዑካን የተፈጸመ ተጓዳኝ መንፈሳዊ ተልዕኮ

በማዕከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ ለመገኘት ቤተ ክርስቲያናችንን ወክሎ ወደ ጀርመን – በርሊን የሄደው የልዑካን ቡድን የተመራው በብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሰሜን ወሎና የዋግ ሕምራ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እንደ መሆኑ መጠን በፍራንክፈርት፤ በበርሊንና በሙኒክ ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያናችን ተከታዮች ምእመናን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል። የአገልግሎቱን ዓይነት በአጭሩ ለመግለጽ ያህል፤

ሀ. በብፁዕነታቸው የሚመራው የልዑካን ቡድን በፍራንክፈርት ቅድስተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመገኘት የእስተርእዮ ማርያምን በዓል አክብሯል። በበዓሉ ላይ ብፁዕነታቸው ለምእመናኑ ትምህርትና ቡራኬ በመስጠትና ቀድሶም በማቁረብ ምእመናኑ ሊያገኙ የሚገባቸውን መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲያገኙ አድርገዋል።

ለ. ቀጥሎም ጥር ሃያ ስድስትና ሃያ ሰባት ቀን (ኢ.አ.አ የካቲት ፫–፬) በበርሊን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን ጸሎት ቤት ለምእመናኑ ሙሉ አገልግሎት ተሰጥቷል። ይህ ቀን የጸሎት ቤቱ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ የሚቋቋምበት ዕለት ስለነበር በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ፈቃድና ቡራኬ ታቦተ አማኑኤል በብፁዕ አቡነ ቄርሎስ እጅ ተልዕኮ አዲሱ ቤተ ክርስቲያን በብፁዕነታቸው ቡራኬ ተመርቆ ተከፍቷል። በዋዜማውም ሆነ በበዓሉ ዕለት በተካሄደው ሥርዓተ ጸሎት ላይ እያሌ ኢትዮጵያውያን ምእመናን ተገኝተው ለፈጣሪያቸው ምስጋና አቅርበዋል። ብፁዕነታቸው ለተሰበሰቡት ምእመናን ትምህርትና ቡራኬ በመስጠት የአዲሱን ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ቤት ሥርዓተ ጸሎት በማድረስና ቀድሶም በማቁረብ በፈጸሙት አገልግሎት ምእመናን የቱን ያህል እንደ ተደሰቱ ከአንደበታቸው ከሚወጣው ቃልና ከፊታቸውም ከሚነበበው ፈገግታ ማረጋገጥ ይቻል ነበር። በዚህ በዓል ላይ ጥሪ የተደረገላቸው የሌሎች አብያተ ክርስቲያናትና ድርጅት ተወካዮች የተገኙ ሲሆን በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ ዶ/ር ቀሲስ መርዓዊ ተበጀ የአዲሱን ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ በማስመልከት ንግግር አድርገዋል። ፕሮፌሰር ራይንሃርድ ፍይከት የበርሊን ዩኒቨርሲቲ ታዋቂ መምህር ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሰፋ ያለ ዘገባ አቅርበዋል።

ሐ. ይህ የተፈጸመው በስብሰባው ወቅት ሲሆን ከስብሰባው በኋላ በቁስ መስፍን ገ/ማርያም በሙኒክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህን ጋባዥነት ልዑካን ወደ ሙኒክ ተጉዞ በዚያ በተቋቋመው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የሦስት ቀን መንፈሳዊ አገልግሎት ፈጽሟል። አገልግሎቱ የተካሄደው በብፁዕ አቡነ ቄርሎስ መሪነት እንደመሆኑ መጠን ምእመናኑ በሊቀ ጳጳስ ደረጃ ትምህርት፤ ቡራኬና የጸሎተ ቅዳሴ አገልግሎት በማግኘታቸው የተሰማቸው ደስታ ወሰን አልነበረውም።

መ. በሙኒክ ቆይታው ወቅት በአይስቴት ከተማ በሚገኘው የአርየንቴ ኮሌጅ በትምህርት ላይ የሚገኙትን አራት የቤተ ክርስቲያናችን ደቀ መዛሙርት በቦታው ተገኝቶ አነጋግሯል። ደቀ መዛሙርቱ በትምህርታቸውም ሆነ በኑሮአቸው በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን የኮሌጅ ዳይሬክተር ዶ/ር አብርሃም ፒርማየር ባደረጉት ገለጻ የልዑካኑ ቡድን ለመረዳት ችሏል። ወደፊትም ቢሆን እንደነዚህ ያሉትን ደቀ መዛሙርት ኮሌጁ ፈቃደኛ መሆናቸውን የኮሌጅ ዳይሬክተር ጨምረው ገልጸዋል። ሆኖም ከተላኩት ደቀ መዛሙርት ለመቀበል መካከል አንድ ቄስ ባለመኖሩ ልጆቹ ቀድሶ ለማቁረብም ሆነ ለመቁረብ አለመቻላቸውን የኮሌጁ ኃላፊ በቅሬታ ገልጸዋል። አንድ ሥዕል ላይ ከኢትዮጵያ ተልዕኮ በኮሌጅ ቅጽር ግቢ የኢትዮጵያ ሥዕል በመሣል የኮሌጅን ግቢ ሊያስጌጥላቸው ቢችል ወጪውን ኮሌጅ እንደሚሸፍኑም ቃል ገብተዋል።

የልዑካን ቡድኑ በጀርመን ቆይታ ምእመናን የቤተ ክርስቲያናቸውን አንድነት ጠብቀው በሰላምና በፍቅር የቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው ተገልጋይ እንዲሆኑ፤ በየደረሰበት ትምህርትና ምክር ሰጥተዋል።

## አጠቃላይ አስተያየት

በአሁኑ ጊዜ በጀርመን አራት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተቋቁመው በዚያ ለሚገኙ ምእመናን የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆኑ እነዚህም፤

የኮለኝ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

የፍራንክፈርት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

የሙኒክ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን

የበርሊን አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ናቸው።

የኮለኝ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በጀርመን የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን ሲሆን የተመሠረተውም ሆነ አገልግሎቱ የሚ ካሄደው በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊና ተጠሪ በሆኑት በሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ ነው።

እንዲሁም የሙኒክ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በቁስ መስፍን ገ/ማርያም የፍራንክፈርት ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን በአባ ሲራክ ወ/ሥላሴ የተሟላ አገልግሎትና አመራር በማግኘት ላይ ሲሆኑ ለበርሊን አማኑኤል ቤተ ክርስቲያንም አንድ ካህን በቅዱስነታቸው በቀዋሚነት ስለተመደበ ምድብ ካህኑ በቅርቡ ወደ ሥፍራው ተልከው ሥራቸውን እንደሚጀምሩ ይጠበቃል። በጀርመን የአንድ ቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ በዓል በሚከበርበት ጊዜ የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን ከሩቅ እየተጓዙ በበዓሉ ላይ ስለሚገኙ ኅብረቱ ክብረ በዓሉን ደማቅ እያደረገው ይታያል። በተለይ በመዘምራኑ የሚቀርበው ማኅሌታዊ መዝሙር ክብረ በዓሉን ፍጹም ኢትዮጵያዊ ስለሚያደርገው የውጭ ሰዎች ሁሉ ከመገረም አልፈው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያከብሩ እያደረጋቸው ይገኛል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በውጭ ሀገር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የበለጠ ተጠናክረው በውጭ ለሚገኙ ምእመናን የበለጠ አገልግሎት እንዲሰጡና ገና ቤተ ክርስቲያን ላልተቋቋመላቸው ምእመናንም እንዲቋቋምላቸው ከፍተኛ ትኩረት የሰጡበት ስለሆነ በጀርመን የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትም በበለጠ ተጠናክረው አገለግሎታቸውን እንደሚቀጥሉ ያለን እምነት ጽኑዕ ነው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አሜን

## ከዩጋንዳ መልስ

ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃና ማስተባበሪያ መምሪያ ዋና ኃላፊ ከጥር ፳፫– ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም የወጣቶች ጉባኤ በዩጋንደ በካንፓላ መዲና ተገኝተው የቤተ ክርስቲያናችን ልዑክ በመሆን የቤተ ክርስቲያናችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ለጉባኤ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቧል።

በዚሁ ጉባኤ የተገኙት ሀገሮች ኢትዮጵያ፤ ኬንያ፤ ዩጋንዳ ሲሆኑ የጉባኤው መለያ "Eastern Africa Sub-Regioal Leaders Meeting" የሚል ሆኖ በመርሐ ግብሩ ከተቀረጹ አጀንዳዎች፤

.Youth peace training manual

.Subregional General overview and activities report

.Objectives and Expectations

.Countr report

.Group discussion and national project proposals and planning

.Country presentation of proposals

.Subregional strategies and project planning

.Sharing on upcoming regional programs

.Subregional plan of action የሚሉ ናቸው

ጉባኤው በእነዚህ ርእሶች ጥልቅ ውይይት የተደረገ ሲሆን በስብሰባው የተገኙት የጉባኤው አባላት አብዛኞዎቹም ወጣቶች ቢሆኑም ለሀገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን የነበራቸው አክብሮትና ታሪካዊ ግንዛቤ በእጅጉ አስደሳች እንደ ነበር ከቀረበው ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል።

## እርቅና ሰላም በዲላ ከተማ

የዲላ ከተማ በሲዳሞ ሀገረ ስብከት በወናጎ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ከተማ ሦስት አብያተ ክርስቲያን ይገኛሉ እነሱም:-

፩ኛ. የዲላ መካነ ቅዱሳን አ/ገ/መንፈስ ቅዱስ

፪ኛ. የዲላ ቅዱስ ጊዮርጊስ

፫ኛ. የዲላ ደብረ ኀኀት ቅ/ሚካኤል ናቸው።

እነዚህ ሦስት አብያተ ክርስቲያናት ለተወሰነ ጊዜ በአንድ ላይ ሲተዳደሩ ቆይቷል። ከ፲፱፻፹፱ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ድረስ በመካከላቸው በተፈጠረው አለመግባባት ለአምስት ዓመታት ያህል ተለያይተው ቆይተዋል።

በዚህም ምክንያት የከተማው ምዕመናን በሁለት ጎራ በመከፈል እስከ መወጋገዝ የደረሰ ፀብ እንደ ነበር ታውቋል።

ይሁን እንጂ የከተማው ምዕመናን የጋራ ስብሰባ በማድረግ ፲፪ አባላት ያለው የዕርቅና የሰላም ኮሚቴ አቋቁመው በሀገረ ስብከቱ አንታዘዝም ባሉት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ተፈጥሮ የነበረው ከፍተኛ አለመግባባት ኮሚቴው ባደረገው ጥረት ወደ ዕርቅ በማምራቱ ለዚህም አፈጻጸም ከዋናው መሥሪያ ቤት፡

፩. ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፡ የሰሜን ወሎና የዋግ ሕምራ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፡

፪. ቀሲስ በላይ ተገኝ የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ

፫. ከቦረና ሀገረ ስብከት ብፁዕ አቡነ ዲሜጥሮስ፡

፬. ከሲዳሞ ሀገረ ስብከት ብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ

፭. መምህር ኃይለሥላሴ ይግዛው የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ባሉበት ከየካቲት ፳፫ ቀን እስከ ፳፬ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በተደረገው የሰላም ውይይት በሀገረ ስብከቱና በመካነ ቅዱስ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እና በቅዱስ ጊዮርጊስ አብያተ ክርስቲያን ተፈጥሮ የነበረው አለመግባባት በእርቅ ተፈጽሟል።

ይህ ለአምስት ዓመታት የዲላ ከተማን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምዕመናንን ከፋፍሎ ሲያተራምስ የቆየው ሊያበቃ የቻለው፡

፩. ራሱ የዲላ ከተማ ሕዝብ ሰላምን በመፈለግ ጉዳዩን ተከታትለው የሚያስፈጽሙ ፲፪ የሰላምና የእርቅ ኮሚቴ አባላትን መርጦ ክትትል በማድረግ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠቱ፡

፪. ከዋናው መ/ቤት ችግሮችን በብቃት ሊያስወግዱ የሚችሉ ልዑካን በመመደባቸው፡

፫. በብፁዕ አቡነ ዲሜጥሮስ እና በአቡነ በርተሎሜዎስ ከፍተኛ ጥረት መሆኑን ከተላከልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል። ✣





www.ethiopianorthodox.org